# በትግራይ ክልል ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የቃላት አመራረጥ ፤አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋከልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም ኤ ዲግሪ
ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ሞላ አጽብሃ

የካቲት 2003 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ፋከልቲ

## የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በትግራይ ክልል ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የቃላት አመራረጥ ፤አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና

በ

ሞላ አጽብሃ

የፈተና ቦርድ አባላት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ADDIS A
LIBRARY

___________________ ___________________

አማካሪ ፊርማ

___________________ ___________________

ፈታኝ ፊርማ

# ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የአሰራር አቅጣጫን በማመልከት፣ የጥናቱን ረቂቅ በማረም ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠትና በማበረታታት ጥናቱ የአሁኑን ቅርጽ እንዲይዝ ለረዱኝና በተጨማሪም የእረፍት ጊዜያቸውን ጭምር መስዋዕት በማድረግ፣ በዚህ ወቅት አይደርስ የነበረውን ስራዬን ለፍጻሜ እንዲደርስ ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ ለአማካሪዬ ለአቶ ጌታቸው እንዳለማው (ረ/ፕሮፌሰር) ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ለቤተሰቤ ማዋል የሚገባኝን ጊዜ ለትምህርቴና የጥናት ስራዬ አድርጌ፣ በእርጋታ እንድከታተልና እንድሰራ በትዕግስት ከጎኔ ለቆሙት ባለቤቴ ወ/ሮ አበባ ግደይና ልጆቼ (ሚኪና ሮዳስ) የብርታቴ መሰረት ናችሁና ላመሰግናችሁ ወደድኩኝ ፡፡

በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬም ሙሉ ወጪዬን በመሸፈን እንድማር ለፈቀዱልኝ ለትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ እና ለማይጨው ከተማ ትምህርት ቤቶች ጽሕፈት ቤት ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም የጥናቱን ስራ የማከናውንበት በጀት በመመደብ ከፍተኛ እገዛ ያደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

በትምህርት ቆይታዬ ዘወትር ድጋፋችሁ ሳልተለየኝና በማቴሪያልም ሆነ በሞራል ለረዳችሁኝ ወንድሞቼና እህቶቼ ምስጋናዬን ይድረሳችሁ፡፡

መጠይቆችን በማባዛትና ተፈላጊ ሰነዶችና መረጃዎች እንዳገኝ ለተባበሩኝ የእንዳ መሆኒ ወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤት፣ የአራቱም ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራንና መምህራን፣ እንዲሁም የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ አዘጋጅና ተማሪዎች ያደረጉልኝን እገዛ ለዚህ ውጤት ያበቃኝ በመሆኑ ከልብ አመሰግናቸዋለሁ፡፡ በተለይም በማቴርያልና በሃሳብ የደገፈኝ ጓደኛዬ የአቶ ሰማን ሞላ፣ የክፍል ጓደኞቼ የአሚነት ሸምሱ እና እያሱ መሠለ ውለታ የሚረሳ አይደለም፡፡

በመጨረሻም አድካሚውን የጽሕፈት ሥራ ሳትሰለች ለተየበችልኝ ወ/ሪት አርማዬን አደራ የማይዘነጋ እና ወደር የሌለው ውለታም ምስጋናዬም ከፍ ያለ ነው፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና ........................................ I

ማውጫ ........................................ II

የሰንጠረዥ ማውጫ ........................................ V

አጠቃሎ ........................................ VII

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ ........................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................ 4

1.2 የጥናቱ ዓላማ ........................................ 4

1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት ........................................ 5

1.4 የጥናቱ ወሰን ........................................

ምእራፍ ሁለት

የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ........................................ 6

2.1 የቃላት ምንነት ........................................ 7

2.2 የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት ........................................ 10

2.3 የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ ........................................ *11*

2.3.1 የቃላት ድግግሞሽ ........................................ *13*

2.3.2 የተማሪዎች ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ መጣጣም ........................................ *14*

2.3.3 በቅርብ መገኘት ........................................ *14*

2.3.4 ተስተማሪነት (Learn ability) ........................................ *15*

2.3.5 የፍቺ ሽፋን ........................................ 16

2.4 የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ........................................ *17*

2.4.1 ቃላት በሚያወሱት ርእሰ ጉዳይ (Topic) ማደራጀት ........................................ *17*

2.4.2 ቃላትን በፍቺ ማደራጀት ........................................ *18*

2.4.3 ቃላትን በቅርጽ ማደራጀት ........................................ 18

2.5 የቃላት ትምህርት ማቅረብያ መንገዶች ........................................ *20*

2.5.1 ቃላትን በዐውድ አስደግፎ ማቅረብ ........................................

........................................................ 23
2.5.2 ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው አማካኝነት ማቅረብ ........................................ 24
2.5.2.1 ቃላት በተመሳሳይ ፍቺ ማቅረብ (Synonym) .................................... 24
2.5.2.2 የቃላት ተቃራኒ ፍቺ ........................................................ 26
2.5.2.3 የቃላት አጠቃላይ ዝርዝር ግንኙነት ................................................ 26
2.5.2.4 አበሮ ተሰላፊ ቃላት ........................................................ 27
2.5.3 የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርአት መሰረት አድርጎ ማቅረብ.................... 29
2.5.4 የቃላት አጠቃቀምና አመራረጥ ስልትን መሰረት በማድረግ ማቅረብ .............. 29
2.5.4.1 እማሪያዊና ፍካሪያዊ ........................................................ 30
2.5.4.2 ፈሊጣዊ አነጋገሮች ........................................................ 32
2.5.4.3 የተለመዱ አገላለጾች ........................................................ 32
2.5.5 ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ማቅረብ ................................................ 34
2.5.6 የቃላት ትምህርትን በመዝገብ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ................................ 35
2.5.7 የቃላት ትምህርት መመሪያ የአቀራረብ ግልጽነት ........................................ 36
2.6 በሀገር ውስጥ የተካሄዱ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት........................................

ምዕራፍ ሶስት ........................................................................ 39
3.1 የአጠናን ዘዴ........................................................................ 39
3.2 የናሙና አመራረጥ ........................................................................ 39
3.2.1 የመጸሐፍ ናሙና አመራረጥ ........................................................ 39
3.2.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ................................................ 40
3.2.3 የመምህራን የናሙና አመራረጥ ........................................................ 40
3.2.4 የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ ........................................................ 41
3.3 መረጃ መሰብሰቢያ መሳርያዎች ........................................................ 41
3.3.1. የሰነድ ምርመራ ........................................................................ 41
3.3.2 የመምህራን የጹሁፍ መጠይቅ ........................................................ 42
3.3.3 የተማሪዎች የጹሁፍ መጠይቅ ........................................................ 43
3.3.4 የባለሙያዎች ቃለመጠይቅ ........................................................ 43
3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........................................................................

ምእራፍ አራት

የጥናቱ ውጤት ትንተና እና ማብራሪያ ................................................ 44
4.1 የተተኳሪ መጽሐፉ ዳራ ........................................................................ 46
4.2 የናሙና መምህራን፣ተማሪዎችና የመጽሐፉ አዘጋጆች ዳራ........................................

.............................................................................................. 46

4.2.1 የናሙና መምህራን ዳራ ............................................................................ 47

4.2.2 የናሙና ተማሪዎች ዳራ መግለጫ ...................................................................... 48

4.2.3 የመጽሐፉ አዘጋጅ ዳራ .............................................................................. 49

4.3 የቃላት አመራረጥ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና ............................................... 53

4.4 የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ............................................................................ 58

4.5 የቃላት ትምህርት አቀራረብ ትንተና ................................................................ 58

4.5.1 የቃላት አውዳዊ አቀራረብ

4.5.2 የቃላት ተመሳስሎና ተቃርኖ፣ ዝርዝርና አጠቃላይ እና የአብሮ ተሰላፊ ታላት ..... 64

አቀራረብ ትንተና ................................................................................... 68

4.5.3 የቃላት ርባታና ምስረታን አቀራረብ ትንተና .................................................. 71

4.5.4 የቃላት አጠቃቀምና አመራረጥ ስልት መሰረት በማድረግ ማቅረብ ........................ 73

4.5.5 ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ማቅረብ .......................................................... 75

4.5.6 የቃላት ትምህርት በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ........................................ 78

4.5.7 የቃላት ትምህርት መመሪያ አቀራረብ ግልጽነት

ምእራፍ አምስት

ማጠቃለያና አስተያየት ...................................................................................... 81

5.1 ማጠቃለያ ...................................................................................................... 84

5.2 አስተያየቶች ................................................................................................ 86

ዋቢ ጽሑፎች

አባሪ ............................................................................................................. 91

ሀ. ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ አስረጂዎች ................................................................... 97

ለ. ለ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ .......................... 101

ሐ. የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ...................................................................... 103

መ. ለመጽሐፍ አዘጋጅ የቀረበ ቃለ መጠይቅ

# የሰንጠረዥ ማውጫ


ሠንጠረዥ 1፦ የትግራይ ክልል ስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በየምዕራፉ በሚገኙ መልመጃዎች ሥራ የቀረቡ ተግባሮች በጥቅሉ .................. 45

ሠንጠረዥ 2፡- የናሙና መምህራኑን ዕድሜ፣ፆታ፣ የሰለጠኑበት ትምህርት፣ የትምህርት ደረጃና አገልግሎት ዘመን እና በመቶኛ የመግለጽ ሰንጠረዥ ....................46

ሠንጠረዥ3፡- የናሙና ተማሪዎች ሁኔታ መግለጫ ....................47

ሠንጠረዥ 4 በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የቃላት ትምህርት ይዘቶች ሽፋንና ለደረጃው ስላላቸው መጣኝነት ለቀረቡ ጥያቄዎች በመምህራን የተሰጠ መልስ፡ ...............51

ሠንጠረዥ 5፡- የመጽሐፉ የቃላት ትምህርት ይዘት ለደረጃው ስላለው መጣኝነት ለቀረበው ጥያቄ በተማሪዎች የተሰጠ መልስ....................52

ሰንጠረዥ 6፡- ስለመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ለቀረቡ ጥያቄዎች በመምህራን የተሰጡ ምላሾች ....................55

ሰንጠረዥ7፦ ስለመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ለቀረቡ ጥያቄዎች በተማሪዎች የተሰጡ መልሶች ....................56

ሠንጠረዥ 8 ፡- ስለመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት መንገዶች ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ መልሶች ....................57

ሰንጠረዥ 9፦ ስለቃላት አውዳዊ አቀራረብ ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ መልሶች ....59

ሰንጠረዥ 10፡- ስለቃላት አውዳዊ አቀራረብ ለተማሪዎች ለቀረበው ጥያቄና የተሰጠ መልስ .......60

ሠንጠረዥ 11፦ ስለተተኳሪ መጽሐፉ የቃላት አውዳዊ አቀራረብ ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ ....................61

ሠንጠረዥ 12፡- ስለ አረፍተነገራዊ አውዶች ተተንባይነት እና አውዳዊ ባህሪ በተመለከተ ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ መልሶች....................63

ሠንጠረዥ 13 ፡- ስለመጽሐፉ የቃላት የፍቺ ዝምድና አቀራረብና የመምህራን ምላሽ ..............64

ሠንጠረዥ 14፦ የፍቺ ዝምድና ትምህርት አቀራረብ ለተማሪዎች የቀረበ ጥያቄና የተሰጠ ምላሽ ....................65

ሠንጠረዥ 15፡- ስለቃላት ፍቻዊ ዝምድና አቀራረብ ከሰነድ ምርምር የተገኘ መረጃ ...........67

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1፦ የትግራይ ክልል ስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በየምዕራፉ በሚገኙ መልመጃዎች ሥራ የቀረቡ ተግባሮች በጥቅሉ ..................... 45

ሠንጠረዥ 2፦ የናሙና መምህራኑን ዕድሜ፣ፆታ፣ የሰለጠኑበት ትምህርት፣ የትምህርት ደረጃና አገልግሎት ዘመን እና በመቶኛ የመግለጽ ሰንጠረዥ ..............................46

ሠንጠረዥ3፦ የናሙና ተማሪዎች ሁኔታ መግለጫ ......................................................47

ሠንጠረዥ 4 በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የቃላት ትምህርት ይዘቶች ሽፋንና ለደረጃው ስላላቸው መጣኝነት ለቀረቡ ጥያቄዎች በመምህራን የተሰጠ መልስ፡...............51

ሠንጠረዥ 5፦ የመጽሐፉ የቃላት ትምህርት ይዘት ለደረጃው ስላለው መጣኝነት ለቀረበው ጥያቄ በተማሪዎች የተሰጠ መልስ..........................................................................52

ሰንጠረዥ 6፦ ስለመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ለቀረቡ ጥያቄዎች በመምህራን የተሰጡ ምላሾች ............................................................................55

ሰንጠረዥ7፦ ስለመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ለቀረቡ ጥያቄዎች በተማሪዎች የተሰጡ መልሶች ..........................................................................................56

ሠንጠረዥ 8 ፦ ስለመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት መንገዶች ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ መልሶች ...........................................................................57

ሰንጠረዥ 9፦ ስለቃላት አውዳዊ አቀራረብ ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ መልሶች ....59

ሰንጠረዥ 10፦ ስለቃላት አውዳዊ አቀራረብ ለተማሪዎች ለቀረበው ጥያቄና የተሰጠ መልስ .......60

ሠንጠረዥ 11፦ ስለተተኳሪ መጽሐፉ የቃላት አውዳዊ አቀራረብ ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ ..........................................................................................61

ሠንጠረዥ 12፦ ስለ አረፍተነገራዊ አውዶች ተተንባይነት እና አውዳዊ ባህሪ በተመለከተ ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ መልሶች...........................................63

ሠንጠረዥ 13 ፦ ስለመጽሐፉ የቃላት የፍቺ ዝምድና አቀራረብና የመምህራን ምላሽ ............64

ሠንጠረዥ 14፦ የፍቺ ዝምድና ትምህርት አቀራረብ ለተማሪዎች የቀረበ ጥያቄና የተሰጠ ምላሽ ..........................................................................................65

ሠንጠረዥ 15፦ ስለቃላት ፍቻዊ ዝምድና አቀራረብ ከሰነድ ምርምር የተገኘ መረጃ ...........67

ሠንጠረዥ16፡- የቃላት እርባታና ምስረታን የተከተለ ትምህርት አቀራረብ ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ ምላሾች ......................................................69

ሠንጠረኝ 17፦ ስለ ቃላት ርባታና ምስረታ ትምህርት የተማሪዎች ምላሽ ....................................69

ሠንጠረዥ18፡ ስለመጽሐፉ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም በመጽሐፉ የቀረቡበትን ሁኔታ ለመምህራን ለቀረበው ጥያቄና የተሰጠ መልስ ..........................................71

ሠንጠረዥ19፡- ስለመጽሐፉ የቃላትን አመራረጥና አጠቃቀም ስልት አቀራረብ ለተማሪዎች የቀረበ ጥያቄና የጠሰጠ ምላሽ ......................................................72

ሠንጠረዥ 20፡ የቃላት ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ስላላቸው ጥምረት ለመምህራን ለቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ ምላሾች ......................................................74

ሠንጠረዥ 21፡- በመጽሐፉ ስለመዝገበ ቃላት የተደገፈ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ለመምህራን የቀረበው ጥያቄና የተሰጠ ምላሽ ......................................................76

ሠንጠረዥ 22፡ በመዝገበ ቃላት የተደገፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎች ምላሽ........77

ሠንጠረዥ 23፦ ስለቃላት ትምህርት መመሪያዎች ተገቢነት መምህራን ምላሽ .......................79

ሠንጠረዥ 24፦ በተተኳሪ መጽሐፉ ውስጥ ስለ ቃላት ትምህርት መመሪያዎች ግልጽነት የተማሪዎች ምላሽ ......................................................79

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ1990 ዓ.ም በትግራይ ክልል ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱትን የቃላት ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መተንተን ነው። ጥናቱን ከግብ ለማድረስም የተለያዩ ምሑራን ስለ ቃላት ትምህርት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ባነሷቸው ንድፈ ሃሳባዊ መሠረቶችና መርሆዎች ላይ በመመርኮዝ አጥኚው በመማሪያ መጻሕፉ ላይ የሰነድ ፍተሻ በማድረግና በአጋዥነትም የጽሑፍና የቃለ መጠይቆችን መረጃ ማሰባሰቢያነት ተጠቅሟል። በሰነድ ምርመራ፣ በጽሑፍ መጠይቅና በቃል መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎች በቁጥርና በመቶኛ ከተተነተኑ በኋላ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል። ጥናቱ በትግራይ ክልል ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጀው አማርኛ መማሪያ መጸሐፍ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ በታላሚው የክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች የባህልና የዕውቀት ዳራ በአገናዘበ መልኩ የተዘጋጁ ናቸው። ቃላቱ ከሚነበቡ ጽሑፎች ጋር የተያያዙ፣ መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀ የተመለከቱ፣ ወቅታዊ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቁ፣ አካባቢን ለመግለፅና ለመገንዘብ የሚያስችሉ ናቸው። ከአደረጃጀታቸውም አንፃር ተከታታይነታቸውን የጠበቁና ደረጃ በደረጃ የቀረቡ ናቸው። በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ታላሚ የሆነው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጸሐፍ ለቃላት ትምህርት ተገቢ ትኩረት የሰጠ፣ በተቻለ መጠን ቃላትን በተለያዩ መንገዶች ተጠቅሞ ለማስተማር የሞከረ፣ ይዘቶቹ ተከታታይና ተዋረዳዊ ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ መሆናቸውን መረዳት የተቻለ ቢሆንም ይዘቶቹ የቴክኒክ ችግሮች ያሉባቸው መሆናቸውን በጥናቱ የተደረሰባቸው ውጤቶች ይጠቁማሉ።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

በመማር ማስተማር ሂደት፣ በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ በሚደረጉ መስተጋብሮች ተግባቦት የቀለጠፈና የዳበረ ይሆን ዘንድ የቃላት ሚና የጎላ እንደሆነ ድርሳናት ይመሰክራሉ ። እንደ Harmer (1993:154) ገለጻ፣ ተማሪዎች የቃላት እውቀታቸውን ለማዳበር የቃላት ትምህርት ይዘቶች በተገቢው ሁኔታ ሊማሩ ይገባል። ይሁን እንጂ ለብዙ አመታት ለቃላት ትምህርት ይሰጥ የነበረው ትኩረት በጣም ዝቅተኛ ነበር። ቃላትን ይጠቀሙባቸው የነበረው ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን (ማድመጥን፣መናገርን፣መፃፍንና ማንበብን) ለማስተማር እንጂ ቃላትን ለማስተማር ታስቦ አልነበረም። ይህም ለቃላት ትምህርት ይሰጥ የነበረው ትኩረት በጣም ዝቅተኛ እንደነበር ያስረዳል። እንዲሁም Richards and Rodgers (1986:94) እንደጠቀሙት፣ የቃላት ትምህርት ለበርካታ አመታት ትኩረት ተነፍጎት ይቆይ እንጂ ቀስ በቀስ ግን ቃላትን የማስተማር አስፈላጊነት እየታመነበት በመምጣቱ የራሱ የሆኑ አላማዎችና የተለያዩ የማስተማርያ ስነ ዘዴዎች ተነድፈውለት በአግባቡ መቅረብ እንደጀመረ ገልፀዋል።

ለቃላት ትምህርት ትኩረት እንዲያገኝ በርካታ የስነልሳን ምሁራን ጥረት አድርገዋል። ለምሳሌ Wilkins (1972፣111) "አንድ ሰው ያለ ሰዋስው በጣም ጥቂት መልእክት ሊያስተላልፍ ይችላል። ነገር ግን ያለ ቃላት ምንም መልእክት ሊያስተላልፍ አይችልም" በማለት ቃላት የቋንቋ ዋነኛ አካላት እንደሆኑና በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ከሰዋስው ይልቅ ቃላት ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ገለጸዋል። እንዲሁም ጌታቸው (1994) እንደሚያስረዱት፣ በትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላት አቀራረባቸው በመማርያ መጻሕፍት ዝግጅት የሚወሰን መሆኑንና የሚዘጋጁት መማርያ መፃህፍትም ተማሪዎች ቃላትን በራሳቸው መንገድ እንዲማሩ ለማድረግ የሚያስችሉ መሆን ይገባቸዋል። ስለዚህ ቃላት እንዴት ባለ አኳኋን ተደራጅተው ይቅረቡ? እና ምን አይነት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ይካተቱ? ለሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች አስቀድመን መልስ መስጠት አለብን። በመሆኑም መማርያ መጻሕፍቱ ተማሪውን ከቋንቋው፣ ተማሪውን ከተማሪው፣ ተማሪውን

ከማኅበረሰቡ፣ ተማሪውን ከመምህሩ ወዘተ. ጋር ማገናኘት የሚችሉና ተማሪዎቹን ለፈጠራ ስራ የሚጋብዙ ሊሆኑ ይገባል።

ለቋንቋ ማስተማርያነት ታስበው የሚዘጋጁ መማርያ መጻሕፍት የታላሚውን ቋንቋ ክሂሎች ለማዳበር የሚረዱ ይዘቶችን አቀናብረው የያዙና የቋንቋውን ሥነልሳናዊ እና ሥነትምህርታዊ ሁኔታዎችን ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባል። ሥነ-ልሳናዊ ይዘቶች ስንል በታላሚው ቋንቋ ላይ ያሉትን ፣ድምፆች፣ ቃላት፣ አረፍተነገሮች፣ ወዘተ ይመለከታል። ይህም አንድ ድምፅ ከሌላ ድምፅ ጋር ሲቀናጅ ምን አይነት ባህሪ እንደሚያሳይ፣ አንድ ቃል በዓረፍተነገር ውስጥ ያለውን አገባብና አገልግሎት፣ ምን እንደሚመስል እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ይመለከታል። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ አንዱ ለሌላኛው መሰረት ናቸው። ለምሳሌ ለኢ-አፍፈት ተማሪዎች ድምፆችን ሳናስተምር ቃላትን ማስተማር አንችልም። እንዲሁም ቃላትን ሳናስተምር አረፍተ ነገርን ማስተማር አይቻልም። ስለዚህ ስነ-ልሳናዊ ይዘት ከምን ተነስተን ምን እንደምናስተምርና ምን ላይ ማተኮር እንዳለብን ለመወሰን ይረዳናል። ሥነ ትምህርታዊ ይዘት ስንል ደግሞ ተማሪው ቀድሞ ምን ተምሯል?፣ ምን አይነት ይዘት ይፈልጋል? ፣ በቋንቋው ምን መጠቀም ይፈልጋል? ፣ ይዘቶች እንዴት መቅረብ አለባቸው? እና የመሳሰሉት ጉዳዮችን ይመለከታል። ስለዚህ የቋንቋ መማርያ መጻሕፍት ሲዘጋጁ ስነልሳናዊና ስነትምህርታዊ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው (Dubin and Olishtain 1992፣45)።

ከዚህ የምንረዳው ስነልሳናዊና ስነ ትምህርታዊ ግንዛቤዎች ግምት ውስጥ አስገብተው የተዘጋጁ የቋንቋ መማርያ መፃሕፍት የመማር ማስተማር ሂደቱ የተሳካ ከማድረግ አንፃር ጉልህ ድርሻ ያላቸው መሆኑን ነው። በዚህ ሁኔታ የተዘጋጁ መማርያ መጻሕፍትም በውስጣቸው የተለያዩ ይዘቶችን አካተው ይዘዋል። ከነዚህ ይዘቶች መካከል አንዱ ቃላትን የሚመለከት ይዘት ነው። በመሆኑም ኣንድ ተማሪ ሃሳቡን በፅሁፍም ሆነ በንግግር ለመግለጽ የቃላት ዕውቀት ሊኖረው ይገባል። እንዲሁም Batstone (1994 b :231) እንደገለፁት፣ ቃላት በልሳን ለሚከናወን ተግባቦት አስኳል ናቸው። በጥናት እንደተረጋገጠው በቋንቋ ለመዳ ሂደት ከስነ አገባብ እውቀት በፊት በቅድሚያ የሚዳብረው የቃላት እውቀት ነው። በመሆኑም ለቋንቋ ትምህርት መሰረቱ የቃላት ትምህርት መሆን እንዳለበት መረዳት ይቻላል።

ግምገማ የቋንቋ ትምህርት መርሀ ግብር አካል ነው። በመሆኑም ተከታታይ ግምገማዎችን በማካሄድ የግምገማ ውጤቱን ተመርኩዞ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት የቋንቋ ትምህርት ደካማ ጎኖችን ለማስተካከልና የትምህርቱን ጥራት ለመጠበቅ ያስችላል:: ስለዚህ በየጊዜው የሚታተሙ የቋንቋ መማርያ መጻሕፍት የሚፈልገውን አላማ ከግብ ለማድረስ እንዲያስችሉ ከተፈለገ የይዘት አመራረጣቸወን ፣ አቀራረባቸውንና አደረጃጀታችውን መገምገም ያስፈልጋል:: የግምገማ ውጤት መሰረት ተደርጎም የመማርያ መጻሕፍቱ የትምህርት አደረጃጀትና አቀራረብ ለማሻሻል ካስፈለገም ለመለወጥ የሚያበረክተው ኣስተዋፅኦ ትልቅ ነው (Elley 1989፣285)።

አሁን ባለው የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የአንደኛ ደረጃ መማርያ መሃህፍት የሚዘጋጁት በክልሎች ነው:: በክልሎች ከሚዘጋጁ መማርያ መጻሕፍት መካከል አንዱ በ1991ዓ.ም የተዘጋጀው የትግራይ ክልል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ነው:: በመሆኑም አጥኚው ጥናቱን ለማቅረብ ያነሳሱት ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው:: አንደኛ ምንም እንኳ የቃላት ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ የተወሰኑ ስራዎች ቢሰሩም በትግራይ የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማርያ መፅሃፍ በተመለከተ የተሰሩ ጥናቶች አጥኚው ባደረገው ዳሰሳ ባለማግኘቱ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ነው።

ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚዘጋጁ መማሪያ መፃሕፍት በአደረጃጀታቸውም ሆነ በአቀራረባቸው ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልጉ ናቸው። በተለይ በ8ኛ ክፍል ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የቃላት እውቀትም ሆነ አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታቸው የዳበረ ሊሆን ይገባል። ምክንያቱም ቀጣዩ የክፍል ደረጃ (2ኛ ደረጃ) ለአፍፊትና ለኢ-አፍፊት ተማሪዎች ለጋራ ለተዘጋጁ መጻሕፍት እኩል ስለሚጋለጡ ነው። ከዚህ አንፃር በተተኳሪ መጽሐፉ ውስጥ ለቃላት ፍቺ አቀራረብ የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት የሚያዳብር ይሆን? የሚለው ጥያቄ ሁለተኛው አነሳሽ ምክንያት ነው። እንዲሁም መጽሐፉ ውስጥ ለትምህርት የተመረጡ ቃላት የዘርፉ ምሁራን በጠቆሟቸው የቃላት መምረጫ፣ማደራጃና ማቅረቢያ መንገዶች በመጠቀም በመጽሐፉ ቀርበው ይሆን? የሚለውም ጥያቄ ሌላው አነሳሽ ምክንያት ነው።

## 1.2 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሃፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መገምገም ነው:: ከዚህ ግብ መድረስ እንዲቻልም ለሚከተሉት ዝርዝር ጥያቄዎች ምላሽ በማፈላለግ ላይ ትኩረት ይደረጋል::

1. ተተኳሪ መፅሃፉ የቃላት ትምህርት ይዘቶችን ለመወሰን ተገቢ መስፈርቶች መጠቀሙንና አለመጠቀሙን
2. መፅሃፉ የቃላት ትምህርት ይዘቶችን ሲያደራጅ ለቃላት ትምህርት አደረጃጀት መሰረት የሆኑ መስፈርቶችን ባገናዘበ መንገድ ያደራጀ መሆኑንና አለመሆኑን
3. በመጽሐፉ ውስጥ ተገቢ የሆኑት የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ብልሃቶች አገልግሎት ላይ መዋላቸውንና አለመዋላቸውን

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

በቋንቋ መማርያ መፅሃፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብን ገንቢነት ባለው ሁኔታ ይገመግማል። ከዚያም በግምገማው የሚገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ ጠንካራ ጎኑን ይዞ ለመቀጠል ወይም ደካማ ጎኑን ለማረም ያስችላል። እንዲሁም የቃላትን የማስተማርያ ስልቶች በማሳደግ የመማር ማስተማር ሂደቱ የተቃና እንዲሆን ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል:: በመሆኑም ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት ተብሎ ይታመናል::

1. በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀት እና አቀራረብ ምን መምሰል እንደሚገባቸው ለቋንቋ መማሪያ መፃህፍ አዘጋጆች ፍንጭ ይሰጣል፣
2. የሁለተኛ ቋንቋ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥና አቀራረብ ምን መምሰል እንዳለበት ወደፊት ለሚድረግ ማሻሻያ ጠቃሚ ሃሳቦችን ለአዘጋጆችና ለመምህራን ይጠቅማል፣

3. ወደ ፊት በዚህ መስክ ለሚካሄዱ ጥናቶች መነሻ የሚሆን ሃሳብ ይሰጣል ተብሎ ይገመታል።

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት አፋቸውን በትግርኛ ቋንቋ ለፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ መማርያ መፅሃፍ ውስጥ የቃላት ይዘት አቀራረብ አጠቃላይ ገፅታ ምን እንደሚመስል ትኩረት ያደርጋል። በመፅሃፉ የቀረቡ ሌሎች ክሂሎች፣ ስነልሳንና ስነ-ፅሁፍ ላይ ያተኮሩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብን አይመለከትም። እንዲሁም በትግርኛ አፋቸውን ለፈቱ ተማሪዎች በአሁኑ ወቅት ግልጋሎት እየሰጠ ካለው በፊት አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የተዘጋጁ መጻሕፍትንም ከግምት ውስጥ አያስገባም። ከተጠቀሰው ቋንቋ ውጪና በአማርኛ አፋቸውን ለፈቱ ተማሪዎች የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትም ከጥናቱ እይታ ውጪ ናቸው።በቃላት ትምህርት አሰጣጥ የመምህር ተማሪ መስተጋብር፣ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የመምህራን የቃላት ትምህርት አተገባበር ከዚህ ጥናት ትኩረት ውጪ ናቸው። እንዲሁም የትምህርት መሳርያዎች ማለትም መርሃ ትምህርቶች፣ የመምህሩ መመሪያዎችና የመማርያ መፅሃፍት ተያያዥነት ከጥናቱ ትኩረት ውጭ ናቸው።

# ምእራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

## 2.1 የቃላት ምንነት

የቃላትን ምንነት በተመለከተ በርካታ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎች ሰጥተዋል። ከተሰጡት ብያኔዎች መካከል ለአብነት ያክል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል። ቃላት ትርጉም ያላቸውና ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ የቋንቋ አሃዶች ናቸው። ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ስንል ነጠላ ቃላት፣ በተለያየ የእርባታና የምስረታ ምእላዶች የረቡና የተመሰረቱ ቃላት፣ ጥምር ቃላት፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮችና የተለመዱ አገላለፆች የያዙ ቃላት ማለታችን ነው (Mccarthy 1990:3)። እንደ ባየ (2000፣72) ገለጻ፣ ድምፆች በራሳቸው ትርጉም አልባ እንደሆኑ፣ እነዚህ ፍቺ አልባ ድምፆች ስርአት ባለው መንገድ ተቀናጅተው የሚፈጥሩት ፍቺ አዘል ምእላድ ነው። እንዲሁም Ur (1996:60) እንደጠቆሙት ቃል ከአንድ በላይ የሆኑ ድምጾች በሥርዓት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት ትርጉም ያለው የንግግር ድምፆች ስብስብ ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት ምሁራን በተጨማሪ በቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የተዘጋጀው አዲሱ የአማርኛ መዝገበ ቃላት(1993፣193) ቃል አንድ ፅንሰ ሐሳብ በመወከል በድምፅ የተነገረ ወይም በጽሑፍ የሰፈረ የድምጽ ምልክቶች ቅንብርና አነስተኛ የአረፍተነገር ክፍል እንደሆነ ያስረዳል።

ባጠቃላይ ቃልን በተመለከተ የተሰጡት ብያኔዎች ስንመለከት አንዱ ምሁር ያነሳቸው ነጥቦች በሌላ ምሁር ሲነሱ ታይተዋል። ለምሳሌ ትርጉም አልባ ድምጾች የአንድን ቋንቋ መዋቅራዊ ስርአት ተከትለው ሲሰደሩ ትርጉም አዘል የሆነ ቃል ይመሰርታሉ። እንዲሁም እነዚህ ትርጉም አዘል ቃላት በተለያዩ የእርባታና የምስረታ ቅጥያ ምእላዶች የተመሰረቱና የረቡ ቃላት፣ በጥመራ የተመሰረቱ ቃላት፣ እንዲሁም የተለመዱና ውሱን አገላለጾች ናቸው ማለት ይቻላል።

## 2.2 የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ቃላት ወሳኝ ሚና አላቸው። በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ለቃላት ትኩረት መስጠት እንዳለብን ድርሳናት ይጠቁማሉ። እንደ Celce Murcia (1991፡277) ገለጻ፣ የአንድ ቋንቋ መሰረቱ ቃላት ናቸው። እነዚህ ቃላትም በቋንቋ ውስጥ ለሚገኙ ጽንሰ ሃሳቦች መገለጫ ሆነው ያገለግላሉ። በመሆኑም ቃላት በቋንቋ ውስጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። Harmer (1993:153) እንደጠቆሙት፣ የቋንቋ መዋቅር የቋንቋውን አፅም ሲገነባ ቃላት ደግሞ አስፈላጊውን የቋንቋውን ስጋና ነፍስ ይፈጥራሉ። ይህም ቃላት የቋንቋ መገንበያ ጡብ በመሆን ያገለግላሉ። በመሆኑም ቃላት የተግባቦት መሰረት ናቸው።

ከነዚህ ምሁራን ገለጻ መረዳት የሚቻለው ቋንቋ የመግባብያ መሳሪያ መሆኑ እና በቋንቋ ውስጥም የቃላት ሚና ወሳኝ መሆኑን ነው። Pikulski እና Templeton (2004) እንደጠቆሙት፣ ቃላት እለት በእለት በምናደርገው አጠቃላይ መስተጋብር ማለትም ሐሳብ መለዋወጥን፣ መልእክት ማስተላለፍን፣ ጥያቄ ማቅረብንና የመሳሰሉት ነገሮች ለማሳካት የምንጠቀምባቸው ሁለገብ የቋንቋ መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው። በመሆኑም በመናገር፣ በማዳመጥ፣ በማንበብ እና በመጻፍ ለመግባባት ቃላት ቁልፍ ሚና አላቸው።

ተማሪዎች በቋንቋው የሚፈጥሩት ተግባቦት የጠራና የቀለጠፈ ይሆን ዘንድ ቃላት ቁልፍ ሚና እንዳላቸው በተለያዩ ምሁራን ከተሰጡት አስተያየቶች ለመረዳት ይቻላል። በመሆኑም ቃላትን ትኩረት ሰጥቶ በመደበኛው የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ማስተማር ያስፈለገው ተማሪዎች በቂ የቃላት ክምችትና እውቀት ኖሯቸው ቋንቋውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ለማድረግ ነው Pikulski እና Templeton (2004):: እዚህ ጋር በተያያዘ Wallace (1982:27) በቋንቋ ትምህርት ቃላት ያላቸው ቁልፍ ሚና እንደሚከተለው ዘርዝረዋል።

- በንግግር ወቅት የቃላትን ትክክለኛ ቅላጼ መጠቀም ያስችላቸዋል።
- የቃላትን እማርያዊና ፍካርያዊ ፍቺ እንዲገነዘቡ ያግዛቸዋል።
- ቃላትን ከተገቢው ቁስና ጽንሰሃሳብ ጋር ማዛመድ እንዲችሉ ያግዛቸዋል።

- ቃላትን በተገቢው ሰዋስዋዊ ቅርጽ እንዲጠቀሙባቸው ይረዳቸዋል።
- የቃላትን ትክክለኛ ዘይቤያዊ አጠቃቀም እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል።
- የቃላትን የንግግር ወይም የጽሕፈት ቅርጽ ለመለየት ያስችላቸዋል።
- የቃላት ተገቢውን የመደበኛነት ደረጃ ጠብቀው እንዲጠቀሙ ይረዳቸዋል።

ከላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች መረዳት የሚቻለው የቃላትን ትርጉም ከማወቅ ባሻገር የቃላት እውቀት አስፈላጊ መሆኑንና ቃላት ሌሎች የቋንቋ ዘርፎችን ለማቀላጠፍ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ መሆኑን ነው። እንደ Richards እና Rogers(2001) አገላለጽ፣ በቋንቋ ትምህርት ለተግባቦት እንደመሰረት ድንጋይ የሚቆጠሩት የሰዋስው ይዘቶች ሳይሆኑ ቃላት ናቸው። በመዋቅር ውስጥ የትኛው ነው ትክክለኛ ሰዋስው? ወይም የትኛው ነው ትክክል ያልሆነ ሰዋስው? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ የሚወስኑት ቃላት ናቸው። Lewis (1993:1) ስለ ቃላት አስፈላጊነት ሲያብራሩ፣ ከሰዋስው ይልቅ ቃላት በቅድሚያ አስፈላጊ ናቸው። ምክንያቱም ስነ አገባብ ቃላትን አገልግሎት በሚሰጡበት ሁኔታ ለማዋቀር የሚያገለግል ነው። ይህ ተጠይቃዊ ግንኙነት የሚያሳየን ቃላት ከሰዋስው በተሻለ ሁኔታ አስፈላጊ መሆናቸውን ነው።

Pikulski እና Tampleton (2004፣36) እንደጠቆሙት፣ ተማሪዎች በዚህ አለም ከሚገኙ የለውጥ ተዋናዮች ረድፍ ለመሰለፍ ተገቢ የቃላት እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች በዚህ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ውስብስብነት በሞላበት አለም የሚኖራቸው አቅም የሚወሰነው በአላቸው የቋንቋ ችሎታና የቃላት እውቀት ነው። በተጨማሪም Pikulski እና Templeton, (2004፣49) አንድ ሰው ለመናገርና ለመጻፍ ተገቢ የሆኑ ቃላት ከመረጠ፣የቃላት ግዝፈት ከተረዳ፣ የቃላት ፍች ስፋትና ጥበት ካወቀ እና መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችል እውቀት ካለው ተገቢ፣ የሆነ የቃላት እውቀት አለው ማለት እንደሚቻል ገልፀዋል።

Ur(1996:60-9) ቃላትን ማስተማር ከቃላት በላይ እንደሆነ በተመሳሳይ መልኩ ገልጸዋል። በገለጻቸው ላይ በተጨማሪ ያከሉት ከቃል በላይ የሆኑ ነገር ግን የቃልን ያህል ፍች የያዙ ቃላት እንዳሉ ነው። ይኸውም አስር ቃላት ለማስተማር በአንድ ምንባብ ውስጥ ከ100 ቃላት በላይ ልንጠቀም እንችላለን። በመሆኑም ቃላትን በቃላት ማስተማር ይቻላል። ለምሳሌ፡- ቡና ቤት፣ ቤተክርስቲያን፣ ኳስ ሜዳ እና የመሳሰሉት ጥንድ ወይም

ከዚያ በላይ ሆነው ስለ አንድ ነጠላ ሀሳብ የሚገልጹ በርካታ ቃላት ፣ እንዲሁም ከአንድ በላይ ፍቺ ያላቸው ቃላት ለምሳሌ ገና፣ ሳለ፣ ቀጠፈና ወዘተ. ማስተማር ይቻላል።

እንደ Gairns እና Redman (1986፣16) አገላለጽ የቃላት ትምህርት በርካታ ጉዳዮች የያዘ ነው። ከእነዚህ መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፣

- የአንድ ቃል የተለያዩ ግን ተቀራራቢ የሆኑ ፍችዎች መስጠት፣
- በተመሳሳይ ቃላት መካከል ያለውን ልዩነት ማስተማር፣
- የቃላት እማርያዊና ፋካርያዊ ፍች መለየትና መተርጎም፣
- ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ ያላቸውን ቃላት መለየት፣
- ቃላት በቅጥያ አማካኝነት የተለያየ ቅርጽ የሚይዙበትን ሁኔታ ማወቅ፣

ከእዚህ ጋር በተያያዘም Ur(1996:62-3) እና Harmer (1996፣161-2) ቃላትን ለማስተማር የሚያስችሉ የሚከተሉትን ስልቶች ጠቁመዋል።

1. በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ቃላት በማቅረብ፣
2. አዳዲስ ቃላት በተለያየ ስልት ማቅረብ ለምሳሌ ፦
   - የመዝገበ ቃላት ፍቺ በመስጠት፣
   - ጥልቅ ገለጻ በመስጠት፣
   - ተመሳሳይና ገላጭ ስዕሎች በመጠቀም፣
   - ሰርቶ በማሳየት (በተግባር፣ በመኮረጅ)
   - ቃሉ ከተገኘበት ታሪክ ወይም ይዘታዊ ገለፃ በመጠቀም ወዘተ.
3. ትግበራና ንጽጽር (Application and Comparision)
4. ውይይት ( discussion) ወዘተ. በመከተል።

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት የሚቻለው የቃላት ትምህርት የሚያካትታቸው ጉዳዮች የተለያዩ መሆናቸውን ነው። ይህም የተወሰኑ ምሁራን ለምሳሌ Ur(1991) እና Harmer (1996) ጠቅለል አድርገው ሲያቀርቡ Gairns እና Redman (1986)

ደግሞ ዘርዘር አድርገው ማቅረባቸውን ለመመልከት ችለናል። ይሁን እንጂ ምሁራኑ በመሰረተ ሃሳብ ደረጃ ተመሳሳይ ጉዳዮች እንዳነሱ ለመረዳት ይቻላል።

## 2.3 የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ቃላት በይዘታቸውም ይሁን በቅርጻቸው የተማሪዎች አቅም፣ ባህላዊና ማህበራዊ ዳራ ያገናዘቡ መሆን አለባቸው። በተለይ ለሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ቃላት በዘፈቀደ ሳይሆን በጥንቃቄ መመረጥ እንዳለባቸው የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ። Sinclear እና Renouf(1988፣148) እንደጠቆሙት በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ስለሚካተቱ የቃላት ትምህረት ሲነሳ፣ ለተማሪዎች ባላቸው ጠቀሜታ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቃላት እንዴት ይመረጡ? የሚለው አብይ ጥያቄ ነው። እንደ Pikulski እና Templeton (2004፣61-62) አገላለጽ፣ የቃላት ትምህርት ለእለት ተእለት መግባቢያነት በሚያገለግሉ ቃላት መጀመር ያስፈልጋል። ይህም ቀስ በቀስ የቃላትን የአገልግሎት ደረጃ እና ተገቢነት ተከትሎ ለማስተማር ያግዛል።

ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላት ስንመርጥ የተለያዩ መምረጫ መስፈርቶችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል። ለምሳሌ፡- የቃላትን ድግግሞሽ መጠን (Frequency)፣ የተማሪውን ፍላጎት ፣ ባህላዊ ተላውጦን (Cultural factors) እና የቃላቱን አስፈላጊነት (Expediency) ከግምት በማስገባት ተፈላጊዎቹን ቃላት መምረጥ ይገባል (Gairms እና Redman 1986, 57-64)። እንዲሁም Harmer (1991:154-156) ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ሽፋን እና የቃላት ረቂቅነትና ጉልህነት ከግምት ማስገባት እንደሚያስፈልግ ይጠቁማሉ። በዚሁ መሰረት ጉልህ ጽንሰ ሀሳብ የሚወክሉ ቃላት በቀላሉ ከሚወክሉት ነባራዊ ነገር ጋር ስለሚያያዙ ለመገንዘብ የቀለሉ ሲሆኑ ረቂቅ ፅንሰ ሃሳብን የሚወክሉ ደግሞ በአንፃራዊነት ለመረዳት እንደሚከብዱ ይታመናል። ስለዚህ በትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላት ሲመረጡ ውክልናቸው ለረቂቅ ወይም ለጉልህ ጽንሰ ሃሳብ ሆነው ከተማሪው እድሜና የትምህርት ደረጃ አንፃር የተገናዘቡ ሊሆኑ የገባል።

McCarthy (1990:79-90) ከተጠቀሱት በተለየ ተሰተማሪነትን (learnability) በመጨመር የምርጫ መስፈርቶች አስቀምጠዋል። በመሆኑም በተለያዩ ምሁራን ከቀረቡ መስፈርቶች መካከል ዋና ዋናዎቹን ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን።

### 2.3.1 የቃላት ድግግሞሽ

Harmer (1993:154) እንደጠቆሙት፣ የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ አባላት በተግባቦት ሂደት አዘውትረው የሚጠቀሙት ቃላትን ነው። እነ Biber et.al.(1998:53) በበኩላቸው፣ ድግግሞሽ በውህድ አሃድ ስብስቦች ላይ ያተኮረ የቃላት አጠቃቀም ጥናትን መሰረት በማድረግ በጣም ተደጋግመው የተከሰቱ ቃላትን መለየት የሚቻልበት የመምረጫ ስልት ነው። Nunan(1991:118)፣ በዕለት ተእለት ተግባቦት ሂደት የሚያገለግሉ ተዘውታሪ ቃላትን ለይቶ ማስተማር ተማሪዎችን በቋንቋ ለመጠቀም የሚያስችል ውጤታማ የማስተማር ስልት እንደሆነ ያስረዳሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ McCarthy (1990:66) ተዘውታሪ ቃላት ለማንኛውም ቋንቋ እጅግ በጣም አስፈላጊ ናቸው። ስለሆነም የተማሪዎችን የተግባቦት አቅም ለማሳደግ ተዘውታሪ ቃላትን አስቀድሞ ማስተማር ጠቃሚ ነው በማለት ገልጸዋል።

እንደ McCarten (2007:4) ገለጻ፣ ለቋንቋ ማስተማርያነት የሚቀርቡ ቃላት ተዘውታሪ ቃላት ሊሆኑ ይገባል። ተዘውታሪ ቃላት መርጠ ቅደም ተከተላቸውን ለመወሰን በእለት ተእለት በሚደረግ ተግባቦት ያላቸውን የድግግሞሽ መጠን(Frequency) ዝርዝር (Word list) አዘጋጅቶ መወሰን ይቻላል። ለምሳሌ እንደ የአመጋገብ ስርዓት፣ቀለምን የሚለዩ ቃላት፣ የአለባበስ ስርአት፣ የጥያቄና መልስ ሂደት የሚያወሱ ቃላት ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን ዘይቤን የሚገልጹ ቃላት ግን በተማሪው በእለት ተእለት ክንዋኔዎች ብዙም ስለማይደጋገሙ በመጨረሻ ቢቀርቡ የተሻለ ነው። በተጨማሪ McCarten (2007: 5-6) የአሃድ ስብስብ ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላትን በመምረጥ ረገድ የትኞቹ ቃላት ወይም የተለመዱ አገላለጾች ተዘውታሪ እንደሆኑ፣ የንግግርና የጽሑፍ ቃላትን ለመለየት፣ የቃላትን አውዳዊ አጠቃቀምና የጠበቀ ቁርኝት ያላቸው ቃላት ለመለየት ያስችላል።

ከMcCarten ገለጻ መረዳት የሚቻለው ለትምህርትነት የሚያገለግሉ ቃላት ምርጫ ሲካሄድ መታየት ያለባቸው ጉዳዮች ያሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ መረጣው የሚካሄድበት ውሁድ አሃድ አንዱ ነው። ይዘቱ በተወሰነ ሙያ ላይ የሚያተኩር ከሆነ በድግግሞሽ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት የተለመዱ አገላለጾችና ሙያን የሚገልጹ ቃላት ብቻ ይሆናሉ። እንዲሁም የአሃድ ስብስብ ለትምህርትነት ሊቀርቡ የሚችሉ ቃላትና ቃላዊ ሃረጋት ለመለየት ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑ መረዳት ይቻላል።

ተዘውታሪ ቃላት ለመለየት ጥረት በሚደረግበት ጊዜ በድግግሞሽ ዝርዝር ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎችን መቆጣጠር አስፈላጊ ነው (Nunan 1991፣119 እና Gairns and Redman 1986፣ 68)። በመሆኑም በድግግሞሽ ቆጠራ ውጤት ላይ ተፅእኖ ከሚያሳድሩ ተላውጦዎች መሃል Gairns እና Redman (1986፣55-59) እና McCarthy (1990:66-88) የሚከተሉትን ነጥቦች ጠቁመዋል።

- የድግግሞሽ ቆጠራው የተካሄደበት የውህድ አሃድ ስብስብ መጠን፣የስብስቡ መጠን መብዛት ውጤቱን በማስተማመን አስተዋጽኦ ይኖረዋል።
- የውህድ አሃድ ስብስቡ አይነትና መጠን፣ ምንጩ ከጽሑፍ፣ ከንግግር ወይም ሁለቱም ያካተቱ ቢሆን ይመረጣል።
- ተቆጣሪው የውህድ አሃድ ስብስብ ያካተታቸው የውህድ አሃድ አይነቶች፣ ርእሰ ጉዳዮች፣ ዓይነት ልሳናት ወዘተ. ያካተተ መሆን አለበት። ይህ ስብስብ ሁሉንም የውሁድ አይቶች (አስረጅ፣ ገላጭ፣ ተራኪ፣ ወዘተ.) የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮችን፣ የተለያዩ ስርአተ አባባሎችን (የሀኪሞች፣የመምህራን፣የመሃንዲሶች ወዘተ.)፣ አጠቃሎ የያዘ ሆኖ መገኘቱን የሚመለከት ነው። ከሁሉም ዓይነት አጠቃሎ ካልያዘ በቆጠራው ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል።
- የውህድ ስብስቡ የተቀናበረበት የጊዜ ርዝማኔ፣ የውህድ አሃድ ስብስቡ የተጻፈበት ወይም የተነገረበት ጊዜ የራሱ ተጽእኖ ይኖረዋል። ለምሳሌ ከ60 አመት በፊት በተጻፉና በተነገሩ ውህድ አሃዶች ውስጥ በጣም ተደጋጋሚ ቃላት የነበሩ ዛሬ ተደጋጋሚነታቸው ሊቀንስ ይችላል። በቅርብ የተፈጠሩ እንደ ኮምፒዩተር፣ ቪድዮ ያሉ ቃላት ደግሞ ጨርሶ በውስጣቸው ላይገኙ ይችላሉ።
- ቆጠራው በጣም ተደጋጋሚ የሆኑ ቃላዊ ሀረጋትን ማጠቃለሉን ማረጋገጥ። እንዲሁም በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ውስጥ ቃላዊ ሃረጎች (ድርብ ቃላት፣ በቃላት ጥምረት የሚፈጠሩ ፈሊጦችና የተለመዱ አገላለፆች) በተደጋጋሚ መኖራቸውን ማስተዋል ያስፈልጋል። ስለዚህ ቆጠራው እነዚህንና ከአንድ ቃል ጋር አብረው የሚሰለፉ ቃላትን ድግግሞሽ የሚያሳይ ቢሆን የይዘት መረጣው ያስተማምናል።

በአጠቃላይ በተዘውታሪነታቸው የተለያዩ ቃላት እንዳይቀርቡ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች በርካታ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ቃላቱ ከታላሚው ቋንቋ ባህላዊ እሴት፣ ከመማሪያ ክፍሉ አካባቢ፣ ከተማሪዎች ተግባቦታዊ ፍላጎትና ቀደምት እውቀት ጋር

መስማማት ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ድግግሞሽ እንደቃላት መምረጫ መስፈርት በስራ ላይ ሲውል ከላይ የተዘረዘሩትን ተላውጦዎች ተቆጣጥሮ ተግባሩን በጥንቃቄ ማከናወን ያስፈልጋል McCarten (2007:4):: በተያያዘም Carter (1991:187) ድግግሞሽ የቃላት ትምህርት ይዘት መምረጫ አንዱ መስፈርት እንጂ የመጨረሻው አለመሆኑን መረዳት እንዳለብን አጥብቀው ይመክራሉ።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሌላው የሚነሳ ጉዳይ የስርጭት ሽፋን ነው። McCarthy (1990:66) እንደጠቆሙት፣ ለተማሪዎች ጠቃሚ ቃላት የሚባሉት በተለያዩ አሃዶች ውስጥ በመከሰት በጣም ተደጋጋሚ የሆኑት ሲሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ድግግሞሻቸው ሰፊ የስርጭት ሽፋን ያለው ከሆነ ነው። በመሆኑም አንድ ቃል ወይም ቃላዊ ሀረግ በተለያዩ አሃዶች ውስጥ በተደጋጋሚ ከተገኘ፣ ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ በትምህርት ይዘትነት ሊመረጥ ይገባዋል።

## 2.3.2 የተማሪዎች ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ መጣጣም

McCarthy (1990:69) እንደጠቆሙት፣ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ የተማሪውን እድሜ፣ የትምህርት ደረጃና የቀድሞውን እውቀት ያገናዘበ መሆን አለበት። እንዲሁም Allen (1983:108) የተማሪዎችን ፍላጎት የመተንበይ ተግባር ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ በመፈለግ ሊከናወን እንደሚችል ይታመናል። ጥያቄዎቹም ተማሪዎች በአካባቢያቸው ስላሉ ሰዎች፣ ስለነገሮችና ስለክስተቶች መናገር እንዲችሉ የትኞቹ ቃላት ያስፈልጓቸዋል? ሲማሩ በተደጋጋሚ ለሚያጋጥሟቸው ትእዛዞችና መመሪያዎች ምላሽ መስጠት እንዲችሉ የትኞቹ ቃላት ማወቅ ይኖርባቸዋል? በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚካሄድ የቋንቋ ልምምድ የትኞቹ ቃላት ያስፈልጓቸዋል? የተወሰነ አካዳሚያዊ ብቃታቸውን ለማሟላት የትኞቹ ቃላት ማውቅ ይጠበቅባቸዋል? እነዚህን ጥያቄዎች በመመለስ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የተማሪዎችን ፍላጎት በመተንበይ በቃላት መረጣው ለማካተት እንደሚቻል ይታመናል። በመሆኑም የሚመረጡት ቃላት የተማሪውን የቀድሞ እውቀት አገናዝበው አዳዲስ ነገሮችን ሊጨምሩለት የሚችሉ መሆን አለባቸው።

### 2.3.3 በቅርብ መገኘት

Gairns and Redman (1986: 61-62) እንደጠቆሙት ፣ ቃላት የመማር ማስተማሩን ሂደት ያግዛሉ ተብሎ ሲታመንባቸው በትምህርት ውስጥ ይካተታሉ ። ለምሳሌ ቴክኖሎጂ ጋር የተያያዙ፣ ሙያን የሚገልጹ ቃላትና ወቅታዊ ቃላት ሊሆኑ ይችላሉ። ከእዚህ ጋር በተያያዘም Wallace(1982:16)፣ የቃላት በቅርብ የመገኘት መስፈርት የሚመለከተው በተወሰኑ የመማር ሁኔታዎች ውስጥ ያልተለመዱ( በተደጋጋሚ በአገልግሎት ላይ ያልታዩ) ቃላት፣ እነዚህ ቃላትም የመማር ሂደቱን የሚገድቡ ሆነው ሲገኙ በይዘትነት የሚካተቱበትን ሁኔታ ነው። አንድ ቃል ሰፊ የአገልግሎት ሽፋንና ስርጭት ሳይኖረው ቋንቋን ለማስተማር በሚቀርብ ውህድ አሃድ ውስጥ የተለየ አስፈላጊነት ይዞ ሊከሰት ይችላል። በመሆኑም አንድ ቃል ሰፊ የስርጭትና የፍቺ ሽፋን ሳይኖረው ለቋንቋ ማስተማሪያነት በሚመረጥ ምንባብ/አሃድ ውስጥ በአጋጣሚ ኖረው የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚገድብ ሆኖ ሲገኝ ቃሉ ተመርጦ ለይዘትነት እንዲካተት ይደረጋል።

Richards(2001:15) እንደጠቆሙት አንዳንድ ቃላት ተዘውታሪ ሳይሆኑ ነገር ግን በአጋጣሚ ግልጋሎት ላይ ሲውሉ በርካታ ቃላት እንዲታሰቡ ያደርጋሉ። ለምሳሌ ትምህርት ቤት ስንል በውስጡ መምህር፣ ተማሪ፣ መማሪያ ክፍል፣ ወዘተ ይታሰቡናል። እንዲሁም እንስሳ ስንል በግ፣ ፍየል፣ አንበሳ ወዘተ. የመሳሰሉት ቃላት በአእምሮአችን ይከሰታሉ። ስለዚህ ነጠላ እሳቤ ካላቸው ቃላት ይልቅ በርካታ ቃላትን በውስጣቸው ሊሸከሙ የሚችሉ (ለምሳሌ፡- እንስሳት፣እፀዋት፣ መኪና ወዘተ) የመሳሰሉትን በቅድሚያ ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

### 2.3.4 ተስተማሪነት (Learn ability)

McCarthy (1990:86) እንደጠቆሙት፣ ቃላትን ለመማር አስቸጋሪ የሚያደርጉ በርካታ ምክንያቶች አሉ። ለምሳሌ ቃላት ውስብስብ ባህሪ ሲኖራቸውና ቃላቱ ከተማሪዎች ህይወትና የሕይወት ልምድ ሲርቁና ተማሪዎች የተለያዩ ቃላት በፍቺ ተመሳሳይ እንደሆኑ ሲያስቡ ቃላን ለመማር ይቸገራሉ።በመሆኑም በጣም ተደጋግመው በአገልግሎት የሚውሉ ቃላት የተስተማሪነት ደረጃቸው ከፍተኛ ሲሆን ከላይ እንደተጠቀሰው ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላት ከተማሪዎች የሕይወት ልምድ

የማይገናኙ ከሆኑና የቃላቶቹ አገባባዊ ባህሪ ውስብስብ ከሆነ የተስተማሪነት ደረጃቸው ዝቅተኛ ይሆናል።

ቃላት ለትምህርትነት ስናቀርብ በዋነኛነት የቃሉ ተስተማሪነት ማሰብ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ይህም ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላት ተስተማሪነታቸው ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ መሄድ ይኖርባቸዋል። የቃላት ትምህርት በዚህ ሁኔታ የሚቀርብ ከሆነ ተማሪው የቀረበለትን ትምህርት ላውቀው እችላለሁ የሚል ስሜት ሊፈጥርለት ስለሚችል የመማር ስሜትን ከመቀስቀስ አንጻር ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል። Richards (2001:5)። ስለዚህ በትምህርት ይዘትነት የሚቀርቡ ቃላት ከተስተማሪነት አንጻር ሲታይ ከተማሪዎች ሕይወት ጋር የተያያዙ፣ ለመማር የማያስቸግሩና የተነሳሽነት ስሜት የሚቀሰቅሱ ሊሆኑ ይገባል።

### 2.3.5 የፍቺ ሽፋን

Carter እና McCarthy (1988:10) እንደገለጹት፣ በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ቃላት ፍቺ ከማስተላለፍ ረገድ አንድ አይነት የፍቺ ይዘት የላቸውም ። አንዳንዶቹ ቃላት ሰፊ ፍቺ ሲኖራቸው ሌሎቹ ደግሞ ጠባብ ፍቺ ይኖራቸዋል። በርካታ ፍቺን መሸከም የሚችሉ ቃላት በተለያዩ አውዶች በስፋት ተገኝተው መልእክት ማስተላለፍ ሲችሉ ጠባብ ፍቺ ያላቸው ቃላት ደግሞ ሰፊ ፍቺ ባላቸው ቃላት ይተካሉ። በሌላ አነጋገር፣ ሰፊ ፍቺ ያላቸው ቃላት ጠባብ ፍቺ ያላቸውን ቃላት የመተካት ሚና ይጫወታሉ።

ከዚህ አንጻር አንዳንድ ቃላት ሰፊ ፍቺ ስላላቸው ሃሳብን አምቀው የመያዝ ችሎታ ሲኖራቸው አንዳንዶቹ ደግሞ ጠባብ ፍች ስላላቸው ሰፊ ፍቺ ባላቸው ቃላት ስር ይጠቃለላሉ። በመሆኑም ቃላት ከሚሰጡት ትርጉም አንጻር እማርያዊና ፉካርያዊ ፍቺ ይኖራቸዋል Wallace (1982:18-19)። ሰፊ ፍቺ ያላቸው ቃላት፣ ምስጢርን አምቆ የመያዝ፣ ለአድማጭ ወይንም ለአንባቢ የተለየ ትርጉም የመስጠት ጠባያቸው ፍካሪያዊ ትርጉም ሲሆን፣ ምንም ስውር ትርጉም ሳይኖረው ለአድማጭ ወይም ለአንባቢ ሁሉ የጋራ የሆነ ግልጽ ትርጉም የመስጠት ባህሪያቸው ደግሞ እማርያዊ ትርጉም ይባላል። እንዲህ ያለ ሁለት ፍቺ ያላቸው ቃላት የሚኖራቸው የአገልግሎት ሽፋን ሰፊ ነው።

## 2.4 የቃላት ትምህርት አደረጃጀት

ለቋንቋ ትምህርትነት ዓላማ የሚውሉ ቃላት በምርጫ መስፈርት መሰረት በጥንቃቄ መመረጥ እንዳለባቸው ከላይ ተመልክተናል። የተመረጡት ቃላት ደግሞ የተማሪዎችን ፍላጎት፣ አቅምና ዳራ መሰረት አድርገው መደራጀት ይኖርባቸዋል። በመሆኑም የተመረጡት ቃላት በመማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት ሂደት ውስጥ ተማሪዎች በእለት ተእለት ተግባሮታቸው ሊጠቀሙባቸው በሚያስችል መልክ መደራጀት አለባቸው።

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋ አሃዶች እድገታቸውን ጠብቀው በትምህርቱ ሊሸፈኑ ይገባል፤ይህም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የቋንቋ አሃዶች እድገት ባለው አካሄድ፣ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ እንዲማሩ በሚያስችላቸው ሁኔታ፣ የቃላት ትምህርት ማስታወስን የሚፈልግ መሆኑን ባገናዘበ መንገድ፣ በተወሰነ በጊዜ ርቀት በመደጋገምና በተለያዩ አውዶች ለመማር እድል በሚሰጥ መንገድ መቅረብ ይኖርባቸዋል። ከዚህም ሌላ ቃላት በቋንቋ ክንውኖች ውስጥ የድግግሞሽ መጠናቸውና እድገታቸው ጠብቀው መደራጀት አለባቸው (Nation 2006:6)። እንዲሁም Dubin and Olshtain (1986: 46-47) እንደገለጹት፣ አደረጃጀት የአዳዲስ ርእሰ ጉዳዮች (Topics)አቀራረብ፣ ክትትሎሽና መጠነ ርእይ ውሳኔዎች የሚመሰረቱት በስነ ትምህርታዊና በስነ-ልቦናዊ እሳቤዎች እንዲሁም በሚኖረው የመማርና ማስተማር ሂደት ላይ ይመሰረታል በማለት ያስረዳሉ።

በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ቃላት በሚያወሱት ርዕሰ ጉዳይ ማደራጀት የተለመደ ነው እንዲሁም ቃላትን የገሃዱ ዓለም ቡደና፣ቋንቋ ተኮር ቡደና እና ግላዊ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ቡደና አደራጅቶ ማቅረብ ይቻላል። ከዚህ አንጻር ቃላትን በተለያዩ አሃዶች ከፋፍሎ ለማቅረብ በሚያነሱት ርእሰ ጉዳይ (Topic) እና የቅርጽ መመሳሰል እንዲሁም በሚኖራቸው የፍቺ ዝምድና ማደራጀት ይቻላል(Mccarthy፣ 1990)። በመሆኑም ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላት በመልመጃ ለማዋቀር የቃላቱን የተለያዩ የፍቺ ይዘቶች፣ ስነ-ድምጻዊና ሰዋስዋዊ አወቃቀሮች መሰረት አድርጎ ማቀናጀት ይቻላል። ከዚህ አንጻር የማደራጃ መንገዶች ቀጥለን በዝርዝር እናያለን።

### 2.4.1 ቃላት በሚያወሱት ርእሰ ጉዳይ (Topic) ማደራጀት

በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ቃላት በሚያወሱ ርእሰ ጉዳይ መሰረት አደራጅቶ ማቅረብ ይቻላል። ለምሳሌ፡- ገበያ የሚለው ቃል ሲነገር፣ ቦርሳ፣ ልብስ ፣ ሰዓት፣ እህል፣ ብዙ ሰው ያለበት ቦታ ወዘተ. የሚሉ ቃላትና ሐረጋት ይታወሱናል። እንደ Grains እና Redman (1986:69) ገለጻ፣ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ስር ሊጠቃለሉ የሚችሉ ለአንድ ደረጃ የተመረጡ ቃላት የሚያገናኛቸውን ርዕሰ ጉዳይ በመግለጽ እንዲያገለግሉ ከተደረገ በኋላ፣ ቃላቱ በመልመጃ መልክ ለትምህርት የሚቀርቡበት አደረጃጀት ነው።

McCarthy (1990:91) እንደጠቆሙት፣ ቃላት በሚያነሱት ርእሰ ጉዳይ አደራጅቶ ማቅረብ የራሱ የሆነ ችግር አለው። ይኸውም ርእሰ ጉዳይን በተጨባጭ ለመለየት ማስቸገሩ፣ የትኛው ርእሰ ጉዳይ ለተማሪ ጠቃሚ መሆኑ፣ የርእሰ ጉዳዩ ምንነት ማወቅና የመሳሰሉት ጉዳዮች ከሚያጋጥሙን ችግሮች መካከል ምሳሌዎች ናቸው። ይሁን እንጂ አደራጅቶ የማቅረብ ችግር ቢኖርም ቃላትን አቧድኖ ማቅረብ ጠቃሚ ዘዴ መሆኑን ሊታወቅ ይገባል።

### 2.4.2 ቃላትን በፍቺ ማደራጀት

Carter እና Mccarthy (1988:19) እንደገለጹት፣ አንዳንድ ቃላት በርካታ የፍች አካባቢዎችን ታሳቢ ያደርጋሉ። አንዳንዶቹ የፍቺ አካባቢዎች ሰፊ( ለምሳሌ ፍልስፍና፣ ስሜቶችን ወዘተ) ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ የሚወክሉትን በቀጥታ ሊጠቁሙ የሚችሉ ጠባብ (ለምሳሌ፡- የዘር ሀረግ መግለጫ ቃላት፣ቀለማት፣ የአናጺ መገልገያ እቃዎች ወዘተ.) ናቸው።

ቃልን በመሚገባ ለመረዳት ተማሪዎች ማወቅ ያለባቸው ቃሉ የሚወክለውን ፍቺ ብቻ ሳይሆን ተዛማጅ ፍቺ ካላቸው ቃላት የሚለየውንም ጭምር ነው። ስለሆነም በፍቺያቸው መነሻነት ቃላት ሲደራጁ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። መጀመሪያ ቃላቱ የሚቀርቡበትን ተገቢ አውድ መፍጠር ይኖርብናል። ሁለተኛው ቃላትን ከአውዳቸው ፍቺያቸውን ለመገመት የሚያስችሉ የትንበያ ስልቶችን ከግምት አስገብተው የተማሪዎቹን የመገመት ብቃት ሊያሳድግ በሚችል አኳኋን ትምህርቱ ማደራጀት አለብን። ስለዚህ ይህንን ታሳቢ በማድረግ ቃላት ማደራጀት ከቻልን ተማሪዎች በተፈጠረላቸው ምቹ

ሁኔታ ተጠቅመው የቃላትን ፍቺ ከአውድ የመፍታት አቅም ያዳብራሉ (Gairns እና Redman 1986:69)።

### 2.4.3 ቃላትን በቅርጽ ማደራጀት

ቃላትን በትምህርትነት ለማደረጃት የሚረዳ ሌላው መንገድ የቃላት የቅርጽ ተመሳስሎ ነው። ተመሳሳይ ነገሮች በቀላሉ ሊታወሱን እንደሚችሉ ሁሉ ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸው ቃላትም አንድ ላይ ቢቀርቡ የትምህርት ሂደቱ ውጤት ሊኖረው እንደሚችል ይታመናል። እንደ Mccarthy (1990) እና Nattinger (1988) ገለጻ፣ ተመሳሳይ ቅጥያ የሚጨምሩ ቃላት አንድ ላይ መቅረባቸውና እነዚህኑ መገንዘብ መቻል በተመሳሳይ መንገድ ሌሎች ቃላትን የመመስረት ወይንም የማራባት ችሎታን ሊያዳብሩ ይችላሉ። በዚህም የተለያየ የቅጥያ አጨማመር ከሚታይበት የቃላት ትምህርት አቀራረብ የተሻለ ማወቅ መቻል በበኩሉ የቃላትን ቅርጽ ትክክለኛነት ጠብቆ የመጠቀም ችሎታ ባለቤት ሊያደርግ እንደሚችል ይታመናል። በመሆኑም ተመሳሳይ ቅጥያ የሚወስዱ ቃላት በትምህርትነት አንድ ላይ አደራጅቶ ማቅረብ ተመራጭ ነው።

ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው ተመሳሳይ ቅድመ/ድህረ አምድ ቅጥያ የሚጨምሩ ወይም በተመሳሳይ መንገድ የሚረቡ/የሚመሠረቱ ቃላት አንድ ላይ ቢቀርቡ በተሻለ ሁኔታ የቃላቱን አምዶችና ቅጥያዎች ለይቶ የመገንዘብ እድል ሊፈጥር የሚችል መሆኑን ነው። እንዲሁም በትምህርትነት የቀረበ የቃል አምድ ከአዲስ ቅጥያ ጋር ወይም ቀድሞ በትምህርትነት የቀረበ ቅጥያ ከእንግዳ አምድ ጋር ተቀናጅቶ ቢቀርብ ከቀረበበት አውድ እና ቀድሞ በትምህርትነት ቀርቦ ከተለመደ የቃል ቅርጽ በመነሳት የቃሉን ፍቺ ለመገመት እንደሚያስችል ለመረዳት ይቻላል።

## 2.5 የቃላት ትምህርት ማቅረብያ መንገዶች

አዳዲስ ቃላትን በመማሪያ መጻሕፍት አቅርቦ ማስተማር ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላት ተማሪው በእለት ተእለት ሕይወቱ ሊጠቀምባቸው የሚችል ሊሆኑ ይገባል። ይህን ለማድረግም ለትምህርትነት የሚመረጡ ቃላት የተማሪውን እድሜ፣ የትምህርት ደረጃ ፣ ባህል ወዘተ. ያገናዘቡ መሆን አለባቸው።

Blachowicz እና Fisher (2005:4) እንደጠቆሙት፣ የቃላት እውቀት የቃላትን ፍቺ ከማወቅ በላይ የዘለለ ውስብስብ ሂደት ነው። ይኸውም በመጀመሪያ ቃል የመማር ዝንባሌ (ፍላጎት) መኖርን፣ የቃሉን ትርጉም መገንዘብን፣ በትምህርት የተገኘውን አዲስ እውቀት ከቀድሞው ጋር አገናኝቶ መረዳትን ይጠይቃል። ለምሳሌ "ገባ" የሚለውን ቃል ፍቺ ለመረዳት "ከውጭ ወደ ውስጥ" የመግባት (የመንቀሳቀስ) ባህሪ ሊያሳየን ይችላል። እንዲሁም፣ እንቅስቃሴው፣ ድርጊት ፈጻሚው ድርጊቱ የተፈጸመበት ሁኔታ ድርጊቱ የተፈጸመበት ጊዜ ወዘተ. የመሳሰሉትን ነገሮች መረዳት እንችላለን። ከዚህ በዘለለም ቃሉ በምን አይነት አውድ ሊከሰት እንደሚችል፣ ከዚህ ሌላ ምን አይነት ፍቺ ሊኖረው እንደሚችል፣ ከሌሎች ቃሎች ጋር ያለው መዋቅራዊ ባህሪ፣ የቃሉ ሰዋሰዋዊ ባህሪ ወዘተ. ሁሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለዚህ ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላት እውናዊ አውድ መስረት አድርገው መቅረብ ይኖርባቸዋል።

ተማሪዎች አንድን የቃል አይነት ያለችግር እንዲገለገሉበትና ስለ ፍቺው በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከተፈለገ በተቻለ አቅም ቃሉ በተደጋጋሚ በተለያየ አውድ ውስጥ ሊያገኙት ይገባል(Cunningsworth 1995:59)። ለምሳሌ "ገባ" የሚለውን ቃል በተለያዩ አውዶች ማቅርብ ይቻላል። ይህም "ሃይሌ ወህኒ ገባ"፣ "ሐይሌ እቁብ ገባ፣ "ሀይሌ ገደል ገባ"፣ "ሐይሌ ኮሌጅ ገባ" ወዘተ. በመሳሰሉት አውዶች በማስገባት በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ ይቻላል። Seal (1991:301) እንደገለጹት፣ የቃላት ትምህርት አቀራረብ የተነጣጠለ ሳይሆን አንዱ ከንውን ቀጥሎ ካለው የተቆራኘና ደረጃ በደረጃ የተዋቀረ ሊሆን ይገባል። ይኸውም በመጀመሪያ አዳዲስ ቃላት ለተማሪዎች የሚቀርቡበት ሁኔታ ላይ ያተኩራል። በመቀጠል ተማሪዎች አዳዲሶቹን ቃላት መረዳታቸውን የሚረጋገጥበት ሂደት ይሆናል።

Scrivener(1998:74) እንደጠቆመው፣ በስርአት የተዋቀረ ትምህርት መስጠት፣ ተማሪዎች የአዲሱን ቃል አጠቃቀም የሚያለማምድ፣ የአዲሱን ቃል ማስታወስ የሚችሉበት መንገዶችን የሚጠቁም፣ የአዲሱን ቃል ፍቺ እንዲረዱና አጠቃቀሙን እንዲለዩ የሚያደርግ፣ የቃሉን ቅርጽ መመርመርና ተዋቃሪዎቹን ከነፍቺያቸው ለመለየት የሚያስችል እና አዲሱን ቃል ተገቢ በሆነበት አውድ ለመጠቀም የሚያስችል ስልት ነው። ከምሁሩ ገለጻ መረዳት የሚቻለው፣ አዳዲስ ቃላት በተማሪዎች አእምሮ እንዲሰርፁና

ከግንዛቤያቸው እንዲዋሃዱ፤ እንዲሁም ለአፍልቆት እንዲውሉ ከተፈለገ የሚቀርበው ትምህርት በስርአት ሊዋቀር ይገባል።

በአጠቃላይ የቃላት ትምህርት ለማስተማር የሚቀርቡ መልመጃዎች፣ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት የሚያነሳሱ፣ በራሳቸው ጥረት ቃሉን እንዲያውቁ የሚገፋፉና የተማሪ ተሳትፎን የሚያጎለብቱ ሆነው ከተዘጋጁ ቃላቱ አይረሴ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት ይቻላል። እንዲሁም መልመጃዎቹ በሳይንሳዊ መርህ መሰረት ከተደራጁ ተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜት እንዲኖራቸው ከማስቻላቸውም በላይ በመልመጃዎቹ አማካኝነት የተለያዩ የታላሚ ቋንቋ የአጠቃቀም ገጽታዎችን የመመርመር እድል ያገኛሉ። ስለዚህ በትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላት አይረሴ ለማድረግ የተለያዩ ሳይንሳዊ የአቀራረብ አማራጮችን መጠቀም አስፈላጊ ነው። በመሆኑም የተለያዩ ምሁራን የጠቆሟቸውን የቃላት ማቅረቢያ መንገዶች ዋና ዋና የሚባሉት ከዚህ በታች ቀጥለን እናያለን።

### 2.5.1 ቃላትን በዐውድ አስደግፎ ማቅረብ

አውድ ቃሉ በቁሙ ከሚሰጠው ትርጉም በተለየ ሁኔታ በሌሎች ከጉኑ በሚቆሙ ቃላት አማካኝነት ትርጉም የሚወስንበት ሁኔታን ይመለከታል። እንዲሁም አውዱ ንግግሩ የተነገረበትን ሁኔታ እና ንግግሩ የፈለቀበትን ስነልሳናዊ አካባቢ ያካትታል። ስለዚህ አውድ ስንል ሁኔታዊ አውድና ስነ ልሳናዊ አውድ በማለት በሁለት መንገድ ከፍሎ ማየት ይቻላል (Lewis 1993:8) እና(Ellis 1985:7)። አውድ ቋንቋ በጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ የሚያመቻች የመረጃ ጥንቅር ነው Harmmer (1991:57)። አውድ በአንድ የቀረበ ንግግር ወይም ጽሑፍ በአጠቃላይ ባህሪ ሊገለጽና ሊከፋፈል ይችላል። ለምሳሌ በአንድ ጽሑፍ ውስጥ እንደ ስነምእላዳዊ፣ ስነ አገባባዊና ዲስኩራዊ መረጃ ሊታሰብ የሚችል ነገር ነው። ይህ እሳቤ በቀረበው ጽሑፍ ወይም ንግግር ውስጥ አንባቢው ወይም አድማጩ ሊኖረው የሚገባ ዳራዊ እውቀት ምን ሊሆን እንደሚገባ ትኩረት ያደርጋል Nation እና Cody (1988: 101) ።

ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው የአንድ ቃል ፍቺ መወሰን የሚቻለው ቃሉ በቀረበበት አውድ ነው። ይህም አንድ ሰው ለአለቃውና ለጓደኛው በአንድ አይነት ቋንቋ

አይናገርም፤ እንዲሁም ሃዘን ቤትና ሰርግ ቤት ተመሳሳይ ቋንቋ አይጠቀምም። ስለዚህ ቃላት በሚነገሩበት አውድ ተከትለው እንደሚለዋወጡ መገንዘብ ይቻላል።

እንደ Lowson እና Hogben (1996,106) አገላለጽ፣ አውድ ለቃላት ትምህርት ትልቅ ድርሻ አለው። ይኸውም ቃላት ከስነልሳናዊም ሆነ ከስነልቦናዊ እይታ አንጻር ፍቺያቸው ግልጽ የሚሆነው በተገቢው አውድ ውስጥ ሲገቡ ነው። በተያያዘም River (1994:131) እንደጠቆሙት፣ አንድ ቃል በተናጠል ከማቅረብ ይልቅ ተማሪዎች በድርጊት እየተሳተፉ በሚማሩበት አውድ ውሰጥ ማቅረብ ትምህርቱን አይረሴ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር ጉልህ ድርሻ አለው። በመሆኑም የቃላት ትምህርት አቀራረብ ቃላት በገቡበት አውድ ውስጥ መገመት በሚያስችል መንገድ መሆን አለበት ።


Hunt እና Belgar (2002፣83) ተማሪዎች ራስ አገዝና ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ ቃላትን በተገቢው አውድ አቅርቦ ማለማመድ ተገቢ ነው። በሚቀርቡት አውድ ውስጥ ከቀረቡ ቃላት መካከል ከሃያዎቹ አስራዘጠኙ የሚታወቁ መሆን አለባቸው። ይህም የቃላትን ፍቺ ከአገባባቸው በመገመት በቀላሉ ለመገንዘብ ያስችላቸዋል። ይህ ካልሆነ ግን ቃላትን ከአገባባቸው መረዳት ውስብስብና አስቸጋሪ ይሆናል። በመሆኑም አንድ ተማሪ አንድን ቃል ከአገባቡ ለመረዳት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይኖርበታል።

- አውዱን በሚገባ መረዳት፣
- የቃል ክፍሉ መለየት፣
- በአውዱ ውስጥ ያሉትን ፍንጮች መፈተሽና መገንዘብ፣
- የቃሉን ትርጉም መገመት፣
- የግምቱ ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣ ናቸው።

ከላይ እንደተጠቆመው የቃላት ትክክለኛ ፍች በአውዳዊ ፍንጮች አማካኝነት መገመት ይቻላል። እንደ (Nattinger 1988:62) ገለጻ፣ ቃላትን ከአውዳቸው መተንበይ ሲባል፣ የአዲሱን ቃል ፍቺ መገመትን በአንድ በኩል ፍቺ ለማስታወስ በሚቻልበት አኳኋን መመርመርን ሲመለከት፣ በሌላ በኩል አውዳዊ ፍንጮችን በመጠቀም የአዲሱን ቃል ፍቺ መገመትን ይመለከታል። በአውድ ውስጥ ለመገመት የሚያስችሉ የተለያዩ ፍንጮች

አሉ። ከነዚህ ፍንጮች መካከል Nattinger (1988:62)፣ Nunan (1991:121) እና Ying (2000:19-20) ከዘረዘሯቸው መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ።

- ሥነ-ምዕላዳዊ ፍንጭ፡- ይህ ቃሉ የተገነባበትን የተለያዩ ክፍሎች፣ የቃላት ቤተሰብንና ሌሎች የቃሉን መዋቅራዊ ስርአቶችን በመመርመር የአዳዲስ ቃላትን ፍች ለመተንበይ የሚያስችል ፍንጭ ነው።
- የብየና ፍንጮች፡- ቃሉ በውህድ አሃዱ የተሰጠው ብያኔ ካለ ፍቺውን ከብያነው መገመት ይቻላል።
- ዝርዝር ምሳሌዎች በመስጠት፡- ይህ ዋናው ቃል ከሌሎቹ ዝርዝር ጽንሰ ሐሳብ ካላቸው ቃላት ጋር ዝምድናውን በማሳየት ማቅረብ የቃሉን ትርጉም ፍንጭ መስጠት ይችላል። ለምሳሌ Gairns and Redam (1986:24) ያስቀመጡትን መመልከት ይቻላል።




ከስእሉ መገንዘብ የሚቻለው ጥቅል ጽንሰ ሃሳብን የያዘው ቃል ዝርዝር ጽንሰ ሃሳብን ከሚወክሉት ቃላት ጋር እቻ ትርጉም የሌላቸው መሆኑን ነው። ነገር ግን ተዛማጅነት ያላቸው መሆኑንም ያሳያል።

- የተመሳሳይና የተቃራኒ ቃላት ፍንጮች፡- የአዲሱን ቃል ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ጽንሰ ሐሳብ የያዙ ቃላትን በተለያዩ የማቅረቢያ መንገዶች በመጠቀም ፍንጭ መስጠት ይቻላል። ይህም አዲሱ ቃል የቀረበበትን አውድ ከቃሉ ጋር ከተሰጡት ተመሳሳይና ተቃራኒ ሀሳቦች፣ ቃሉ በተከታች ወይም በከታችነት የቀረበበትን ሁኔታ በመመርመር ፍንጭ ማግኘት ይቻላል።
- የትንበያ ፍንጭ፡- በዚህ በቀረበው አረፍተነገር፣ አንቀጽና ዕሑፍ ላይ በመመስረት የአዲሱን ቃል ፍቺ ለመገንዘብ የሚጠቅሙ የማጠቃለያ ፍንጮች በመጠቀም አንባቢው ከቀድሞው እውቀቱ ጋር በማገናኘት የሚረዳበት ሂደት ነው። የቃሉ ፍች ለመገመት

ከሚረዱ አያያዥ ቃላትም እንደመሆኑም፣ ለምሳሌ፣ ያም፣ ስለዚህ ወዘተ የመሳሰሉ ናቸው ።

- የንፅፅርና የአማራጭ ፍንጮች፡- አዲሱን ቃል ከሌላ ቃል ጋር በማነጻፀር ወይም ለቃሉ ሌላ አማራጭ በመስጠት የቃሉን ፍቺ መገመት ይቻላል።

ከቃላት አውዳዊ አቀራረብ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ቃላቱ የሚገኙባቸው ዓረፍተነገራዊ አውዶች መጠን (ርዝማኔ) ነው። ቃላት የሚቀርቡባቸው ዓረፍተነገራዊ አውዶች ከመጠን በላይ አጥረው ወይም ረዝመው የቃላቱን ፍቺ ለመገመት የሚያስቸግሩ መሆን የለባቸውም። በመሆኑም ቃላት የሚቀርቡባቸው ዓረፍተነገራዊ ዓውዶች ከአምስት እስከ አስር ቃላትን የያዙ ቢሆኑ የቃላትን ፍች መገመት እንደሚያመቹ፤ በአንጻሩ ከአምስት በታች ወይም ከአስር በላይ ቃላት የሚይዙ ከሆነ የቃላቱ መጠን እያነሰ ወይም እየጨመረ በሄደ ቁጥር ለትንበያ የሚያደርጉት አስተዋፅኦ እየቀነሰ ይሄዳል Nation እና Cody (1988፡105) ።

## 2.5.2 ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው አማካኝነት ማቅረብ

ተማሪዎች የቃላትን ንበት መመሳሰል መሰረት አድርገው ቃላት ቢያከማቹም፣በኋላ በትምህርት እየገፉ ሲሄዱ ቃላትን በአእምሮ ሰሌዳቸው ቀርጸው የሚያስቀምጡት በፍቺአቸው አማካኝነት ነው። በመሆኑም ተማሪዎች በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ ላይ እያሉ ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው መነሻነት ማቅረብ በቀላሉ የቃሉ ፍቺ እንዲገነዘቡ ያደርጋል (Richards 2001:187 እና McCarthy 1990:39)።

ቀደም ሲል የቃላት እውቀት በርካታ ጉዳዮችን እንደሚዳስስ ተመልክተናል። እንደ Wilkins (1982:124-126) እና Bauer (1988: 31-34) ገለጻ፣ ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆነውን የቃላት እውቀት ለማስጨበጥ የአዳዲስ ቃላት ፅንሰ ሀሳባዊና አገልግሎታዊ ልዩነቶች በሚያሳይ መንገድ ማቅረብ ይገባል። በመሆኑም ቃላትን በተመሳስሎአቸው፣ በተቃርኗቸው፣ በጥልቅና ዝርዝርነታቸው፣ እንዲሁም በአብሮ ተሰላፊነታቸው ለይቶ ማቅረብ ተገቢ ነው።

### 2.5.2.1 ቃላትን በተመሳሳይ ፍቺ ማቅረብ (Synonym)

በቃላት መካከል ፍጹም የሆነ ተመሳስሎ የለም። ምክንያቱም ቃላት በፍች ተመሳስሎ ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም አውድ አንዱ ቃል ሌላውን ሊተካ አይችልም። እንዲሁም ቃላት በተወሰነ መልኩ የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩበት መጠነኛ ባህሪ አላቸው። ይህም ማለት የአንዱ ቃል የሰፋ ጽንሰ ሐሳብ መያዝ፣ አንዱ በገባበት ሌላው አለመግባት፣ ሰዋሰዋዊ ባህሪያቸው መለያየት ወዘተ የሚሉት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ Allen(1983)።

Gairns እና Redman (1986:23) እንደገለጹት ሁለት ቃላት ፍጹም በሆነ ተመሳሳይነት ማገልገል የሚችሉ ቢሆን ኖሮ በቋንቋው ውስጥ የሚኖራቸው ተፈላጊነት አጠያያቂ ይሆን ነበር። ከገለፃው መረዳት የሚቻለው ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ናቸው ሲባል በፍቺ መቀራረባቸው እንጂ አንድ መሆናቸው አይደለም። በመሆኑም በሁለት ቃላት መካከል ፍጹም የሆነ አንድነት የለም። በመሆኑም በቋንቋ ትምህርት ተመሳሳይ የሚለውን ቃል ስንጠቀም ከፊል መመሳሰል እንጂ ሙሉ መመሳሰል አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

### 2.5.2.2 የቃላት ተቃራኒ ፍቺ

የቃላት ተቃርኖ በመጠቀም ቃላትን በተለያዩ የማቅረቢያ አይነቶች በማቅረብ ማስተማር ይቻላል። የቃላትን ተቃራኒ ፍቺ ስናስተምር የተለያዩ የተቃርኖ አይነቶችን ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለብን ምሁራን ያስገነዝባሉ። በመሆኑም Wilkins (1982: 126) Gairns እና Redman (1986: 25-27) እና Carter እና Mccarthy (1988: 23-24) የጠቆሟቸውን የተቃርኖ አይነቶች ቀጥለን እናያለን።

**ሀ. የደረጃ ተቃርኖ**

የደረጃ ተቃርኖ ማለት ቃላት ትንሽ ወይም ትልቅ የተመሳሰሉ ተቃራኒ ግንኙነት ያላቸው ቃላት ደረጃ አወጣጥን ይመለከታል። እነዚህ ቃላት በመካከላቸው ያለው ደረጃም በጣም ትልቅ፣ ትልቅ፣ መካከለኛ ፣ ትንሽ፣ በጣም ትንሽ ፣ እጅግ በጣም ትንሽ ወዘተ የሚሉ እንደግለሰቡ ግላዊ እሳቤ ደረጃ የሚሰጣቸው መጠኖችን ያካትታል። እንዲሁም የአንድ ነገር ትንሽ መሆን ወይም በተቃራኒ ትልቅ መሆን በተናጋሪው የግል እሳቤ ላይ

ይመረኮዛል። ይህም በሁለት ቃላት መካል ያለው ልዩነት አንጻራዊ መሆኑን ያሳያል። ለምሳሌ አንድ ሰው በሀሳቡ እራሱን ከ80 ኪ.ግ ክብደት ካለው ሰው ጋር አነጻዕሮ የሰውየውንና የራሱን የሰውነት ሁኔታ ወፍራም ወይም ቀጭን ሊል ይችላል።

ለ. የተገላቢጦሽ ተቃርኖ፡-

የተገለላቢጦሽ ተቃርኖ ሁለት ቃላት የተገላቢጦሽ ሊታይ የሚችል ተቃራኒ ግንኙነት እንዳላቸው የሚያሳይ ነው። ለምሳሌ፡- እህት/ ወንድም ፣ ባል/ ሚስት፣ ልጅ/ወላጅ ወዘተ. በሚሉት ቃላት መካከል ያለውን ተቃርኖ ለመግለጽ እህቱ ነች ለሚለው ወንድሟ ነው ወይም ሚስቱ ናት ለሚለው ባሏ ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ እንደነዚህ የመሳሰሉት ቃላት የተገላቢጦሽ ተቃርኖ አላቸው ማለት ነው ።

ሐ. አቅጣጫ ጠቀስ ተቃርኖ

ይህ አቅጣጫን መስፈርት ያደረገ የቃላት ተቃርኖን ይመለከታል። ለምሳሌ፡- እንደ መምጣት/መሄድ፣ መቆም/መቀመጥ፣ መውጣት/መውረድ የመሳሰሉ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አቅጣጫን የመጠቆም ባህሪ የሚታይባቸው ተቃራኒ ቃላትን ያጠቃልላል።

መ. ተጻራሪ ተቃርኖ

በተጻራሪ ተቃርኖ ሁለት ቃላት እርስ በርሳቸው ትይዩ ሳይሆኑ በአንድ ጊዜ ለአንድ ነገር መገለጫ አይሆኑም። ይህም ወንድ/ሴት ወይም ጧት/ማታ ዓይነት ተቃርኖ አንዱ ሌላውን መሆን በማይችሉ ቃላት መካከል የሚታይ ተቃርኖ ነው። ለምሳሌ አንድ እንስሳ ወንድ ከሆነ በምንም ተአምር ሴት ሊሆን አይችልም። በመሆኑም ወንድና ሴት፣ ጧት እና ማታ ጥንድ ተቃርኖ ያላቸው ቃላት ናቸው።

ከላይ ስለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ሲብራራ ሁለት ቃላት ከፍቺ አንጻር ፍጹም ተመሳሳይ እንደማይሆኑ ተገልጧል። እንዲሁም በሁለት ተቃራኒ ቃላት መካከል ፍጽም የሆነ ተቃትኖ እንደሌለ አይተናል። እዚህ ጋር በተያያዘ (Carter and McCarthy (1988:23 -29) እንደጠቆሙት፣ ተቃርኖ የሚመሰረተው በዲስኩር አውድ ስለሆነ እውነተኛ ተቃርኖ አለ ማለት አይቻልም። እንዲሁም እውነተኛ ተመሳስሎ ማግኘት ስለማይቻል የቃሉ እውነተኛ ፍች የምናገኘው ከአውዱ ነው ።

#### 2.5.2.3 የቃላት አጠቃላይና ዝርዝር ግንኙነት

ቃላት ከሚይዙት ጽንሰ ሃሳብ ስፋትና ጥበት መሰረት አጠቃላይ /ከታች/ ዝርዝር/ተካታች/ በማለት በሁለት ይከፈላሉ። አንዱ ቃል በርካታ ዝርዝር ጉዳዮችን አካቶ ሊይዝ ይችላል። ለምሳሌ፦ "እንስሳ" የሚለውን ቃል ብንወስድ በውስጡ የቤትና የዱር እንስሳት በሙሉ አካቶ ይዟል። ስለዚህ እንደ "እንስሳ" የመሳሰሉት ቃላት አጠቃላይ ናቸው ማለት ይቻላል። እንደ Yule (1996:119) አገላለጽ፣ የአንድን ቃል ፍቺ በሌላ ቃል ፍቺ የሚጠቃለል ሆኖ ከተገኘ የሁለቱ ቃላት ዝምድና የአጠቃላይና የዝርዝር የፍቺ ግንኙነት ነው ማለት ይቻላል።

የጥቅልነት እና የዝርዝርነት የቃላት ዝምድና ብዙ ጊዜ የሚታየው በስሞች መካከል ሲሆን ቃላት ከሚቀርቡባቸው ዋና ዋና መንገዶች አንዱ ነው። ለምሳሌ የ"ፍራፍሬ" እና "ተክል" የሚሉትን ቃላት መካከል ያለውን ዝምድና ብንመለከት ፍራፍሬ ተክል ነው በማለት በአንድ አቅጣጫ መጠቆም ይቻላል። ነገር ግን "ተክል ፍራፍሬ ነው" በማለት ለመጠቆም አይቻልም። ተክል ፍራፍሬ ብቻ ሳይሆን ከዛ እጅግ የሰፉ ፍቺን የያዘ ስለሆነ ነው። በመሆኑም ለተማሪዎች ጥቅል ቃላትን ሰጥቶ በውስጡ ሊካተቱ የሚችሉ ቃላትን እንዲዘረዝሩ በመጠየቅ በአጠቃላይና በዝርዝሮቹ መካከል ሊኖር የሚችለውን የፍቺ ዝምድና እንዲፈትሹ ማድረግ ይቻላል።

#### 2.5.2.4. አብሮ ተሰላፊ ቃላት

McCarthy (1990:12) እንደጠቆሙት "ውስኑነት" ከሚታይበት የፈሊጦችና ሌሎች ቃላዊ ሃረጋት አገላለጾች፣ በተለይ በቋንቋ ውስጥ በቃላት መካከል ዝምድናን የሚፈጥረው የቃላት አብሮ ተሰላፊነት ነው። ይህም አብሮ ተሰላፊ ቃላት እርስ በርሳቸው የአንዱ መኖር ለሌላው መኖር የግድ የሚያስፈልግና በፍች የተሳሰሩ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም ይህ የቃላት ዝምድና አይነት በማንኛውም ቋንቋ የቃላት ጥናት ውስጥ ቃላትን አደራጅቶ ማቅረብያ ዋና መርህ በመሆን ያገለግላል።

Nattinger (1988: 69-70) እንደሚያስረዱት የቃላት አብሮ ተሰላፊነት ለመረዳት የሚያስችሉ ሁለት መሰረታዊ ባህሪያት አሉ። አንደኛው አንድ ቃል አዘውትሮ አብሮት ከሚሰለፍ ሌላ ቃል ጋር በመሆን ሰፊ የፍች ይዘት ማስገኘት መቻሉ ነው። ይህም አብሮ

ተሰላፊ ቃላቱን በትውስታ ማህደር ለማከማቸት የሚረዳ ከመሆኑም በላይ የአንድ ቃል የፍቺ አካባቢን ለመበየን ያግዛል። ሁለተኛው ተማሪዎች አብረው ሊሰለፉ የሚችሉ ቃላትን እንዲለዩና ከአንድ ቃል ጋር አብረው ሊሰለፉ የሚችሉ ሌሎች ቃላት ይኖራሉ የሚል ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስችል ነው።

ከላይ እንደተገለጸው የቃላት አንድ ላይ የመከሰት ሁኔታ የቃላቱ የጥንካሬ ደረጃ ይወስነዋል። አንዳንዶቹ ቃላት የተወሰነ ቁርኝት ሲኖረቸው አንዳንዶቹ ቃላት ደግሞ የጠበቀ ቁርኝት የላቸውም፤ ሁል ጊዜ ጎን ለጎን ላይመጡ ይችላሉ። ከዚህ በተያያዘ Biber et al. (1998:251) እንደገለጹት፣ የጠበቀ ቁርኝት ያላቸው አብሮ ተሰላፊ ቃላት ሁል ጊዜ ጎን ለጎን አይቀመጡም፣ ምክንያቱም ቁርኝታቸው የሩቅ ሊሆን ስለሚችል። ይሁን እንጂ የቃላቱ ቁርኝት የሩቅ ቢሆን እንኳ በመካከላቸው በሚገቡ ቃላት ላይ ተፅእኖ አያደርጉም ። ለምሳሌ፡- "አንበሳው በሐይል አገሳ" በሚለው አውድ "አንበሳ ጮኸ" ማለት ያልተለመደ በመሆኑ ነው። ስለዚህ "አንበሳ" እና "አገሳ" የሚሉት ቃለት ምንም እንኳ ጎን ለጎን ባይቀመጡ እንኳን የጠበቀ ቁርኝት እንዳላቸው ግን መገንዘብ ይቻላል።

ከዚህ መረዳት የሚቻለው የቃላት አብሮ ተሰላፊነት ሊያሳዩ የሚችሉ መልመጃዎች በተለያዩ ዘዴዎች ተጠቅሞ መቅረፅ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ በአረፍተነገራዊ አውድ ተገቢውን አብሮ ተሰላፊ ቃል በሌላ ቃል ተክቶ በማቅረብ ተማሪዎች አረፍተነገሩን በመመርመርና ተገቢ ያልሆነውን ቃል በመለየት በተገቢ ቃል እንዲተኩ በመጠየቅ ሊከናወን ይችላል። ይህንን አስመልክቶ Nattinger (1988: 70) ሲገልጹ አብሮ ተሰላፊ ቃላትን አንዱን ቃል በአውድ ውስጥ በማቅረብ የሌለውን ቦታ ክፍት ትቶ ተማሪዎች እንዲሞሉት በማድረግ ማለማመድ ይችላል።

### 2.5.3 የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርአት መሰረት አድርጎ ማቅረብ

በቋንቋ ውስጥ በአንፃራዊ አነጋገር ጥቂት ቁጥር ያላቸውን ቃላት አፈጣጠር ሂደት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን አዳዲስ ቃላት መፍጠር ይቻላል Macarthy (1990:90):: ቃላት የተለያዩ አርቢ ምእላዶችን በመጨመር ልዩ ልዩ ቅርፆች ሊይዙ ይችላሉ።

እንደ ጌታሁን (1990፣50) ገለጻ፣ በአማርኛ ቋንቋ ቅጥያዎች ቃላትን የማርባትና የመመስረት ተግባር አላቸው። የእርባታ ሂደት የቃሉ መሰረታዊ ባህሪ ሳይለወጥ

በቅጥያዎች አማካኝነት የሚደረግ የቃላት የእርባታ ሂደት ሲሆን በቅጥያ አማካኝነት ከነበሩበት የቃል ክፍል ወደ ሌላ የቃል ክፍል የሚለዋወጡበት ሂደት ደግሞ ምስረታ ይባላል። ለምሳሌ "በግ" ብለን በጎቼ፣ በጎቻችን፣ በጎችህ፣ ወዘተ ብንል ቃሉ ከነበረበት የቃል ክፍል ወደ ሌላ የቃል ክፍል ስላልተለወጠ ሂደቱ እርባታ ነው ስንል። "ቆረጠ" ብለን መቁረጫ፣ ቁራጭ፣ ቆራጣ ወዘተ. ብንል ቃሉ ከነበረበት የቃል ክፍል ወደ ሌላ የቃል ክፍል ስለተለወጠ ሂደቱ ምስረታ ነው ማለት እንችላለን። በሁለቱም ሂደቶች ቅጥያዎች በቅድመ አምድና በድህረ አምድ መግባት ይችላሉ።

በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ቃላትን ለማርባትና ለመመስረት የሚያስችሉ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ቅጥያዎች አሉ። እነዚህ ቅጥያዎች በሰዋስዋዊ ተግባራቸው መነሻነት የእርባታና የምስረታ ቅጥያዎች በመባል በሁለት ይከፈላሉ። የእርባታ ቅጥያዎች በቃል አምድ ላይ እየተቀጠሉ ቃሉ ለመደብ፣ ለቁጥር፣ ለሙያ፣ ለእምርነት ወዘተ በመርባት የተለያየ ቅርጽና ተጨማሪ ፍቺ እንዲኖረው ያደርጋሉ። ይህንን "ልጅ" የሚለውን ቃል እንደምሳሌ ወስደን ብንመለከት "ልጅ" ላይ/-ኡ-/ የሚል ድህረ አምድ ቅጥያ ብናስከትለበት "ልጁ" ይሆናል። በፍቺ ረገድም ማንኛውም ልጅ ሳይሆን ተናጋሪውና አድማጩ የሚያውቁት ልጅ መሆኑን ግልፅ ያደርጋል (ባየ 2000፣108 እና 109)።

የምስረታ ቅጥያዎችም እንዲሁ በቃል አምድ ላይ በመቀጠል በቃሉ ላይ የቅርጽ ለውጥ ብቻ ሳይሆን የነበሩበትን የቃል ክፍል ወይም ንኡስ የቃል ክፍል ሊለወጡ ይችላሉ። ለምሳሌ /-ነት/ የሚል ድህረ አምድ ቅጥያ "ሰው" በሚል ነባር ስም ላይ ሲቀጥል "ሰውነት" የሚለውን ቃል ያስገኛል። ነገር ግን "ሰውነት" የሚለው ምስርት ቃል "ሰው" ነው እንደሚለው ነባር ስም ሳይሆን ረቂቅ ስም ነው። ስለዚህ ሂደቱ ከአንድ ቃል ሌላ አዲስ ቃል መፍጠርን ያሳያል (ባየ 2000፣ 154-155)። በቃላት የእርባታና የምስረታ ሂደት ላይ ያተኮረ ትምህርት ለተማሪዎች ማቅረብ ተገቢ ነው። ለምን ቢባል የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርአት ማስተማር ለተማሪዎች የቃላትን ፍቺ ለመረዳትም ሆነ አፍልቆ ለመጠቀም ይረዳቸዋል Ur(1996:62) እና (McCarthy 1990:99)። በመሆኑም ትምህርቱ ከማፍለቂያ ክሂሎች አንጻር ሲታይ ደግሞ ተማሪዎች ጥቂት መሰረታዊ የሆኑትን የቃለት አፈጣጠር መርሆችና የተወሰኑ ምሳሌዎች ማወቃቸው፣ በተመሳሳይ የአረባብና የአመሰራረት ስርዓት ተጠቅመው ሌሎች ቃላትን ባስፈለጋቸው ጊዜ እያረቡና እየመሰረቱ መጠቀም ይችላሉ።

Gairns and Redman (1986:49) እንደገለጹት፣ የቃላት ምስረታና እርባታ ሂደት መሰረት ያደረገ የቃላት ትምህርት ለጀማሪዎች ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ እንዲሁም፣ ከፍ ላሉ ተማሪዎች ደግሞ በቀጥታ ማቅረብ ተገቢ ነው። በመሆኑም የቃላት ምስረታና እርባታ መሰረት ያደረገ ትምህርት የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ ከተፈለገ የተማሪዎችን የአቅም ደረጃ ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

### 2.5.4 የቃላት አጠቃቀምና አመራረጥ ስልትን መሰረት በማድረግ ማቅረብ

ቃላት ነገሮችን ከመግለጽ አንፃር የተለያዩ ተግባራት አላቸው አንዳንዶቹ ቃለት ምስል ካሰች ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ተራና እምቅ ቃላት ናቸው ። እንዲሁም ቃላትን ለተለያዩ ጉዳዮች ስንጠቀም እንደ ርእሰ ጉዳዩ፣ እንደ ተወያዮች፣ እንደ መወያያው ቦታና ሁኔታ እንደ ተወያዮቹ ማህበራዊ ደረጃና ሙያ፣ እንደ ተወያዮቹ እድሜና ጾታ ወዘተ ግምት ውስጥ በማስገባት አጠቃቀማቸውን እንወስናለን። በመሆኑም ተማሪዎች ይህንን የቃላት አገልግሎታዊ ባህሪ ተገንዝበው ቃላትን እንደአስፈላጊነቱ መርጠው እንዲጠቀሙ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው (ተስፋዬና ማረው 1993፣4)።

Scriverner (1998:75) እንደጠቆሙት የቃላት ትምህርት ትኩረት ነጠላ የሆኑ ቃላትን ብቻ ሳይሆን ረጅምና ባለብዙ ሀረጎችንም መመርመር ያስፈልጋል ። እንዲሁም Lewis እና Hill (1992:98) የቃላት ትምህርት ትኩረት ቃላዊ ሀረጋት በቃላት ትምህርት ውስጥ ማካተት ከቻለ ተማሪዎች በቋንቋው በመሚገባ ለመግባባት እንዲችሉ ከማገዝ አንጻር ትልቅ ድርሻ አለው።

#### 2.5.4.1 እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ

የአንድን ቃል ፍቺ በምንመለከትበት ጊዜ በእውኑ አለም ምንን ያመለክታል ወይም ይወክላል ማለታችን ነው። ወካይነቱም እማሪያዊ ወይም ፋካርያዊ ይሆናል። ለምሳሌ፡- "ውሻ" የቤት እንስሳ የሚለው ፍቺ እማርያዊ ሲሆን፣ልክስክስ፣ ዙረታም፣ ቆሻሻ የሚሉት ደግሞ ፍካሪያዊ ፍቺ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ውሻ በተለያየ አካባቢ የተለያየ ፍቺ ሊኖረው ይችላል። የቤት እንስሳ የተለመደ ሲሆን በአረቦች ደግሞ "ነጂስ" ማለትም ያልተቀደሰ፣ የረከሰ፣ ቆሻሻ ወዘተ. ሊሆን ይችላል። አልፎ አልፎም ልክስክስ የሚለውን

ፍቺ ሊይዝ ይችላል። እነዚህ ፍቺዎች ከመዝገበ ቃላት ውጪ የሚገለጹ ናቸው። ሌላው ፍቺ ደግሞ ማሕበራዊ አውድን ተከትሎ የሚገለጽ ነው። በአንዳንድ አካባቢዎች የሚነገሩ ቃላት የጋራ መጠቀሚያ በሌላ አካባቢ ደግሞ ሓራም (Taboo) ቃላት ሊሆኑ ይችላሉ።

Harmer (1993:157 እና ማረው 1998፡8) እንደጠቆሙት፣በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ላሉ ተማሪዎች ተጨባጭ የሆኑና አማርያዊ ፍቺ የያዙ ቃላት ማቅረብ ይኖርብናል። ምክንያቱም ተጨባጭ የሆኑና አማርያዊ ፍቺ ያላቸው ቃላት ብዙን ጊዜ የሚገልጹት የሚታይና የሚዳሰስ ነገር ስለሆነ ቃላቱ በቀላሉ እንዲወሱ ያደርጋሉ። በመሆኑም ተማሪዎች የተማሯቸውን ቃላት አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ለማስታወስና ሀሳባቸውን በንግግር ሆነ በጽሑፍ ለመግለጽ ያስችላቸዋል።

### 2.5.4.2 ፈሊጣዊ አነጋገሮች

ፈሊጣዊ አነጋገሮች የተለያዩ ነገሮችን ለመግለጽ እንደ ተራ/ነጠላ/ ቃላት በቀጥተኛ ፍቺ ሳይሆን በተለያየ መንገድ መግለጽ ማለት ነው።

ፈሊጣዊ አነጋገሮች አልፎ አልፎ እንደ ድርብ ቃላት የሚታዩበት ጊዜ አለ። ይኸውም ከሚሰጠው ፍቺ አንጻር ነው። ድርብ ቃላት የሚሰጡት ፍች ለምሳሌ በመጀመሪያ ቃላቱ " ዐይን" እና "አውጣ" የተለያዩ ቃላት ሲሆኑ የተለያየ ፍቺ አላቸው። ነገር ግን በአንድ ላይ በማጣመር "ዐይን አውጣ" የሚል ድርብ ቃል ሲመሰረቱ ከፊተኞቹ ሁለት ፍችዎች የተለየ ይፍች ይሰጣሉ። ፈሊጣዊ አነጋገርም በተመሳሳይ መልኩ በስርአት ተሰባስበው ፈሊጣዊ አነጋገር ቢመሰረቱም ቃላቱ የመጀመሪያ ፍቻቸውን በመልቀቅ ሌላ አዲስ የተለየ ፍቺ ያስገኛሉ።

እንደ Wallace (1982፣117) አገላለጽ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከቃላት የሚለዩባቸው ሁለት መሰረታዊ ነገሮች አሉ እነሱም፡-

ሀ. ፈሊጣዊ አነጋገሮች ቀጥተኛ ፍቺ የያዙ አይደሉም እንደ ድርብ ቃላት የተለየ ፍቺ በመግለጽ የሚታወቁ ናቸው።

ለ. የፈሊጣዊ ንግግር ፍቺ የተለየ መሆን ብቻ ሳይሆን ፍቻቸውን በቀላሉ መገንዘብ ያስቸግራል።

ከፍ ሲል እንዳየነው የፈሊጣዊ አነጋገር ችግር የፍች ጉዳይ ነው። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን የአማርኛ ፈሊጣዊ አነጋገሮች እንመልከት

1. የሰማይ ስባሪ = ረዥም
2. ቀትረ ቀላል = ከውካዋ

McCarthy (1990:7) እንዳስገነዘቡት፣ ፈሊጦች በውስጣቸው ተመርጠው የሚገኙ ቃላትን በመነጣጠል ለመፍታት መሞከርና ፍቻቸውን ለመረዳት ማሰብ ብሎም በዚህ መንገድ ለተማሪዎች ማቅረብ የፈሊጣዊ አነጋገሮችን ፍቺ መረዳት አይችሉም።

እዚህ ጋር በተያያዘም Wallace (1982:118) ሲገልጹ፣ አንዳንድ መማሪያ መጽሃፍት ፈሊጣዊ ቃላትን ከአንድ ቃል ጋር በጥምረት የሚመሰረቱ ፈሊጦችን በአንድ ላይ እንደሚያቀርቡ ቢታዩም አካሄዱ ተገቢ እዳልሆነ አብክረው ይገልጻሉ።

ከዚህ አንጻር ፈሊጣዊ አነጋገሮች ለተስተምህሮ ምቹ በሆነ መልኩ መቅረብ ይኖርባቸዋል። ይህንን በተመለከተ Wallace (1982፣119) ሲገልጹ፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ለማስተማርም ሆነ ፍቺ ለመግለጽ፣ የሚያስችል የተስተምህሮ ስልት በብዛት አይታዩም። ሆኖም የጋራ ባህሪይ ያላቸውን ቃላት የያዙትን በአንድ ላይ በመሰብሰብ ማጥናት ይቻላል። ለምሳሌ ስም የያዙ በአንድነት በማቅረብ ማስተማር ይቻላል። ከላይ ከተገለጸው አቀራረብ በተጨማሪ የሚከተሉትን ነጥቦች በመጠቀም ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ለትምህርት ማቅረብ ይቻላል።

- የሚቀርቡት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከተሻጋሪ ወደ ኢ-ተሸጋሪ እንዲሁም ከኢ-ተሸጋሪ ወደ ተሻጋሪ አረፍተነገር በማቀያየር መመልከት ይችላል።
- ባለ ብዙ ቃላትና ጥምር ቃላት የያዙትን በመለየት ማስተማር ይቻላል።
- በሀረግ ደረጃ ማቅረብ እና በመሳሰሉት አቀራረቦች በመጠቀም ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ለትምህርት ማቅረብ ይቻላል።

ከፍ ሲል የተገለጹት ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ለማሰተማር አመቺ ስልቶች ናቸው። ሆኖም ከአማርኛ ቋንቋ አንጻር ስንመለከታቸው ግን በሙሉ የሚያስኬዱ አይመስሉም ። የአማርኛ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ግሶቻቸውን ብቻ በመቀያየር ማስተማር ይቻላል።

ለምሳሌ " የሱ ነገር ፍሬ ከርስኪ ነው" የሚል አነጋገር " የሱ ነገር ፍሬ ከርሲኪ ሆኗል" የእሱ ነገር........ ነበር፣ ወዘተ. በማለት መግለጽ ይቻላል።

### 2.5.4.3 የተለመዱ አገላለጾች

Lewis (1993:94) እንደጠቆሙት፣ የተለመዱ አገላለጾች በተግባቦት ሂደት ተናጋሪወ ወይም ፀሐፊው ሊገልጸው የፈለገውን ጉዳይ አስቀድመው ይጠቁማሉ። ዋና አገልግሎታቸውም ተግባቦቱ ስኬታማና ፍሰት ያለው እንዲሆን ማድረግ ነው። እንዲሁም አድማጭ ወይም አንባቢ ተናጋሪው ወይም ፀሐፊው ሊገልጽ ወይም ሊያደርግ የፈለገውን በፍጥነት መለየት ማስቻል ነው።

ከምሁሩ ገለፃ መረዳት የሚቻለው የተለመዱ አገላለጾች በተግባቦት ሂደት ተናጋሪው ከአድማጩ፣ ጸሐፊው ከአንባቢው ጋር በሚያደርገው መስተጋብር ውስጥ የመስተጋብሩን አካሄድ መንገድ የሚያስይዙ የቃላት ጥምረቶች ናቸው። የተለመዱ ቃላዊ አገላለጾች እጅግ ብዙ ናቸው። ለምሳሌ ያህል፣ በዚህ ረገድ ፣ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ከዚህም ሌላ፣ በተጨማሪ ፣ ነገርግን ፣ ለማጠቃለል ያህል ፣ ያም ሆኖ፣ ይህንን በተመለከተ፣ በነገራችን ላይ፣ በዚህም በዝያ ብሎ፣ የሆነ ሆነና ወዘተ. መጥቀስ ይቻላል።

McCarthy (1990:9) እንደጠቆሙት፣ የተለመዱ አገላለጾች ሃሳብን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ለማስተላለፍ፣ ሃሳብን ለመጀመር ፣ አፅንኦት ለመስጠት፣ በምሳሌ ለማስረዳት፣ ፍሰቱን ለመጠበቅ ርእስ ጉዳዩን ለመቀየር፣ ለማጠናከር፣ ልዩነቱን ለማሳየት ወዘተ. ለመግለጽ ይጠቅማሉ።

የተለመዱ አገላለጾችን ለአፍልቆት አስፈላጊ ስለሆኑ ለተማሪዎች ሲቀርቡ በጥቂት የተለመዱ ሃረጋት በመጀመር ቀስ በቀስ በማስፋፋት መሙላትና የትክ(መተኪያ) መልመጃዎችን በማዘጋጀት ማለማመድ ይቻላል። እንዲሁም ከንግግርና ከጽሕፈት ጋር በማያያዝ በተግባር እንዲጠቀሙባቸው ማለማመድ ይኖርብናል (Nattinger 1988:78)።

### 2.5.5 ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ማቅረብ

ተማሪዎች የተረዱቸውን አዳዲስ ቃላት አስታውሰው ትርጉም ባለው አውድ መጠቀም የሚጀምሩት የቅበላ ክሂሎቻቸውን ተጠቅመው ባገኙት እውቀት ነው።የተገነዘቧቸውን

ቃላት አፍልቀው መጠቀም ማለት ደግሞ በተለያዩ አውዶች ስልታዊና ፈጠራ በተሞላበት መንገድ መገልገል ይመለከታል (Ming 1993: 11-12)። እንዲሁም Lewis (1993:114) እንደገለጹት፣ ተማሪዎች መግባባት እንዲችሉ በተገቢ የቃላት ትምህርት መታገዝ ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ቃላትን ከሌሎች ክሂሎች ጋር አጣምሮ ማቅረብ የመማር ሂደቱን የተቃና ያደርገዋል ። ይህም የተማሪዎች የተግባቦት አቅም መጠኑን በጠበቀ የቃላት ትምህርት ክንውን እንዲታገዝ ያደርጋል።

ተማሪዎች ቃላትን እንዲረዱ ከተፈለገ የቃላት ፍቺን ግልጽ በማድረግ ከሌሎች ቃላት ጋር አብረው የሚገኙባቸውን ውህድ አሃዶች እንዲያነቡ ወይም እንዲያዳምጡ መደረግ አለበት። በዚህ ሂደት ተማሪዎች አስቀድሞ በተቀመጠላቸው ተግባር መሰረት ተፈላጊውንና የማይፈለገውን መረጃ የመለየት ሙከራ ያደርጋሉ። የውህድ አሃዱን ተፈላጊ መረጃ ለማግኘት ሲባልም የትኞቹ ቃላት ተከታትለው እንደተከሰቱ፣ በመካከላቸው ምን አይነት ዝምድና እንደመሰረቱ በቀረቡበት አውድ የቃላቱን ፍቺ ምን ሊሆን እንደሚችል መርምረው ይረዳሉ። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች አቀባይ ክሂሎችን ተጠቅመው ቃላትን የመረዳት ችሎታቸውን የሚያዳብሩ መሆኑን ነው (Joe 1995:1-2) Cumino (1990: 15)።

Eyraud (2000:2) እንደጠቆሙት፣ አብዛኛው የቃላት እውቀት የሚጨበጠው በክሂሎች (በማንበብ፣ በማድመጥ፣ በንግግርና በመጻፍ) ነው። በተለይ ከንባብ ጋር አጣምሮ ማቅረብ ከሁሉም የበለጠ ተስማሚ እንደ ሆነ የቀድሞ ጥናቶች ይጠቁማሉ። በመሆኑም የቃላት ትምህርት ከክሂሎች ጋር ተጣምሮ መቅረብ ይኖርበታል ማለት ነው።

የጥያቄና መልስ ስልትን እንዲሁም ያነበቡትንና የሰሙትን እንደገና የመናገር ስልት መጠቀም የአፍልቆት ቃላት እውቀትን ለማዳበር ጉልህ ድርሻ አለው። በዚህ ስልት በቅድሚያ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላት ያለበትን አንድ ታሪክ በየግላቸው እንዲያነቡ ይደረጋል። በመቀጠል ያነበቡትን ወይም ያዳመጡትን መልሰው በጥያቄና መልስ እንዲናገር ይደረጋል። ይህም ተማሪዎች ጥንድ እንዲሆኑ በማድረግ አንዱ ተማሪ ጠያቂ ሌላው መላሽ፤ እንዲሁም መላሽ የነበረውን ጠያቂ በማድረግ ማከናወን ይችላል። እዚህ ላይ የሚቀርቡ ጥያቄዎች በትረካው የተከካተቱ ነጥቦች ጨምቀው ያያዙ ሊሆኑ ይገባል (Simcock 1993:1 እና Joe 1995: 1-4) ።

ባጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት የሚቻለው፣ ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ተጣምረው ሲቀርቡ በማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ውህድ አሃዶች ከንግግርም ከጽሑፍም የተገኙ መሆን እንዳላቸው፣ ቃላትን አፍልቆ የመጠቀም ልምምድ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በንግግርም በጽሑፍም መከናወን እንደሚገባው እና የቃላትን ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ጋር አዋህዶ ማቅረብ የቃላትን ዐውዳዊ አጠቃቀም በተጨባጭ ዐውድ ማሳየት አስፈላጊ መሆኑን ነው።

### 2.5.6 የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ

ተማሪው መምህሩን ወይም ጓደኛው ጠይቆ መረዳት በማይችልበት ወቅት መዝገበ ቃላትን በመጠቀም ችግሩን ሊፈታ እንደሚችል ይታመናል። በመዝገበ ቃላት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከሆኑት መካከል ንበትን፣ ሰዋሰውንና ፍችን ማስተማር ይቻላል (Gairns እና Redman 1986: 70-71)። እዚህ ጋር በተያያዘም Hunt እና Belgar 2002፣6) "ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ተማሪዎች የአንድን ቃል የተለያየ ፍች እንዲረዱ ያግዛቸዋል ፤ የአንድን ቃል ትክክለኛ ፍቺም ከዐውድ እንዲገነዘቡ ጉልህ ድርሻ አለው።" በማለት ይገልጻሉ።

በቃላት ትምህርት ተማሪዎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ሶስት አይነት መዝገበ ቃላት አሉ። የመጀመሪያው ልሳነ ክልኤ መዝገበ ቃላት ሲሆን የታላሚውን ቋንቋ ቃላት በተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ይተረጉማል። ሁለተኛው ልሳነዋህድ መዝገበ ቃላት ሲሆን የታላሚውን ቋንቋ ቃላት በዚያው በታላሚው ቋንቋ የሚገልፅ ነው። ሶስተኛው ደረጃውን የጠበቀ መዝገበ ቃላት ሲሆን እንደ ልሳነ ዋህድ መዝገበ ቃላት ሁሉ በአንድ ቋንቋ የሚዘጋጅ ነው። ልዩነታቸው ደረጃውን በመጠበቅ ረገድ ነው።እንዲሁም ደረጃው የጠበቀ መዝገበ ቃላት ሲዘጋጅ አፍ ፈቶችን ታሳቢ አድርጎ የሚዘጋጅ በመሆኑ ከልሳነ ዋህድ መዝገበ ቃላት ይለያል (Seal 1991:308)።

ከላይ ከተዘረዘሩት መዝገበ ቃላት ለማስተማር ተስማሚ የሆነው የትኛው ነው ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ አስተያየቶችን ሰንዝረዋል። Morley (1990:21) እንዲጠቁሙት፣ አንድም ለተማሪዎች በተሰጡት ተግባራትና ባላቸው የቋንቋ እውቀት ይወሰናል። በሌላ መልኩ ደግሞ ፍጹም የሚባል መዝገበ ቃላት ባለመኖሩ ተማሪዎች እንደፍላጎታቸው የሚመርጡትን መዝገበ ቃላት ሊጠቀሙ ይገባል።

ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት የሚቻለው፣ በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሚካተተው ትምህርት ትኩረቱ መዝገበ ቃላትን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ማሳየትና የአጠቃቀም ጥበቡን በማለማድ ላይ ትኩረት ማድረግ ያለበት መሆኑን ነው።

Scrivener (1998:73) እንዲገለጹት፣ በመዝገበ ቃላት አስደግፎ የሚቀርብ የቃላት ትምህርት አቀራረብ በአጠቃቀም ብልሃት ላይ ትኩረት አድርጎ ከቀረበ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ባስፈለጋቸው ጊዜ ስለቃላት የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት መዝገበ ቃላትን የመጠቀም ልምድ እንዲያዳብሩ ከማድረግ አንጻር ድርሻው የጎላ ነው።

## 2.5.7 የቃላት ትምህርት መመሪያ የአቀራረብ ግልጽነት

Alderson (1995:41) እንደገለጹት ፣ ተማሪዎች የሚጠበቀውን የአመለካከትና የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ ከተፈለገ የቋንቋ መልመጃ መመርያዎች ቋንቋ ነክ ተግበራት የሚገልጹና መልመጃዎች ለልምምድ የሚያበቋቸው ሆነው ሊቀርቡ ይገባል። በመሆኑም የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ለተማሪዎች ሲቀርቡ፣ ግለጽ ሆነው ሊቀርቡ ይገባል።

እንዲሁም Wallace (1982:73) እንደጠቆሙት፣ ግልጽና ማብራሪያ የታከለባቸው የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ለማዘጋጀት በቃላት ትምህርት ላይ ያተኩሩ ምርምሮችን መቃኘት አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ ተመሳሳይ ቃላትን ለማለማመድ የተዘጋጁ መልመጃዎች ቢኖሩ የተመሳሳይ ቃላቱ ፍካሪያዊና እማርያዊ ፍቺያቸው ከሚነበቡበት አውድ ወይም አብረው ሊሰለፉ ከሚችሉ ሌሎች ቃላት አንጻር ሊመዘኑ ይገባል። ምክንያቱም ተመሳሳይ ቃላት አጠቃላይ በሆነ እይታ ተመሳሳይ ቢመስሉም በተግባር ሲመረመሩ ግን ልዩነት ሊኖራቸው እንደሚችል ይታመናል። ስለዚህ የተመሳሳይ ቃላት ትምህርት የሚቀርብባቸው መመሪያዎች ይህንኑ መመሳሰል አንፃራዊ መሆኑን የሚጠቁም ማብራሪያ ቢታከልባቸው ተማሪዎቹ የቀረቡላቸው መልመዎች በተፈለገው መንገድ ሊሰሩ ይችላሉ።

በአጠቃላይ የቃላት ትምህርት የመልመጃ መመሪያዎች፣ ትኩረት፣ መልመጃው ያተኮረበትን ይዘት፣ መመሪያዎቹ ግልጽና የተብራሩ፣ በጥናትና በጥንቃቄ የተዘጋጁ እና ተገቢ የሆኑ ምሳሌዎችን አስደግፈው የተቀረጹ ሊሆኑ ይገባል።

## 2.6 በሀገር ውስጥ የተካሄዱ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

አጥኚው ባደረገው አሰሳ በቃላት ላይ ያተኮሩ የሀገር ውስጥ ጥናቶች ተገኝተዋል። ለጊዜው የተገኘው መረጃ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (6 ኪሎ) ሶስት አማርኛን ማስተማር (Teaching Amharic) ለድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለሆለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች መጥቀስ ይቻላል። እነሱም፡- ትንሳኤ(1988)፣ ሲሳይ (1990)፣ እና አንበሴ (1993) ናቸው።

ሀ. ትንሳኤ ብርሃኔ (1988)

የትንሳኤ ርእስ "የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ፈተናዎች በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት" የሚል ሲሆን ጥናቱም ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ነው። የጥናቱ አላማ በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ውስጥ የቀረቡ የቃላት ጥያቄዎች ተገቢነት ያላቸው መሆንና አለመሆናቸውን መመርመር ነበር። በጥናቱ የተገኘው ውጤትም ጥያቄዎቹ በአውድ ያልቀረቡ፣ ግልጽ እና አላማ የሌላቸው፣ አቀራረባቸው አውድን ያልተከተሉ፣ አቀራረባቸው የትምህርቱን አላማና የማስተማር ዘዴ መሰረት ያላደረጉ መሆናቸውን ተረጋግጧል።

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍና የትንሳኤ ስራ በቃላት ትምህርት ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶች በመሆናቸው ይመስላሉ። የዚህ ጥናት ትኩረት ግን አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የትግራይ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ የሚመርመር በመሆኑ ከትንሳኤ/ 1988) ጥናት የተለየ ነው። በመሆኑም ሁለቱም ጥናቶች ከሚያተኩሩበት ርእስ፣የክፍል ደረጃና ከጊዜ አንጻር ልዩነታቸው ሰፊ ነው።

ለ. ሲሳይ ተበጀ (1990)

ሲሳይ "በአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በስራ ላይ ያለው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ቃላትን በማስተማር ረገድ ያለው ብቃት" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት አቅርቧል። የጥናቱ አላማም የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ መገምገም ነው። በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከቃላት

ትምህርት አጠቃቀም ይልቅ በፍቻቸው ላይ የተመሰረተ መሆኑን፣ አውዳዊ አቀራረብ የሚከተልና የቃላት ትምህርት አቀራረብ አብዛኛው ከአንብቦ መረዳት ጋር የተያያዘ መሆኑን ተመልክቷል ።

ይህ ጥናት እና የሲሳይ ጥናት የሚያመሳስላቸው ሁለቱም በቃላት ትምህርት ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶች መሆናቸው ነው። ሆኖም ግን የዚህ ጥናት ትኩረት አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የትግራይ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ መመርመር ሲሆን የሲሳይ ጥናት ግን ትኩረቱ ለአፍፌትና ለኢ-አፍፌት በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ነው። እንዲሁም የክፍል ደረጃው ለሁለተኛ ደረጃ የተደረገ ጥናት በመሆኑ በትኩረት አቅጣጫ እና በክፍል ደረጃ እንዲሁም ከግዜ አንጻር ይለያያሉ።

ሐ. አንበሴ በቀለ (1993)

ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የአንበሴ በቀለ (1993) "በኦሮሚያ ክልል ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ትንተና" በሚል ርእስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ነው። የጥናቱ ዓላማም በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በ1990 ዓ.ም በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት ትምህርት አመራረጥና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል መመርመር ነው። በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በተተኳሪው መጽሐፍ ቃላት በተገቢው መንገድ አለመመረጣቸው እና አለመደራጀታቸው እንዲሁም አዳዲስ ቃላት በተደጋጋሚ አለመቅረባቸው ተረጋግጧል።

የአንበሴ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በ8ኛ ክፍል በቃላት ትምህርት ዙሪያ የተካሄደ ጥናት መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ የአንበሴ ጥናት በኦሮሚያ ክልል በ1990 ዓ.ም በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ መመርመር በሚል ይዘት የተካሄደ ጥናት በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር በክልል፣ በጊዜና በትኩረት አቅጣጫ ይለያያሉ። እንዲሁም ይህ ጥናት በቃላት አቀራረብ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ለቃላት ትምህርት አመራረጥና አደረጃጀትም ትኩረት የሰጠ በመሆኑ ይለያያሉ።

ባጠቃላይ በምእራፍ ሁለት የቃላት ምንነት በተመለከተ ብያኔ በመስጠት፣ ስለቃላት እውቀት ምንነት፣ ስለቃላት አቀራረብ በመስኩ ምሁራን የተሰጡ አስተያየቶችና በምርምር የተደገፉ ልዩ ልዩ መስፈርቶች እንዲሁም ስልቶች በማንሳት በመማርያ መጽሐፍ ዝግጅት ጊዜ በስራ ላይ ማዋል እንደሚያስፈልግ ለመጠቀም ጥረት ተደርጓል። በተከታዩ ምእራፍ ደግሞ ጥናቱ የተከተለው የአሰራር ዘዴ በዝርዝር ይቀርባል።

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.1 የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት መሰረት ያደረገው ዓይነታዊ(Qualitative research) የምርምር ዓይነት ነው። በመሆኑም በመማሪያ መጽሐፉ በቀረቡ ቃላት አመራረጥ፣አደረጃጀትና አቀራረብ ላይ የይዘት ትንተና (Content analysis) ተካሂዷል። ከይዘት ትንተና፣ከመጠይቅና ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በገላጭ (discributive) አፃፃፍ ስልት ተተንትነው ቀርበዋል።

## 3.2 የናሙና አመራረጥ

### 3.2.1 የመፅሃፍ ናሙና አመራረጥ

አሁን ባለው የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የአንደኛ ደረጃ የመማሪያ መፃሕፍት የሚዘጋጁት በክልሎች ነው። በክልሎች ከሚዘጋጁ መማሪያ መፃህፍት መካከል በ1991 ዓ.ም የተዘጋጀው የትግራይ ክልል የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ነው። ምንም እንኳን የቃላት ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ የተወሰኑ ጥናቶች የተካሄዱ ቢሆኑም በትግራይ የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በተመለከተ የተሰሩ ስራዎች አጥኚው ባደረገው ዳሰሳ ባለማግኘቱ ተተኳሪ መጽሐፉ ለዚህ ጥናት ተመርጧል።

### 3.2.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው፣ በ1991 ታትሞ በ2001 ተሻሽሎ በአንደኛው ደረጃ ሁለተኛ እርከን ግልጋሎት በመስጠት ላይ የሚገኘው የትግራይ ክልል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ ነው። ጥናቱ በትግራይ ክልል ያተኮረበት ዋናው ምክንያት አማርኛ ለተማሪዎቹ ሁለተኛ ቋንቋ በመሆኑ የቃላቱ አቀራረብ ከተማሪዎች ጻራ አንጻር ያለው ተገቢነት ለመፈተሽ ያስችላል ከሚል እሳቤ ነው።

በትግራይ ክልል ከሚገኙ 6 ዞኖች መካከል መቀሌ ልዩ ዞንና ደቡብ ዞን አመቺ ናሙና (convenience sampling) በመጠቀም ተመርጠዋል። አመቺ ናሙና የተመረጠበት ምክንያት አንደኛ፣ የመጽሃፉ አዘጋጆች መቀሌ ሰለሚገኙ መረጃውን ለመስብሰብ ያመቻል

ከሚል እሰቤ፤ ሁለተኛ አጥኚው በትግራይ ደቡብ ዞን ለአኾም ጊዜ በመሥራቱ የተለያዩ መረጃዎች በቀላሉ ሊያገኝ ስለሚችል ጥናቱ ከታሰበለት ግብ እንዲደርስ ጉልህ ድርሻ ሊኖረው ይችላል ከሚል እሳቤ፤ ሶስተኛውና የመጨረሻው ምክንያት ደግሞ በክልሉ የሚገኙትን ትምህርት ቤቶች በሙሉ በጥናቱ ለማካተት በገንዘብ፤ በጊዜና ወዘተ በመሳሰሉት ምክንያቶች ለአጥኚው አዳጋች በመሆኑ የመቀሌ ልዩ ዞንና ደቡብ ዞን በዚህ ጥናት ተካተዋል። በተመረጡት ሁለት ዞኖች ውስጥ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ተለይተው ተመሳሳይ መጠን ባላቸው ወረቀቶች ከተፃፉ በኋላ በተራ የእጣ ናሙና ስልት አራት ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል። ተራ የእጣ ናሙና ስልት የተመረጠበት ምክንያት በዞኑ ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች እኩል የመመረጥ እድል ሊያገኙ ይችላሉ ከሚል እሳቤ ነው።

### 3.2.3 የመምህራን የናሙና አመራረጥ

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በተራ የእጣ ናሙና ስልት መሰረት ከተመረጡት አራት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ (ተተኳሪ መፅሃፉ) ሲያስተምሩ የነበሩና በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራን ቁጥር መጠነኛ በመሆኑ፤ መምረጥ ሳያስፈልግ ሁሉም (11) መምህራን የተዘጋጀውን የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደረጓል። የአማርኛ መምህራን ላይ ብቻ ማተኮር ያስፈለገበት ምክንያት አስተማሪዎቹ በመማሪያ መጽሃፉ አስተምረው የነበሩና እያስተማሩበት ያሉ በመመሆኑ ከሌሎች መምህራ ይልቅ አስተማማኝ መረጃ ሊገኝ ይችላል ከሚል እሳቤ ነው።

### 3.2.4 የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ

በትግራይ ደቡብ ዞን በተመረጡት አራት ትምህርት ቤቶች ሃያ አራት የስምንተኛ ክፍል ምድቦች ያሉ ሲሆኑ በነዚህ ምድቦች ውስጥ 786 ወንዶች፣ 687 ሴቶች በድምሩ 1473 ተማሪዎች ይገኛሉ። አጥኚው ከነዚህ ተማሪዎች ውስጥ 13.5% የሚሆኑትን ለናሙናነት ለመምረጥ ባሰበው መሰረት በስርዓታዊ ናሙና አመራረጥ ስልት (systematic sampling) እንዲመረጡ ተደርጓል። አመራረጡም በመጀመሪያ በየምድቡ የሚገኙ ተማሪዎች ዝርዝር ከክፍል ሃላፊ መምህራን ከተወሰደ በኋላ በስም መቆጣጠሪያ ዝርዝር ላይ ስምንት ስምንት ቁጥር በመዝለል ተመዝግበው የሚገኙትን ተማሪዎች በመውሰድ ተከናውኗል። በዚህ መሰረት ለምሳሌ ፦ በአንድ ምድብ 60 ተማሪዎች ቢኖሩ በስም

መቆጣጠሪያው ዝርዝር ላይ በተራ ቁጥር 1፣8፣16... 56 ቁጥሮች ላይ የተመዘገቡ ስምንት ተማሪዎች ተመርጠዋል ማለት ነው ከዚህ አንፃር ከአንድ ምድብ ከሚገኙ ተማሪዎች በመቶኛ ያለው ድርሻ (8/60 X 100)= 13.33% ነው። በዚህ ናሙና አመራረጥ ስልት ተማሪዎችን መምረጥ ያስፈለገበት ምክንያት ናሙናው ሁሉንም አይነት ተማሪዎች ሊያካትት ይችላል ተብሎ ስለሚታመን ነው።

## 3.3 መረጃ መሰብሰቢያ መሳርያዎች

ለዚህ ጥናት የሚፈለገው መረጃ የተሰበሰበው በዋነኝነት ለ8ኛ ክፍል ከተዘጋጀው መማሪያ መጽሃፍ በተደረገ ሰነድ ፍተሻ ሲሆን በደጋፊነት ደግሞ በመምህራንና በተማሪዎች የተሞላ የጹሁፍ መጠይቅ እንዲሁም መጽሃፉን ካዘጋጁት ባለሙያ ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ተጨማሪ መረጃዎች በማሰባሰብ ነው።

### 3.3.1 የሰነድ ምርመራ

አሁን በስራ ላይ ያለው የትግራይ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ለዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ምንጭ ነው። መጽሐፉ ስለቃላት ትምህርት ያነሳቸው ነጥቦች በዝርዝር ተመርምረዋል። በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ በክለሳ ድርሳናት ከተነሱት ንድፈ ሃሳቦች መነሻ በማድረግ ተተንትኗል።

### 3.3.2 የመምህራን የጹሁፍ መጠይቅ

የቃላት ትምህርት አቀራረብ በተመለከተ የተለያዩ ጸሐፍትን ለምሳሌ፡- Pikulski እና Templeton (2004)፣ Harmer (1991)፣ Gairns እና Redman(1986) ወዘተ. ንድፈ ሃሳብ መነሻ በማድረግ የጹሁፍ መጠይቅ ለማዘጋጀት ተሞክሯል ። የተዘጋጁት ጥያቄዎች ሁለት መሰረታዊ ክፍሎች አሏቸው የመጀመርያው ክፍል የተጠያቂዎች የግል ሁኔታ (ዳራዊ መረጃ) የሚቃኝ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የመጽሃፉ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፤ አቀራረብና አደረጃጀት የሚፈትሹ ጥያቄዎች ቀርበዋል።

እነዚህን ሁለት ክፍሎች አካቶ የተዘጋጀውን የጹሁፍ መጠይቅ አቀራረብ ሁለት መልክ አለው አንደኛው ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አራት አማራጮች አንዱን በመምረጥ

እንዲመልሱ የሚጋብዝ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተጠኝዎች ለመረጡት መልስ (ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች) አስተያየታቸውን የሚያሰፍሩባቸው ክፍት ቦታዎች ይገኛሉ። በዚህም በ "Likert scale" ባስቀመጣቸው አምስት ደረጃዎች አራቱን (በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ አልስማማምና ጨርሶ አልስማማም) በሚል የቀረቡ 37 ጥያቄዎች ደረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል። ከነዚህ አማራጮች ውስጥ "ለመወሰን ያስቸግረኛል" የሚል አምስተኛ አማራጭ አልተካተተም። ምክንያቱም ማረው(1987) Wens and straton (1980:150) ጠቅሰው እንደገለፁት የመጠይቆች መልስ መወሰኛ ነጥብ ሙሉ ቁጥር እንዲሆን ያስፈለገበት ምክንያት የመጠይቁን ጠቀሜታ ባለመረዳት ወይም በመሰላቸት ወይም በግደሌሽነት የተነሳ የበርካታ መላሾች ምርጫ አልወሰንኩም ወይም እርግጠኛ አይደለሁም ወይም አላውቅም ወደሚለው አማራጭ እንዳያመዝን በመስጋት ነው።

ጥያቄዎቹ በዚህ ሁኔታ ከተዘጋጁ በኋላ የጥያቄዎቹን ተገቢነት፤ አሰተማማኝነት ፤ግልጽነት፤ ቅደም ተከተል አጠባበቃቸውንና ወዘተ ለመገምገም ሁለት አማርኛን በማስተማር ዘዴ (TEAM) የተመረቁ መምህራን አስተያየት እንዲሰጡ ተጠይቀዋል። በተጨማሪም ሶስት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መጠይቁ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል። ከሁሉም መምህራን የተገኙትን ገንቢ አስተያየቶች መነሻ በማድረግም መጠይቁ እንደገና ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል ።በዚህም መሰረት በጥያቄዎች ቅደም ተከተል የአጠየያቅ ስልት ለውጥ ተደርጓል ። ከጥናቱ ርእሰ ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸውን ጥያቄዎች ተቀንሰዋል። በዚህ ሁኔታ ከተዘጋጁ በኋላ ለዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት እንዲውሉ ከመደረጋቸው በፊት የጥያቄዎች ዝርዝር ለአማካሪ ቀርበዋል።

### 3.3.3 የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ

ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙትን ምላሾች ለማመሳከር ይቻል ዘንድ ለናሙና በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ ተማሪዎች ተመሳሳይ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በመጀመሪያው የሙከራ ጥናት (Pilot Study) ከመምህራን የተገኙት መረጃዎች መሰረት በማድረግ ለተማሪዎችም ሁለት ክፍሎች ያሉት የጹሁፍ መጠይቅ ተዘጋጅቷል ። የመጀመሪው ክፍል ልክ እንደመምህራን መጠይቅ የግል ሁኔታን (ዳራዊ መረጃ) የሚዳስስ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የተተኳሪ መጽሃፉ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ

አቀራረብና አደረጃጀት የሚዳሰሱ ጥያቄዎች የያዘ ነው። ተማሪዎች መጠይቁ እንዲሞሉ የተጠየቁት በሊከርት (Likert Scale) ስኬል መሰረት አራት የነጥብ መልስ መስጫ መለክያ አማራጮች ቀርበውላቸው ነው። ይኸውም "በጣም እሰማማለሁ"፤ "እስማማለሁ"፤ "አልሰማማም" እና "በፍጹም አልሰማማም" ከሚሉት አማራጮች ውስጥ ተማሪዎች መርጠው የሚያምኑበትን ከቀረቡላቸው ጥያቄዎች አንጻር እንዲያመለክቱ በሚደረግ ነው። በመሆኑም አጥኚው ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ትልቅ ድርሻ ይኖራቸዋል ብሎ ያመነባቸውን አማራጮች በጹሁፍ መጠይቁ አቅርቧል ።

### 3.3.4 የባለሙያ ቃለመጠይቅ

የትግራይ 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ አዘጋጅ ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጓል። ቃለመጠይቁ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት አዘጋጁ መጽሐፉን ባዘጋጁበት ወቅት የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ የተጠቀሙባቸው መስፈርቶች፤ የቃላት ማቅረቢያና ማደራጃ መንገዶች ለመለየት ነው።

መጠይቆቹ ውስጥ የተካተቱ ጥያቄዎች በሙሉ በክለሳ ድርሳናት የቀረቡትን ንድፈ ሃሳቦች መሰረት በማድረግ በአጥኚው የተዘጋጁ ናቸው። የጥያቄዎቹን ጥራትና ብቃት ለማረጋገጥ በሁለት የ "Applied Linguistic for Teaching Amharic" ሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ከተገመገሙ በኋላ በአማካሪ ታይተው አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል። በተሰጠው አስተያየት መሰረትም አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎባቸው ስራ ላይ ውለዋል።

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ይህ ጥናት በሰነድ ፍተሻ ከመምህራንና ተማሪዎች በጹሁፍ መጠይቅ እንዲሁም ከባለሙያ በቃለ መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች ገምግሞ ይተነትናል ። ዝርዝር ሂደቱም በመማሪያ መጽሃፉ የቀረቡትን የቃላት ትምህርት አመራረጥ፣ አቀራረብ አደረጃጀት በቅድሚያ ተለይተው ይወጣሉ። እነዚህም ይዘቶች በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ ምን ያህል ትኩረት እንደተሰጣቸው ከተበተነው የጹሁፍና የቃል መጠይቅ የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ እንደየ ቅደም ተከተላቸው ተቀምጠዋል። በመጨረሻም በጥናቱ የተገኙ ውጤቶች በመግለጽ ተጠናቅቋል። እንዲሁም በተተኳሪ መጽሃፍ ውስጥ የመጽሃፉ ጥራት በመቀነስና የትምህርቱ ዓላማ ስኬት የሚፈታተኑ ተለውጦችን በመጠቆምና ችግሮችን የሚቀረፉበትን የመፍትሂ ሃሳቦች ለመሰንዘር ተሞክሯ

# ምእራፍ አራት

## የጥናቱ ውጤት ትንተና እና ማብራሪያ

የዚህ ምእራፍ ትኩረት ደግሞ የጥናቱ አላማ ከግብ ለማድረስ ተግባራዊ በሆኑት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙትን መረጃዎች እየተነተኑ የተገኘውን ውጤት ከነማብራሪያው ማቅረብ ነው። ለመረጃ አቀራረብና አተናተን ያመች ዘንድ ምእራፍን በሁለት ንኡሳ ክፍሎች ከፍሎ ለማየት ይሞከራል።

በመጀመሪያው ንኡስ ክፍል የመማሪያ መጽሐፉ አጭር ቅኝት፣የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም በቃለ መጠይቁ የተሳተፉ የትምህርት ባለሙያ ዳራ ይቀርባል። በሁለተኛው ንኡስ ክፍል ደግሞ በመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አመራረጥ፣ አደረጃጀት፣ አውዳዊ አቀራረብ፣ የእርባታና የምስረታ ሂደት የክሂሎች ትምህርት ጥምረት፣ በመዝገበ ቃላት የተደገፉ የቃላት ትምህርት አቀራብና ለቃላት ትምህርት የቀረቡ መመሪያዎች አነዳደፍ በተገኙ መረጃዎች እየተጣቀሱ በቅደም ተከተል ተተንትኖ ቀርቧል።

### 4.1 ተተኳሪ መጽሐፉ

የትግራይ ክልል የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1990 ዓ.ም በድጋሚ በ2001 ዓ.ም በስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ፣ ጥናትና ምርምር መምሪያ አማካኝነት ተዘጋጅቶ ታትሟል። መጽሐፉ 273 ገጾች ያሉት ሲሆን፣ በውስጡም በተለያዩ ርእሰ ጉዮች ላይ ያተኮሩ 19 ምንባቦች ይዟል። እያንዳንዱ ምንባብ መልመጃ አንድ፣መልመጃ ሁለትና መልመጃ ሶስት በሚሉ ክፍሎች ቀርቧል። የመልመጃዎቹ አቀራረብ አንብቦ መረዳት፣መጻፍ፣ ማዳመጥ፣ መናገር፣ ስነልሳንና ስነጽሑፍን በቅደም ተከለት ይዘዋል። ከስድስቱ ይዘቶች በተጨማሪ የቃላት ትምህርት ይዘት ራሱን ችሎ በመፅሐፉ ቀርቧል። ይህ ይዘት በመጽሐፉ ውስጥ በብዛት ተካቶ የሚገኘው በአንብቦ መረዳትና በመጻፍ ክሂል መልመጃዎች ስር ነው። በአጠቃላይ በመጽሐፉ የቀረቡትን መልመጃዎች በሚከተለው ሠንጠረዥ እንመልከት።

ሰንጨረዥ 1፦ የትግራይ ክልል ስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በየምዕራፉ በሚገኙ መልመጃዎች ስር የቀረቡ ተግባሮች ዝርዝር በጥቅሉ፡

| ምዕራፍ | የተግባር ብዛት | | | | | | አጠቃላይ በመፅሐፉ የሚገኙ ተግባራት ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መልመጃ አንድ | | መልመጃ ሁለት | | መልመጃ ሶስት | | | |
| | ቃላት | ሌላ | ቃላት | ሌላ | ቃላት | ሌላ | ቃላት | ሌላ |
| 19 | 5 (2.4%) | 32 (15.2%) | 126 (59.9%) | 29 (13.7%) | - - | 19 (9%) | 131 62.4%) | 79 (37.6% |

ከሠንጠረዥ 1 ማስተዋል እንደማቻለው፣ በመማሪያ መፍሐፉ ውስጥ ከተካተቱት መልመጃዎች መጠን አኳያ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘው የቃላት የትምህርት ነው። ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የቃላት ትምህርት በአንብቦ መረዳትና በመጻፍ ክሂል መልመጃዎች (1 እና 2) ስር ተካቶ በመቅረቡ የመልመጃዎቹ ቁጥር ከሌሎቹ ተግባራት ጎላ ብሎ ታይቷል። በመሆኑም ካሉት ተግባራት 62.4% በመያዝ ቀዳሚ ሲሆኑ ለሌላ የቀረቡ መልመጃዎች (ተግባራት) ደግሞ 37.6% በመያዝ በሁለተኛ ደረጃ ይገኛሉ። በመሆኑም የቃላት ትምህርት ተግባራት ከሌሎች አንጻር ሲታይ ከግማሽ በላይ የሚሆነውን ቦታ ይዘዋል።

## 4.2 የናሙና መምህራን፣ተማሪዎችና የመጽሐፉ አዘጋጆች ዳራ

### 4.2.1 የናሙና መምህራን ዳራ

ሠንጠረዥ 2፡- የናሙና መምህራኑን ዕድሜ፣ፆታ፣ የሰለጠኑበት ትምህርት፣ የትምህርት ደረጃና አገልግሎት ዘመን በቁጥር እና በመቶኛ የሚገልጽ ሰንጠረዥ

| ዕድሜ | | | ፆታ | | የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት | | | | | | የትምህርት ደረጃ | | | 8ተኛ ክፍል ያስተማሩበት አመት/አመታት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | አብይ | | | ንኡስ | | | | | | | | |
| 25-34 | 35-44 | 45-54 | ወንድ | ሴት | አማርኛ | እንግሊዝ | ትግርኛ | እንግሊዝ | ትግርኛ | ሌላ | ሰርተፊኬት | ዲፕሎማ | የመጀመሪያ ዲግሪ | 1-10 | 11-20 | ከ20 በላይ |
| 2 (18.9%) | 7 (63.6%) | 2 (18.9%) | 7 (63.6%) | 3 (27.4%) | 11 (100%) | - - | - - | 9 (81.8%) | 2 (18.9%) | - - | - - | 9 (81.8%) | 2 (18.9%) | 1 (9.1%) | 8 (72.7%) | 2 (18.9%) |

ሠንጠረዥ 2 እንደሚያመለክተው መጠይቁን የሞሉት መምህራን ከ25-34 (18.9%)፣ ከ35-44 (63.6%)፣ ከ45-54 (18.9%) ዕድሜ ያላቸው ናቸው። ከፆታ አኳያ ደግሞ 63.6% ወንዶች፣ 27.4% ሴቶች ናቸው። ከሰለጠኑት አብይ የትምህርት ዘርፍ አንጻርም 100% በአማርኛ የትምህርት መስክ ተመርቀዋል። ስምንተኛ ክፍል ካስተማሩበት ዘመን አንጻር ደግሞ ከ1-10(9.1%)፣ ከ11-20(72.7%)፣ ከሃያ አመታት በላይ (18.9%) የአማርኛ ቋንቋ አስተምረዋል።

እንዲሁም የመምህራኑ የትምህርት ደረጃ አብዛኞቹ 9(81.8%) ዲፕሎማ፣ ጥቂቶች 2(18.9%) ደግሞ የመጀመሪያ ድግሪ ያላቸው ናቸው። መምህራኑ ካላቸው የረዥም ጊዜ የሥራ ልምድ፣ የሠለጠኑበት አብይ የትምህርት መስክ አማርኛ ቋንቋ በመሆኑ እና የትምህርት ደረጃቸውም ቢሆን ለተተኳሪ የክፍል ደረጃ የሐገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ ካስፈረው ተፈላጊ የትምህርት ችሎታ ጋር የሚስማማ ሆኖ ተገኝቷል።

### 4.2.2 የናሞና ተማሪዎች ዳራ መግለጫ

ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ በተጨማሪ፣ ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችም ተመሳሳይ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ልክ እንደመምህራኑ ለተማሪዎችም የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ ሁለት ክፍሎች እንዳሉት በምእራፍ ሶስት ተገልጿል። በመጀመሪያው ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን አጠቃላይ ሁኔታ ማለትም ዕድሜ፣ፆታ፣ የተማሪ ብዛት ወዘተ. ቀጥሎ የሚዳሰሱ ናቸው። በሁለተኛው ክፍል የቀረቡ ጥያቄዎች ደግሞ አስፈላጊ በሆኑበት ቦታ እየተጠቀሱ ይተነተናሉ።

ሠንጠረዥ 3፡- የናሙና ተማሪዎች ሁኔታ መግለጫ

| ብዛት | ፆታ | | | አፍ መፍቻ ቋንቋ | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ትግርኛ | አማርኛ | ሌላ | |
| በቁጥር | 117 | 83 | 200 | 200 | - | - | 200 |
| በ% | 58.5 | 41.5 | 100 | 100 | - | - | 100 |

መጠይቁን ሞልተው ከመለሱት ሁለት መቶ ተማሪዎች ውስጥ117(58.5%) ወንዶች ሲሆኑ 83(41.5%) የሚሆኑት ደግሞ ሴቶች ናቸው። የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በተመለከተም በጥናቱ የተካተቱ ተማሪዎች 200(100%) ትግርኛ አፍፌት እንደሆኑ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በአጠቃላይ በሰንጠረዥ 3 እንደሚስተዋለው በጥናቱ የታቀፉት ተማሪዎች ከፆታ አኳያ ሲታይ ሁለቱም ፆታዎች በተመሳሳይ ሁኔታ የተወከሉበት ነው ማለት ይቻላል። እንዲሁም የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተመለከተ በጥናቱ የተካተቱ ተማሪዎች በሙሉ በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን እንደፈቱ በሰንጠረዥ የቀረበው ስሌት ያሳያል። ይህም ለሁሉም ተማሪዎች አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው መሆኑን ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል።

### 4.2.3 የመጽሐፉ አዘጋጅ ዳራ

የትግራይ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ያዘጋጁትን ባለሙያ በአካል አግኝቶ ማነጋገር ተችሏል። በቃለ መጠይቅ ቁጥር አንድና ሁለት ስለመጽሐፍ አዘጋጁ የግል ሁኔታ ጥያቄ ቀርቦላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል። መጽሐፍ አዘጋጁ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ትግርኛ ሲሆን በአማርኛ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ፣ በስርአተ ትምህርት ዝግጅት ሁለተኛ ዲግሪ አላቸው። ዘጠኝ አመት በመምህርነት፣ አስራ ስምንት አመት በስርአተ ትምህርት መሳሪያዎች ዝግጅት ስራ አገልግለዋል። በአሁኑ ጊዜ በክልሉ የቋንቋ ስርአተ ትምህርት ዝግጅት ስር የተለያዩ ስርአተ ትምህርት መሳሪያዎች ዝግጅት ስራ እየሰሩ የሚገኙ ባለሙያ ናቸው።

አዘጋጁ ተተኳሪ መጽሐፉ ከማዘጋጀታቸው በፊት በሌላ የትምህርት ማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ተሳትፌው ያውቁ እንደሆነ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። ባለሙያው በ1985 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ለመከላከያ ሰራዊት የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ለጎልማሶች እንጂ ለህፃናት ማስተማሪያነት እንደማይውሉ በአረጋገጠው ግምገማና በመጋቢት ወር ከ1ኛ-6ኛ ክፍል አማርኛ የአፍ መፍቻቸው ለሆኑ ተማሪዎች በተካሄደው የመማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት እንደተሳተፉ ገልፀዋል። በ1986 ዓ.ም አዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ከወጣ በኋላ በተካሄደው መርሃ ትምህርት ቀረፃ ላይ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ በዋና አዘጋጅነት እና ለሁለተኛ ቋንቋ በአርታኢነት የቋንቋ ትምህርት ባለሙያ (expert) በመሆን እንደሰሩ ገልጸው፣ ከዚህ በተጨማሪም የእንግሊዝኛ፣ የአማርኛ እና የኅብረተሰብ ትምህርት ዝግጅት ክፍል አስተባባሪ (Panel co-coordinator) በመሆን በፌዴራል "Flow-chart" ዝግጅት በ1987 ዓ.ም መርሃ ትምህርት በማጽደቅ፣ ቀጥሎ በሙከራ ስርአተ ትምህርት ዝግጅት በሂደት የአንደኛና የአምስተኛ፣ የሁለተኛና የስድስተኛ፣ የሶስተኛና የሰባተኛ፣ እንዲሁም የአራተኛና የስምንተኛ ክፍሎችን አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በማዘጋጀት እንደተሳተፉ ገልጸዋል።

ተተኳሪ መጽሐፉ አዘጋጅ ዳራ የሚያመለክተው፣ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመጀመሪያ ድግሪ፣ በስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ሁለተኛ ድግሪ ያላቸው፣ ባጠቃላይ

እንዲሁም በመምህርነት፣ በስርአተ ትምህርት መሳሪያዎች ዝግጅት የረዥም ጊዜ አገልግሎት ያላቸው በመሆኑ አዘጋጁ ለስራው ብቃት ያላቸው መሆኑን ያመለክታል።

## 4.3 የቃላት አመራረጥን የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ቃላት በይዘታቸው ይሁን በቅርጻቸው የተማሪዎች አቅም፣ ባህልና ማህበራዊ ዳራ ያገናዘቡ መሆን አለባቸው። ትምህርቱ ለደረጃው የተዘጋጀውን መረሐ ትምህርት ያማከለ፣ የትምህርትንና የቋንቋ ሳይንስን መሠረት ያደረገና በጥናት በተደገፉ የመምረጫ መሥፈርቶች አማካኝነት የተከናወነ ከሆነ ተፈላጊውን ውጤት ያስመዘግባል። በመሆኑም ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላትን በመምረጥ ረገድ ጠቃሚ ከሆኑት መመዘኛዎች መካከል የድግግሞሽ መጠን፣ ባህላዊ እሴትን መጠበቅ፣ የስርጭት ሽፋን፣ የፍቺ ሽፋን፣ ተስተማሪነት፣ በቅርብ መገኘትና የተማሪው ፍላጎት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚህ አንፃር በተተኳሪ መጽሐፉ የሚገኙት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የተመረጡባቸው መስፈርቶች መነሻ ምን እንደነበር አዘጋጁ እንዲገልፁ በቃለ መጠይቅ በተራ ቁጥር 3 ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር።

ቃላትን መርጦ ለትምህርትነት ለማቅረብ በዋነኝነት እንደመነሻ የተጠቀሙበት ሰነድ በፌደራል ለደረጃው የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት እንደሆነ ገልፀዋል። እንደ ባለሙያው ገለጻ፣ በመርሃ ትምህርቱ አማካኝነት አስቀድሞ ይዘቱ ተወስኖ ስለሚመጣ ከዚያ ውጪ መውጣት አይቻልም፤ ነገርግን እንደሁኔታው ማስፋት ይቻላል። በተጨማሪም ቀደም ሲል በደርግ ጊዜ ያገለግሉ ከነበሩ የመማሪያ መፃሕፍት አስፈላጊ መረጃዎችን እንደወሰዱ ባለሙያው ተናግረዋል።

በተጨማሪም ከተለያዩ የልቦለድና ሌሎች መፃሕፍት፣ መጽሔቶች፣ በሌላ ቋንቋ የተሰሩ ስራዎችን ወደ አማርኛ በመተርጎም፣ ከጋዜጦች ወዘተ. እንደተጠቀሙ ባለሙያው ገልጸዋል። የተለያዩ ጽሑፎች እንዳሉ በመውሰድ ወይም ለደረጃው በሚመጥን መልኩ በማሻሻል፣ ለምሳሌ፡- አላስፈላጊ ቃላትን በማስወጣት፣ ከባድ ቃላትን በመጣኝ ቃላት በመተካት እና ሌሎች ማሻሻያዎችን በማድረግ፣ እንደተጠቀሙ አስረድተዋል። በመሆኑም አዘጋጁ ለቃላት ትምህርት መረጣ በዋናነት በአገር አቀፍ ደረጃ ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው መርሃ ትምህርት፣ አጠቃላይ የአገሪቱን የትምህርት ፖሊሲ መሰረት አድርገው በወጡ የተለያዩ

መመሪያዎች፣ በተለያዩ የታተሙና ያልታተሙ ጽሑፎች ላይ በመመስረት የቃላት መረጣ እንደተካሄደ ለመረዳት ተችሏል።

ሌላው ለቃላት ምርጫ የተጠቀሙባቸውን መመዘኛዎች እንዲገልፁ በቃለመጠይቅ ጥያቄ ቁጥር አራት ለመፃሐፍ አዘጋጁ ጥያቄ ቀርቦላቸው የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል።

መማሪያ መጽሐፉ ሲዘጋጅ ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላት ከተማሪዎች እድሜና አቅም ጋር ያላቸውን መጣኝነትና ለቃላት ማስተማሪያነት የሚመረጡት ምንባቦች ሳቢነት ግምት ውስጥ እንደገቡ ጠቁመው ምንባቦቹም ለተማሪዎች አካባቢያቸውን ለመገንዘብና ለመግለጽ የሚያስችሉ (ለምሳሌ እንደታዋቂ ቦታዎች፣ ቅርሶች፣ የዱር እንስሳት፣ ታዋቂ ሰዎች ወዘተ.) የሚገልፁና ተማሪዎች ከእለት ተዕለት ሕይወታቸው በሚጠቀሙባቸው ቃላት ያተኮሩ ይዘቶችን እንዳካተቱ ገልፀዋል።

ከዚህ በላይ በመጽሐፉ የተካተቱ ቃላት የተመረጡበትን መስፈርት አስመልክቶ ከመጽሐፍ አዘጋጁ የተሰጡ ምላሾች ተጠቃለው ሲታዩ፣ አብዛኞቹ ቃላት የተመረጡት ለደረጃው ከመረጧቸው ምንባቦች ውስጥ መሆኑን፣ የቃላት መረጣው የተከናወነው በልምድና በትምህርት ያካበቱትን እውቀት በመመርኮዝ እንደሆነና ከትምህርት ፖሊሲው ጋር የሚስማሙ መመሪያዎችን መሰረት እንዳደረጉ ለመገንዘብ ተችሏል። የተተኳሪ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥን በተመለከተ መጽሐፉን ለማዳሰስ ተሞክሯል።

የመፃሐፉ ይዘት ለመዳሰስ በተደረገው ሙከራ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት አብዛኞቹ ቃላት ለንባብ ከቀረቡ ጽሑፎች የወጡ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። ይኸውም መጽሐፉ ውሰጥ ባሉት 131 የሚሆኑ የቃላት ትምህርት ተግባራት 85ቱ ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው። እንዲሁም ባሕልን የሚነኩ ከጾታ ጋር የሚጣረሱ ቃላት አልተስተዋሉም። በአንፃሩ መደበኛነት የሚጎድላቸው ለምሳሌ ውድማ፣ ጨበጨበ፣ ፈፋ፣ ወዘተ. አይነት ቃላትና ሐረጋት መኖራቸውን መመልከት ተችሏል።

በሌላ በኩል የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥን የሚመለከቱ ሌሎች መስፈርቶች ለምሳሌ ተስተማሪነት፣ የፍቺ ሽፋን፣ በቅርብ መገኘትና የተማሪዎች ፍላጎት በሚሉት መሰረት ሲፈተሽ፣ በተስተማሪነት ረገድ ከተማሪዎች አቅም በላይ

አይደሉም ማለት ሲቻል ከፍች እና ከቅርብ መገኛት አንጻር ሲታይ ግን የመጽሐፉ ትኩረት አናሳ ሆኖ ተገኝቷል። ይኸውም የቃላት ዘይቤዎችና ፈሊጦች፣ የቃላት አጠቃላይና ዝርዝር፣ የቃላት ፉካሬ እና እማሬ ፍች የተሰጣቸው ትኩረት አናሳ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ለመምህራን ጥያቄ ቀርቦላቸው የማከተለውን ምላሽ ሰጥተዋ።

ሠንጠረዥ 4፦ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የቃላት ትምህርት ይዘቶች ሽፋንና ለደረጃው ስላላቸው መጣኝነት ለቀረቡ ጥያቄዎች በመምህራን የተሰጠ መልስ፡

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ መልሶች* | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 4 | 3 | 2 | 1 | |
| 1 | ከሌሎች የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች አንጻር ሲታይ መጽሐፉ ለቃላት ትምህርት በቂ ሽፋን ሰጥቷል። | በቁጥር | - | 9 | 2 | - | 11 |
| | | በ% | - | 81.8 | 18.2 | - | 100 |
| 2 | የመጽሐፉ የቃላት ትምህርት ይዘት የክፍልደረጃውን አይመጥንም | በቁጥር | 1 | 2 | 8 | - | 11 |
| | | በ% | 9 | 18.2 | 72.7 | - | 100 |

*መግለጫ

4. በጣም እስማማለሁ 2. አልስማማም

3 እስማማለሁ 1- በፍጹም አልስማማም

በሰንጠረዥ 4 እንደተመለከተው፣ ከሌሎች የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች አንጻር ሲታይ መጽሐፉ ከቁጥር አንፃር ለቃላት ትምህርት በቂ ሽፋን ሰጥቷል ለሚለው መጠይቅ 9(81.8%) ሲስማሙ 2(18.2%) ደግሞ አልተስማሙም። እንዲሁም በመጽሐፉ የቃላት ትምህርት ይዘት የክፍል ደረጃውን አይመጥንም ለሚለው 1(9.1%) በጣም እስማማለሁ፣ 2(18.2%) እስማማለሁ፣8(72.7%) ደግሞ አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። ከመምህራኑ ምላሽ መረዳት የሚቻለው በመማሪያ መጽሐፉ ለቃላት ትምህርት የተሰጠው ሽፋን በቂ እንደሆነና ለክፍል ደረጃው መጣኝ እንደሆነ አብዛኞቹ መምህራን የተስማሙበት መሆኑ ነው። ይህንን የተመለከተው የሰነድ ምርመራ ውጤትም በጠቅላላው ከቀረቡት 210 መልመጃዎች 131(62.1%) በቃላት ትምህርት ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን አረጋግጧል። በመሆኑም በተተኳሪ መጽሐፉ ለቃላት ትምህርት በቂ ሽፋን እንደተሰጠው መረዳት ይቻላል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ መጽሐፉ ለቃላት ትምህርት የሰጠውን ሽፋንና ለክፍል ደረጃው ስላለው መጣኝነት ለመምህራን ነፃ አስተያየት እንዲሰጡ የሚጋብዝ ጥያቄ ቀርቦላቸው፣ አማርኛ ለተማሪዎቹ ሁለተኛ ቋንቋ እንደመሆኑ መጠን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተፅዕኖ ምክንያትና አካባቢያዊ ድጋፍ አለማግኘታቸው ካልሆነ በስተቀር ሌላ የጎላ ችግር እንዳልገጠማቸው ገልፀዋል።

ይህ የመምህራኑ ምላሽ ከመማሪያ መጽሐፉ አዘጋጅ ጋር በተካሄደው ቃለ ምልልስ ከተገኘው መረጃ ጋር የሚጣጣም ሆኖ ተገኝቷል። ስለዚህ የመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት ይዘት የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ባገናዘበ መልኩ፣ በቂ ትኩረት ተሰጥቶትና ሳይንሳዊ የቃላት መምረጫ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ መሆኑ መረዳት ይቻላል። መጽሐፉ ያካተታቸው ቃላት ለክፍል ደረጃው ያላቸውን መጣኝነት ለመፈተሸ ለተማሪዎች ለቀረቡላቸው ጥያቄ የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 5፡- የመጽሐፉ የቃላት ትምህርት ይዘት ለደረጃው ስላለው መጣኝነት ለቀረበው ጥያቄ በተማሪዎች የተሰጠ መልስ።

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ መልሶች* | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 4፣3 | 2፣1 |
| 4 | በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት የጥምርና የምህፃረ ቃላት ትምህርት አቀራረብ አመሰራረታቸውን ለመረዳት | በቁጥር | 166 | 34 |
| | | በ% | 83 | 17 |

*መግለጫ

4፣3 አዎንታዊ መልስ/ በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ/

2፣1 አሉታዊ መልስ/ አልስማማምና ፈጽሞ አልስማማም/

በሰንጠረዥ 5 እንደተመለከተው መጽሐፉ የቃላት ትምህርት ለደረጃው ስላለው መጣኝነት 166(83%) ያህሉ መላሾች አዎንታዊ 34(17%) ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። ከተማሪዎች የተገኘው መልስ በአመዛኙ አዎንታዊ መሆኑ ቀደም ሲል

ከመጽሐፍ አዘጋጁ፣ ከመምህራኑና ከሰነድ ፍተሻው ከተገኘው ውጤት ጋር የሚስማማ ሆኖ ተገኝቷል።

## 4.4 የቃላት ትምህርት አደረጃጀት

በምዕራፍ ሁለት 2.4 እንደተገለፀው፣ የአዳዲስ ቃላት አቀራረብ ክትትሎሽና መጠነ ርእይ ውሳኔዎች የሚመሰረቱት በስነልሳናዊና በስነትምህርታዊ እሳቤዎች እንዲሁም ባለው የመማር ማስተማር ሁኔታ ግንዛቤ ላይ እንደሆነ ይታወቃል። ከዚህ አንፃር ቃላት በጥንቃቄ በሚታቀዱ ተከታታይ ደረጃዎች፣ ተስማሚ በሚሆኑበት ስልትና ያለውን ተጨባጭ የመማር ማስተማር ሁኔታ ባገናዘበ መንገድ መደራጀት ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ተገቢ የቃላት መምረጫ መስፈርቶችን በመጠቀም ለአንድ ደረጃ እንዲመጥኑ ሆነው የተመረጡ ቃላት ባንድ ላይ ለማደራጀትና በመልመጃ መልክ ለመንደፍ የሚያስችሉ የተለያዩ የማደራጃ ስልቶች እንዳሉ በመዕራፍ ሁለት ተገልጿል። ከነዚህ መሃል ርእስ ጉዳይን፣ ፍችን፣ የአወቃቀር ቅርፅን፣ አውዳዊ ዝምድናን መሰረት በማድረግ ማደራጀት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ከዚህ በተጨማሪም ቃላትን እንደአስፈላጊነቱ በቃል ክፍላቸው፣ በዲስኩር አያያዥነታቸው፣ በድርብ ቃልነታቸው፣ በፈሊጥነታቸው፣ ወዘተ. ማደራጀት ለቃላት ትምህርት ስኬት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው።

እንዲሁም የቃላት ትምህርት አደረጃጀት የመማር እድገቱን የጠበቀና ትርጉም ያለው ሊሆን ይገባል። ይኸውም አደረጃጀቱ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ፣ በከፍተኛ ሁኔታ ከሚደጋገሙ ወደ ዝቅተኛ ሁኔታ ወደሚደጋገሙ ቀስ በቀስ የሚሄድ መሆን ይኖርበታል። ከዚህ አንፃር የተተኳሪ መጽሐፍ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ለመፈተሽ ሲባል መጽሐፉ አዘጋጁ በቃለ መጠይቅ ጥያቄ ቁጥር 5 "ቃላቱን ለማደረጃት የተጠቀማችሁበት መስፈርት ምን ነበር" የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው፣ ቃላቱን ለማደረጃት የተጠቀሙበትን መስፈርት አንድ ሁለት ብለው ሊያነሱ እንደማይችሉ ነገር ግን አደረጃጀቱ በቻለ አቅም ከቀላል ወደ ከባድ ለምሳሌ ከሁለት ሆሄያት የሚመሰረቱ ቃላትን በማስቀደም፣ ቀጥሎ ከሶስት ሆሄያት ከዚያም ከአራት ሆሄያት የመሚመሰረቱትን በሂደት በማቅረብ ወይም አንድ ፍቺ፣ ሁለት ፍቺ ወዘተ በማድረግ ለማደራጀት እንደሞከሩ ገልፀዋል።

በተጨማሪ ቃላቱን ከተለያዩ ክሂሎች ስር ከሚገኙ መልመጃዎች ጋር ለማገናኘትና ለማዛመድ እንደሞከሩ ገልፀው፤ በአንብቦ መረዳት ጥያቄ ስር የቃላት ጥያቄዎችም እንደአሉ ጠቁመዋል። ለምሳሌ አንድ አረፍተነገር በመውሰድ አረፍተነገሩ ውስጥ የሚገኝ አንድ አዲስ ቃል መስመር ይደረግበትና የዚያን ፍቺ ምን እንደሆነ ተማሪዎች እንዲመልሱ ይደረጋል።

ከመጽሃፍ አዘጋጁ ገለጻ መረዳት የሚቻለው መጽሐፉ ውስጥ ቃላት ተደራጅተው የቀረቡበት ዋና የማደረጃ ስልት ቃላት በሚያወሱት ርእሰ ጉዳይ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። በምዕራፍ ሁለት ተራ ቁጥር 2.4.1 እንደተገለፀው፣ የቃላት ትምህርት ስፋትና ጥልቀቱን የጠበቀ እንዲሆን ተከታታይነት ሊኖረው ይገባል። እንዲሁም ቃላት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለደረጃው ይመጥናሉ ተብለው በተመረጡ ነጠላ ቃላት በመጀመር ቀስ በቀስ መደበኛ ሃረጋትንና ፈሊጦችን በማቅረብ ከቀላል ወደ ከባድ በመሄድ ማደራጀት ተገቢ ነው። ከዚህ አንፃር አዘጋጁ ተገቢ የሆነ የአደረጃጀት መንገድ እንደተከተሉ መረዳት ይቻላል። በመሆኑም መጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ጠንካራ ጎን እንዳለው ጥናቱ ያመለክታል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የተተኳሪ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል። በመሆኑም መጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ተማሪዎች የቃላትን ፍቺ እና ንበት በገቡበት አውድ ውስጥ ተመርኩዘው እንዲለዩ የሚያደርጉ መልመጃዎችን አካቷል። ይህም የቃላቱን ፍችና ንበታዊ ባህሪያት በአውድ አስደግፎ ማቅረቡ፣ተማሪዎች ቃላቱን ለመጠቀም በሚፈልጉበት ጊዜ የአጠቃቀም ባህሪያቸውን አስቀድመው እንዲገነዘቡ የሚያደርግ ነው። (አባሪ "ሀ" አስረጅ አንድንና ሁለትን ይመልከቱ)።

እንዲሁም በመጽሐፉ ተማሪዎች ለተሰጧቸው ቃላት ፍች ሊሆን የሚችለውን ቃል እንዲመርጡ የሚጠይቁ መልመጃዎች ይገኛሉ። የመልመጃዎቹ አቀራረብ ከመጀመሪያ ያሉት ቃላት ፍቻቸውን በሚወስን አውድ ስላልገቡ በአማራጭነት ከቀረቡ ሌሎች ቃላት ጋር ያላቸውን የፍች ተመሳስሎ መኖርና አለመኖሩ በጥልቀት መመርመር ስለሚያስፈልጋቸው ውስብስብነቱ ይለያያል። ይህም በምዕራፍ ሁለት 2.4.2 "ተማሪዎች በመጀመሪያ የቃላትን ፍችና የፍች አካባቢ ከመማራቸው በፊት ቅርፃቸውን ማየት፣

ቃላቱን በአንደበታቸው መጥራትና መፃፍ ይኖርባቸዋል" በማለት ከተገለጸው ሃሳብ ጋር ይገናኛል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ምን እንደሚመስል ለመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሰንጠረዥ 6፡- ስለመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ለቀረቡ ጥያቄዎች በመምህራን የተሰጡ ምላሾች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3 | የመጽሐፉ የቃላት ትምህርት፥ | | | | | |
| 3.1 | ቃላቱን የሚያወሱት ርእሰ ጉዳይ ያገናዘበ ነው | በቁጥር | 3 | 6 | 2 | - |
| | | በ% | 27.3 | 54.5 | 18.2 | - |
| 3.2 | ከቀላል ወደ ከባድ የሚሄድ ነው | በቁጥር | 3 | 7 | 1 | - |
| | | በ% | 27.3 | 63.6 | 9 | - |
| 3.3 | የቃላቱን ቅርፃዊ ባህሪ ያገናዘበ አይደለም | በቁጥር | 2 | 5 | 4 | - |
| | | በ% | 18.2 | 45.5 | 36.5 | - |
| 3.4 | የቃላቱን አውዳዊ ዝምድና ያገናዘበ ነው። | በቁጥር | 3 | 4 | 5 | |
| | | በ% | 27.3 | 36.4 | 45.5 | |

በሰንጠረዥ 6 ላይ እንደሚታየው ለጥያቄ ተራ ቁጥር 3.1 ምላሽ ከሰጡ መምህራን 9(81.8%) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 2 (18.2%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህ የሚጠቁመው የመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ቃላቱን በሚያወሱት ርእስ ጉዳይ ያገናዘበ መሆኑን ነው። እንዲሁም ከጥያቄ 3.2 እስከ 3.4 ቃላትን በማቧደን በአንድ መልመጃ አደራጅቶ የማቅረቢያ ስልቶችን ከመጠቀም አንጻር የመጽሐፉን አደረጃጀት ለመገምገም የሚያግዙ ጥያቄዎች ነበሩ። በዚሁ መሰረት አደረጃጀቱ ከቀላል ወደ ከባድ የሚሄድ ነው ለሚለው በመምህራን የተሰጡ ምላሾች፣ አብዛኞቹ 10(90.9%) ሲስማሙበት 1(9.1%) ደግሞ አልተስማሙበትም። የቃላቱን ቅርፃዊ ባህሪ ያገናዘበ ነው ለሚለው 7(63.5%) ሲስማሙበት፣ 4(36.5) ደግሞ አልተስማሙበትም። እንዲሁም አደረጃጀቱ የቃላቱን አውዳዊ ዝምድና ያገናዘበ ነው

ለሚለው ጥያቄ 7(63.5%) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 4(36.5) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

የመምህራኑ ምላሽ የሚያሳየው፣ ቃላትን በሚባደን በመልመጃ አደራጅቶ ከማቅረቢያ ስልቶች አኳያ ሲታይ ቃላቱ የሚያወሱትን ርእሰ ጉዳይ ፣ የቃላቱን የተለየ የፍቺ ገፅታ እና የቃላቱን ቅርፃዊ ባህሪ ተመርኩዞ የማደራጀት ስልቶች ጥሩ መሆናቸውን ነው። በአንጻሩ፣ የቃላቱ አውዳዊ ዝምድና ተሞርኩዞ የማደራጀት ጉዳይ ብዙም ትኩረት እንዳልተደረገበት ከመምህራኑ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ይህ ውጤትም መጽሐፍ አዘጋጁ ከሰጡት መልስ ጋር የሚጣጣም ሆኖ ተገኝቷል።

ከዚህ አንጻር መፅሐፉ ውስጥ ቃላት የተደራጁባቸውን መንገዶች ለመዳሰስ ተሞክሯል። በመሆኑም በመጽሐፉ ውስጥ ቃላት በአብዛኛው በርእሰ ጉዳይ፣ በፍች ዝምድናቸው፣ በቅርፃቸውና በመሳሰሉት ስልቶች አደራጅቶ ለማቅረብ ጥረት እንደተደረገ ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። በሰነድ ፍተሻው የተገኘው ውጤት ለማጠናከር የተተኳሪ መጽሐፉን አጠቃላይ የቃላት አደረጃጀት የተመለከቱ ጥያቄዎች ለተማሪዎች ጥያቄዎች ቀርበውላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሰንጠረዥ 7፦ ስለመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ለቀረቡ ጥያቄዎች በተማሪዎች የተሰጡ መልሶች ፦

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ መልሶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 4፣3 | 2፣ 1 |
| 1 | በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የቃላት ትምህርት መልመጃዎች በአብዛኛው ከእለት ተእለት ህይወት ጋር የተያያዙ ናቸው። | በቁጥር | 174 | 26 |
| | | በ% | 87 | 13 |
| 11 | በመጽሐፉ መጀመሪያ አካባቢ ያሉ ቃላት ወደ መጨረሻ ካሉት ለመረዳት ያስቸግራሉ። | በቁጥር | 120 | 80 |
| | | በ% | 60 | 40 |

በሰንጠረዥ 7 ላይ እንደሚታየው፣ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የቃላት ትምህርት መልመጃዎች በአብዛኛው ከእለት ተእለት ህይወቴ ጋር የተያያዙ ናቸው ለሚለው ጥያቄ አብዛኞቹ 174(87%) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 26(13%) ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። እንዲሁም በመጽሐፉ መጀመሪያ አካባቢ ያሉ ቃላት ወደ መጨረሻ

ከአሉት ለመረዳት ያስቸግሩኛል ለሚለው ጥያቄ 120 (60%) ተማሪዎች አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ አብዛኞቹ 80 (40%) ተማሪዎች ግን አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል።

የተማሪዎቹ ምላሽ የሚያሳየው በመማሪያ መጽሐፉ የተካተቱ ቃላት ቀስ በቀስ ከቀላል ወደ ከባድ በሚሄድ አኳኃንና የተማሪዎችን ግላዊ ፍላጎት ባገናዘበ መልኩ የተደራጁ መሆናቸውን ነው። ይህም McCarten (2007:21) ቃላት በመማሪያ መፃሕፍት ውስጥ በርእሰ ጉዳይ፣ በፍች ዝምድና፣የሰዎችን ግላዊ ፍላጎት፣ የእውናዊ አለም የነገሮች ቡድናና የአውዳዊ ዝምድና ባገናዘበ መልኩ መደራጀት አለባቸው ብለው ከገለፁት ሃሳብ ጋር የሚስማማ ሆኖ ተገኝቷል።

ከተማሪዎች የተገኘውን ውጤት ለማጠናከር ሲባል ለመምህራን የተተኳሪ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት የአደረጃጀት መንገዶችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 8፡- ስለመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት መንገዶች ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ መልሶች፡-

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.5 | በመጽሐፉ መጀመሪያ አካባቢ የተለመዱ ነጠላ ቃላት ቀርበዋል | በቁጥር | 2 | 4 | 3 | 2 |
| | | በ% | 18.2 | 36.4 | 27.3 | 18.2 |
| 3.6 | በመጽሐፉ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ይታይባቸዋል | በቁጥር | 2 | 2 | 4 | 3 |
| | | በ% | 18.2 | 18.2 | 36.4 | 27.3 |
| 3.7 | መጽሐፉ ለትምህርት እርከኑ ከሚመጥኑ ነጠላ ቃላት በመነሳት በጥምርነት ወደሚፈጠሩ ቃላት የሚያመራ አደረጃጀት ስልትን ተከትሏል። | በቁጥር | 2 | 3 | 4 | 2 |
| | | በ% | 18.2 | 27.3 | 36.4 | 18.2 |
| 3.8 | መጽሐፉ የቃላት ትምህርት ቅርፅን መሰረት ያደረገ አደረጃጀትን ተከትሏል። | በቁጥር | 1 | 5 | 3 | 2 |
| | | በ% | 9 | 45.5 | 27.3 | 18.2 |

በሰንጠረዥ 8 እንደሚታየው፣ በመጽሐፉ መጀመሪያ አካባቢ የተለመዱ ነጠላ ቃላት ቀርበዋል ለሚለው 6(54.6%) ያህሉ አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 5(46.4%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። በመጽሐፉ የተከተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች

ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ይታይባቸዋል ለሚለው ጥያቄ ደግሞ 4(36.4%) ያህሉ አዎንታዊ 7(64.6%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

ሌላው ለመምህራኑ የቀረበላቸው ጥያቄ፣ መጽሐፉ ለትምህርት እርከኑ ከሚመጥኑ ነጠላ ቃላት በመነሳት በጥምርነት ወደ አሚመሰረቱ ቃላት የሚያመራ አደረጃጀት ስልትን ተከትሏል የሚል ነበር። በመሆኑም 5(46.4%) ሲስማሙበት 6(54.6%) ደግሞ አልተስማሙበትም እንዲሁም መጽሐፍ የቃላት ትምህርት ቅርጽን መሰረት ያደረገ አደረጃጀት ተከትሏል። ለሚለው ጥያቄ 6(54.6%) ሲስማሙበት 5(46.4%) ደግሞ አልተስማሙበትም።

ከመምህራኑ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት የሚያመለክተው መማሪያ መጽሐፉ ቃላትን ከቅርፃቸው አንፃር በማደራጀት ትምህርቱን ለደረጃው በሚመጥኑ ቃላት በመጀመር ቀስ በቀስ በጥምረት ወደሚፈጠሩ ሀረጎች የማሳደግ ስራ ትኩረት እንዳልተደረገባቸው፤ እንዲሁም በመጽሐፉ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት እንደሚጎድላቸው ነው።

በአጠቃላይ የተተኳሪ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት በተመለከተ ከሰነድ ፍተሻ ፣ከመጽሐፉ አዘጋጁ፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች የተሰበሰበው መረጃ የሚያመለክተው፣ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡ ቃላት ከቀላል ወደ ከባድ የሚሄድ መሆኑንና በአብዛኛው በሚያወሱት ርዕሰ ጉዳይ መደራጀታቸውን ነው። ነገር ግን የቃላቱ አደረጃጀት የተማሪዎችን ግላዊ ፍላጎትና የገሃዱ አለም የነገሮች ፍረጃ የተከተለ አለመሆኑ መረጃው ይጠቁማል።

## 4.5 የቃላት ትምህርት አቀራረብ ትንተና

### 4.5.1 የቃላት አውዳዊ አቀራረብ

በክለሳ ድርሳናት በተራ ቁጥር 4.5.1 እንደተገለፀው፣ አንድ ቃል ምንም አይነት የቅርፅ ለውጥ ሳይደረግበት በተለያዩ አውዶች ውስጥ የተለያየ ፍች ሊሰጥ ይችላል። የዚያ ቃል ፍች ግልፅ የሚሆነውም በአውናዊ አውድ ውስጥ ሲቀርብ ነው። እንዲሁም ከስነ ልሳንም ሆነ ከስነ ልቦና አንጻር የቃላት ፍች ግልፅ የሚሆነው ትርጉም ያለው አውድ ውስጥ ሲገቡ ነው። ይህም ቃላት በቁማቸው ለትምህርት ከሚቀርቡ ይልቅ በገቡበት አውድ

ፍቻቸውን ለመገመት በሚያስችል ሁኔታ ቢቀርቡ የበለጠ ተስተማሪነት እንደሚኖራቸው ያስገነዝባል።

በመሆኑም መማሪያ መጽሐፉ ቃላትን በአውድ አስደግፎ በማቅረብ ረገድ ምን ያህል ትኩረት እንደሰጠ ለማወቅ ለመምህራን ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር።

ሰንጠረዥ 9- ስለቃላት አውዳዊ አቀራረብ ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ መልሶች።

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.1 | አብዛኞቹ አረፍተ ነገሮች የአዳዲስ ቃላትን ፍች ለመረዳት የሚያስችሉ አውዳዊ ፍንጮች አሏቸው። | በቁጥር | 1 | 5 | 5 | - |
| | | በ% | 9.1 | 45.5 | 45.5 | - |
| 4.2 | ቃላት በአብዛኛው በአውድ ተደግፈው አልቀረቡም ። | በቁጥር | 2 | 3 | 5 | 1 |
| | | በ% | 18.2 | 27.3 | 45.5 | - |
| 4.5 | ቃላት ከአገባባቸው ፍቺያቸው እንዲተነበይ ለማድረግ ከቀረቡ አረፍተ ነገራዊ አውዶች በመነሳት ለመገመት የሚያስችሉ ናቸው። | በቁጥር | 2 | 5 | 4 | - |
| | | በ% | 18.2 | 45.5 | 36.4 | - |

ከሰንጠረዥ 9 እንደሚስተዋለው፣ በመጽሐፉ አብዛኞቹ አረፍተነገሮች የአዳዲስ ቃላትን ፍች ለመረዳት የሚያስችሉ አውዳዊ ፍንጮች አላቸው ለሚለው 1 (9.1%) በጣም እስማማለሁ፣ 5(45.5%)ደግሞ እስማማለሁ በማለት በድምሩ 6(54.5%) አዎንታዊ 5(45.5%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። እንዲሁም በመጽሐፉ ውስጥ ቃላት በአብዛኛው በዐውድ ተደግፈው አልቀረቡም ለሚለው መጠይቅ 6 (54.5%)፣ ሲስማሙ 5 (45.5%) ደግሞ እንዳልተስማሙ የመምህራኑ ምላሽ ያሳያል። እንዲሁም ቃላት በአብዛኛው ፍቺያቸው እንዲተነበይ ለማድረግ ከቀረቡ አረፍተ ነገራዊ አውዶች በመነሳት ለመገመት የሚያስችሉ ናቸው። ለሚለው ጥያቄ አብዛኞቹ 7(63.7%) ሲስማሙ 4 (36.4%) ደግሞ እንዳል ተስማሙ መረጃው ይጠቁማል። በተጨማሪም ለመምህራኑ ስለመጽሐፉ የቃላት ዓውዳዊ አቀራረብ በጽሑፉ አስተያየት እንዲሰጡ ለቀረበላቸው ጥያቄ፣ በመጽሐፉ ውስጥ ቃላት በአብዛኛው በአዛምድ መልክና ተማሪዎች ጥሬ ትረጉም እንዲሰጡ በሚጠይቅ መንገድ እንደቀረቡ ጠቁመዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ መጽሐፉ ውስጥ ቃላት በአብዛኛው በአውድ ውስጥ መቅረባቸውና የአውዶችን የተተንባይነት ብቃት በተመለከተ ለተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር።

ሰንጠረዥ 10፡- ስለቃላት አውዳዊ አቀራረብ ለተማሪዎች ለቀረበው ጥያቄና የተሰጠ መልስ።

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ መልሶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 4፣ 3 | 2፣1 |
| 2 | በመጽሐፉ ውስጥ በአብዛኛው የቃላት ፍቺ ትምህርት በአውድ የቀረቡ አይደሉም | በቁጥር | 73 | 127 |
| | | በ% | 36.5 | 63.5 |
| 8 | በመጽሐፍ ውስጥ ቃላት የቀረቡባቸው አረፍተነገራዊ አውዶች በአብዛኛው ፍቻቸው ለመገመት አግዞኛል | በቁጥር | 154 | 46 |
| | | በ% | 77 | 33 |

ሠንጠረዥ 10 እንደሚያመለክተው፣ በመጽሐፉ ውስጥ በአብዛኛው የቃላት ፍቺ ትምህርት በአውድ የቀረቡ አይደሉም ለሚለው ጥያቄ 73 (36.5%) ያህሉ አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 127(63.5%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። የተማሪዎቹ ምላሽ የሚያመላክተው በመጽሐፉ አብዛኛው በቃላት ፍቺ ላይ ያተኮረ ትምህርት በአውድ እንዳልቀረበ የሚያመላክት ነው። ይህ ውጤትም መምህራን ከሰጡ ምላሽ ጋር የሚስማማ ሆኖ አልተገኘም።

እንዲሁም በመጽሐፉ ውስጥ ቃላት የቀረቡባቸው አረፍተነገራዊ አውዶች በአብዛኛው ፍቻቸው ለመገመት አግዞኛል ለሚለው ጥያቄ 154 (77%) ሲስማሙበት 46 (33%) ደግሞ አልተስማሙበትም። የተማሪዎቹ ውጤት የሚያመለክተው በመጽሐፉ ቃላት የቀረቡበት አውድ የተተንባይነት ደረጃው የተሻለ መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ መምህራን ከሰጡት ምላሽ ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል።

በመጽሐፉ የቃላት ትምህርት በአውድ ተደግፈው ስለመቅረባቸው ከመምህራንና ከተማሪዎች የተሰበሰበውን መረጃ ለማረጋገጥ ሲባል የመጽሐፉ የቃላት አውዳዊ አቀራረብ ለመፈተሽ ተሞክሯል። በመሆኑም መጽሐፉ ለቃላት አውዳዊ አቀራረብ የሰጠው ትኩረት እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 11፦ ስለተተኳሪ መጽሐፉ የቃላት አውዳዊ አቀራረብ ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ ።

| ተ.ቁ | የቀረቡበት ሁኔታ | በአውድ የቀረበ | | ያለአውድ የቀረበ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | በአረፍተ ነገር ተደግፈው የቀረቡ ቃላት | 45 | 34.6 | - | - |
| 2 | ለቀረቡት ቃላት ፍቺያቸውን አረፍተነገር ሰርቶ ማሳየት የሚጠይቁ መልመጃዎች ። | 19 | 14.6 | - | - |
| 3 | ከፍቺ መመሳሰል ከተቃራኒ ፍቺ አንፃር የቀረቡ መልመጃዎች | - | - | 66 | 50.8 |
| | ድምር | 64 | 49.2 | 66 | 50.8 |

ከሰንጠረዥ 11 መረዳት እንደሚቻለው ፣ መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት አጠቃላይ የቃላት ፍች ተግባራት 45(34.6%) ቃላት አረፍተነገራዊ አውድ ተደግፈው የቀረቡ፣ 19(14.6%) ደግሞ ተማሪዎች ለቀረቡላቸው ቃላት ፍቺያቸውን አረፍተነገር ሰርተው እንዲያሳዩ የሚያለማምዱ፣ በድምሩ 64(49.2%) ቃላት በአውድ አስደግፎ ማስተማርን የሚመለከቱ ተግባራት የያዘ ሲሆን 66(50.8%) የሚሆኑ ደግሞ ከአውድ ውጭ የቀረቡ ቃላት ናቸው።

ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው በመጽሐፉ የቀረቡ የቃላት ትምህርት ተግባራት ግማሽ ያህሉ በአውድ ሲቀርቡ ግማሽ ያህሉ ደግሞ ያለአውድ መቅረባቸውን ነው። የቃላት ትምህርት ውጤታማ ከሚሆንባቸው አቀራረቦች አንዱ የቃላት ትምህርት በአውድ አስደግፎ ማቅረብ ነው። በዚህ ረገድ በመጽሐፉ ግማሽ ያህሉ ተግባራት ያለ አውድ መቅረባቸው መጽሐፉ ክፍተት ያለው መሆኑን ያመለክታል። በመሆኑም Harmer (1993:24) ቃላትን በተናጠል ከማቅረብ ይልቅ በአውድ ማቅረብ ቃላቱ ለረዥም ጊዜ ሳይረሱ እንዲቆዩ ለማድረግ ያግዛል የሚለውን ሀሳብ በተገቢው ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያላስገባ መሆኑን የሰነድ ፍተሻው ውጤት ያመለክታል።

በተተኳሪ መጽሐፉ የቀረቡት ቃላት በአውድ መቅረባቸውንና አለመቅረባቸውን በተመለከተ ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኘውን መረጃ ለማረጋገጥ ሲባል በተደረገው የሰነድ ፍተሻ፣ መጽሐፉ ቃላት በአውድ ከማቅረብ ረገድ ሰፊ ክፍተት ያለው መሆኑ

ተረጋግጧል። (ይህንን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች አባሪ "ሀ" አስረጅ 4 እና 5 ይመልከቱ)።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ በተመለከተ በቃለ መጠይቅ ተራ ቁጥር 6 ለመጽሐፉ አዘጋጅ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። አዘጋጁ የሰጡት ምላሽ በተቻለመጠን ቃላትን በቁማቸው ከማቅረብ ይልቅ በአውድ አስደግፎ ለማቅረብ ከፍተኛ ጥረት እንደተደረገ ገልፀዋል። የአዘጋጁ መልስም ከመምህራንና ከተማሪዎች ምላሽ ጋር የሚስማማ ሆኖ ሲገኝ ከሰነድ ምርመራ ከተገኘው ማስረጃ ጋር ግን የተቃረነ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም መጽሐፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ አውዳዊነት እንደሚጎድለው መረዳት ይቻላል።

የቃላትን አውዳዊ አቀራረብ ስናነሳ ቃላት የቀረቡባቸው አረፍተነገራዊ አውዶች መጠን ማየቱ አይቀሬ ጉዳይ ነው። በምዕራፍ ሁለት 4.5.1 እንደተገለፀው ቃላት የሚቀርቡባቸው አረፍተነገራዊ አውዶች ከአምስት እስከ አስር ቃላትን የያዙ ሲሆኑ የቃላትን ፍች ለመገመት ያመቻሉ። በአንጻሩ ከአምስት መጠን እያነሰ ወይም ከአስር እየጨመረ በሄደ ቁጥር ለትንበያ የሚያደርጉት አስተዋፅኦ እየቀነሰ ይሄዳል። በመሆኑም ቃላት የሚቀርቡባቸው አረፍተነገራዊ አውዶች በጣም አጭር ወይም ረዥም መሆን የለባቸውም።

ከዚህ አንፃር በመጽሐፉ ውስጥ ቃላት የቀረቡባቸውን አረፍተነገሮች መጠን ለመዳሰስ ተሞክሯል። በመሆኑም በመጽሐፉ የቀረቡ አረፍተነገሮች በአብዛኛው ከ5 እስከ 10 የሚደርሱ ሲሆኑ አልፎ አልፎ ግን ከአስር በላይ (11 እና 12) ቃላት የያዙ አረፍተነገሮች ይገኙበታል።

ሌላው በአውዳዊ አቀራረብ የሚነሳው ጉዳይ ቃላት የቀረቡባቸው አውዶች ያላቸውን የተተንባይነት ብቃት የሚመለከት ነው። የቃላት ፍች በገቡበት አውድ ለመገመት ከሚረዱ አውዳዊ ባህሪያት ውስጥ አንዱ አውዶቹ የቃላትን ፍች ለመገመት የሚያስችሉ ፍንጮች ያላቸውና ቃላት እርስ በእርሳቸው የተሳሰሩ ሊሆኑ ይገባል።

ከዚህ አንጻር፣ በተተኳሪ መጽሐፉ የቀረቡ አረፍተ ነገራዊ አውዶች ያላቸው የተተንበይነት ብቃት እና አውዳዊ ባህሪ በተመለከተ ለመምህራን ጥያቄ ቀርቦ ነበር። የቀረቡት ጥያቄዎችና መምህራን የሰጡት ምላሽም በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ሰፍሯል፡

ሠንጠረዥ 12፡- ስለ አረፍተነገራዊ አውዶች ተተንባይነት እና አውዳዊ ባህሪ በተመለከተ ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ መልሶች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.3 | ቃላትን ለማስተማር የቀረቡ ዓረፍተነገሮች ረዣዥም ናቸው። | በቁጥር | - | 2 | 7 | 2 |
| | | በ% | - | 18.2 | 63.6 | 18.2 |
| 4.4 | ቃላትን ለማሰተማር የቀረቡ አረፍተ ነገሮች አጫጭርና በሀረግ መልክ የቀረቡ አይደሉም። | በቁጥር | 2 | 5 | 4 | - |
| | | በ% | 18.2 | 45.5 | 36.4 | - |
| 4.6 | ቃላት የቀረቡባቸው አረፍተነገሮች የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመገመት የሚያስችሉ አይደሉም። | በቁጥር | - | 3 | 8 | - |
| | | በ% | - | 27.3 | 72.7 | - |

በሰንጠረዥ 12 እንደሚታየው በመጽሐፉ ቃላትን ለማስተማር የቀረቡ አረፍተነገሮች ረዣዥም ናቸው ለሚለው ጥያቄ 2(18.2%) ሲስማሙ 9(81.8%) ደግሞ አልተስማሙም የመምህራኑ ምላሽ የመሚጠቁመው በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡ አረፍተነገሮች ከተገቢው በላይ ረዣዥም (ከአስራሁለት በላይ) አለመሆናቸውን ነው። ይህም ተማሪዎች በቀላሉ የቃላትን ፍች መገመት እንዲችሉ ከማድረግ አንጻር ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል። ሌላው ለመምህራኑ የቀረበው ጥያቄ በመፀሐፉ የቀረቡ አረፍተነሮች አጫጭርና በሀረግ መልኩ የቀረቡ አይደለም የሚል ነበር። ለዚህ ጥያቄ አብዛኞቹ መምህራን 7(63.6) ሲስማሙበት፣ 4(36.4) ደግሞ አልተስማሙበትም። በመጽሐፉ የቀረቡ አብዛኞቹ አረፍተነገሮች ከተገቢው በታች (ከ5 በታች) ቃላት አለመያዛቸውና የቃላቱ ፍች በቀላሉ ለመተንበይ አመች መሆናቸውን ከመምህራኑ የተገኘ ምላሽ ያሳያል።

ከዚህ በተጨማሪ ቃላቱ የቀረቡባቸው አውዶች ያላቸውን ተተንባይነት ብቃት ለማወቅ "ቃላት የቀረቡባቸው አረፍተነገራዊ አውዶች የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመገመት የሚያስችሉ አይደለም። " የሚል ጥያቄ ለመመህራኑ ቀርቦ 3(27.3) እስማማለሁ ሲሉ አብዛኞቹ 8(72.2) ደግሞ አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። ይህ የሚያመለክተው በመጽሐፉ የቀረቡ አረፍተነገራዊ አውዶች በአብዛኛው አዳዲስ ቃላትን ለመተንበይ የሚያስችል አቀራረብ ያላቸው መሆኑን ነው። ይህም ቃላት በገቡበት አረፍተነገር ውስጥ

የቃላትን ፍች ለመረዳት የሚያግዙ አውዳዊ ፍንጮች መኖራቸው ያመለክታል። ከዚህ አንጻር መጽሐፉ ቃላትን ለማስተማር ያቀረበባቸው አረፍተነገራዊ አውዶች የቃላትን ፍቺ ለመረዳት የሚያስችሉ አውዳዊ ፍንጮችና በውስጣቸው ያሉት ቃላት የጠበቀ ቁርኝት ያላቸው መሆኑ የመጽሐፉ ጥንካሬ ያመለክታል።

### 4.5.2 የቃላት ተመሳስሎና ተቃርኖ፣ ዝርዝርና አጠቃላይ እና የአብሮ ተሰላፊ ታላት አቀራረብ ትንተና

ተማሪዎች የቃላትን ፍቺ በተመለከተ በቂ እውቀት እንዲኖራቸው ከተፈለገ የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ የሚመለከቱ መልመጃዎች ማቅረብ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑ በምእራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 4.5.2 ተገልጿል። ይኸውም ቃላት ከሚቀርቡባቸው መንገዶች አንዱ ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው አማካኝነት በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ማቅረብ ነው። ቃላትን በፍች ዝምድናቸው መሰረት ማቅረብ የቃላትን፣ ተመሳስሎ/ ተቃርኖ፣ አጠቃላይ/ ዝርዝር እና አብሮ ተሰላፊ ቃላትን ይመለከታል።

ፍቺን መሰረት ያደረገ የቃላት ዝምድና በቃላት ተመሳስሎና ተቃርኖ፣ በከታች ተካታች እና በአብሮ ተሰላፊ ቃላት ዝምድና ላይ ያተኩራል። በመሆኑም ቃላት እርስ በርሳቸው እንዴት ይዘመዳሉ? ፡ በአንድ ስነልሳናዊ አውድ ተከትሎ በመሰለፍ ፍቺ እንዴት ግልፅ ያደርጋሉ? የሚሉት ጥያቄዎች በትምህርት ዝግጅቱ ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች ናቸው።

የቃላት ተመሳስሎና ተቃርኖ ብቻ ሳይሆን የቃላት አጠቃላይነትና ዝርዝርነት በአንድ አውድ አብሮ በመሰለፍ የፍችና የአውድ ዝምድናን የማሳየት ባህሪ አላቸው። በመሆኑም በተቻለ መጠን ቃላትን በአውድ አስደግፎ ማቅረብ ቃላት እርስ በርስ ያላቸውን የፍች ዝምድና ለማስገንዘብ ያስችላል። ከዚህ አንፃር በመጽሐፉ ውስጥ የቃላትን የፍቺ ዝምድና አቀራረብ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ለመምህራን ጥያቄ ቀርቦላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 13 ፡- ስለመጽሐፉ የቃላት የፍቺ ዝምድና አቀራረብና የመምህራን ምላሽ ።

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5 | የቃላት ጥቅልና ዝርዝር የፍቺ ዝምድና ትምህርት አቀራረብ የቃላቱን ዝምድና ለመለየትና ለመጠቀም የሚያስችል ነው። | በቁጥር | 2 | 5 | 4 | - |
| | | በ% | 18.2 | 45.4 | 36.4 | - |
| 6 | በመጽሐፉ ንበት ሊያመጣ የሚችለውን የፍቺ ለውጥና የቃላትን የንግግርና የጽሑፍ ባሕሪያት የሚያስገነዝቡ ይዘቶች አልተካተቱም | በቁጥር | - | 3 | 8 | - |
| | | በ% | - | 27.3 | 72.7 | - |

ከላይ በሰንጠረዥ 13 እደሚታየው የቃላት የጥቅልና ዝርዝር የፍቺ ዝምድና ትምህርት አቀራረብ የቃላቱን ዝምድና ለመለየትና ለመጠቀም የሚያስችል ነው። ለሚለው አስተያየት 63.6% አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ 36.4% ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። የመምህራኑ ምላሽ መጽሐፉ በቃላት ፍቻዊ ዝምድና ስር የሚጠቃለሉ ይዘቶችን በማካተት ረገድ ጠንካራ ጎን ያለው መሆኑን ያስገነዝባል።

በመጽሐፉ ንበት ሊያመጣ የሚችለውን የፍቺ ለውጥና የቃላትን የንግግርና የጽሑፍ ባህሪያት የሚያስገነዝቡ ይዘቶች አልተካተቱም ለሚለውም 27.3% አዎንታዊ 72.7% ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

ከመምህራኑ የተገኘው መረጃ ተጠቃሎ ሲታይ፣ በመጽሐፉ ውስጥ የቃላት የጥቅልና ዝርዝር ፍቺ ዝምድና ትምህርት አቀራረብ የቃላቱን ዝምድ ለመለየትና ለመጠቀም የሚያስችል መሆኑ፣ እንዲሁም በመጽሐፉ ንበት ሊያመጣ የሚችለውን የፍቺ ለውጥና የቃላትን የንግግርና የጽሑፍ ባህሪያት የሚስገነዝቡ ይዘቶችን እንደተካተቱ ያረጋግጣል። ከመምህራን የተገኘውን ማስረጃ ለማጠናከር ቃላት በፍቺ ዝምድናቸው መነሻነት ስለቀረቡበት ሁኔታ የሚመለከቱ ጥያቄዎች ለተማሪዎች ጥያቄ ቀርቦላቸው የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 14፦ የፍቺ ዝምድና ትምህርት አቀራረብ ለተማሪዎች የቀረበ ጥያቄና የተሰጠ ምላሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭመል | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 4፣3 | 2፣1 |
| 7 | በመጽሐፉ የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ የፍቺ ዝምድና ትምህርት ቃላቱን ለመለየትና ለመጠቀም በሚያስችል መንገድ የቀረበ ነው። | በቁጥር | 146 | 54 |
| | | በ% | 73 | 27 |
| 10 | የቃላት የፍቺ ተመሳስሎና ተቃርኖ ትምህርት የቀረበው በአውድ አይደለም። | በቁጥር | 134 | 66 |
| | | በ% | 67 | 33 |

ከሠንጠረዥ 14 እንደሚታየው፣ በመጽሐፉ የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ የፍቺ ዝምድና ትምህርት ቃላቱን ለመለየትና ለመጠቀም በሚያስችል መንገድ የቀረበ ነው ለሚለው ጥያቄ 146(73%) አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። የተቀሩት 54(27%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። እንዲሁም የቃላት ተመሳስሎና ተቃርኖ ትምህርት የቀረበው በአውድ አይደለም ለሚለው ጥያቄ 134 (67%) አሉታዊ 66 (33%) ተማሪዎች ደግሞ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

የተማሪዎቹ ምላሽ የሚያመላክተው በአብዛኛው የመጽሐፍ የአጠቃላይና የዝርዝር የፍቺ ዝምድና ትምህርት ቃላቱን ለመለየትና ለመጠቀም በሚያስችል መንገድ መቅረቡ እና የቃላት የፍቺ ተመሳስሎና ተቃርኖ ትምህርት በአውድ መቅረቡን ነው። ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽም መምህራን ከሰጡት ምላሽ ጋር የሚጣጣም ሆኖ ተገኝቷል።

ከዚህ አንፃር የመጽሐፉን የቃላት የፍች ዝምድና አቀራረብ ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኘውን መረጃ ለማጠናከር የሰነድ ምርመራ ተደርጓል።

ሠንጠረዥ 15፡- ስለቃላት ፍቻዊ ዝምድና አቀራረብ ከሰነድ ምርምር የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | የይዘት አይነት | የይዘት ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥ | በ% |
| 1 | የቃላትን ጥሬ ትርጉም እንዲሰጡ የሚጠይቁ | 11 | 14.7 |
| 2 | የቃላትን ፍች ዓረፍተነገር እንዲያሳዩ የሚጠይቁ | 18 | 24 |
| 3 | የቃላት አጠቃላይና ዝርዝር ፍቺ የሚመለከቱ ይዘቶች | 4 | 5.3 |
| 4 | በዓረፍተነገራዊ አውድ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች | 24 | 32 |
| 5 | ለአብሮ ተሰላፊ ቃላት አውድ ተኮር ሆነው የቀረቡ | 7 | 9.3 |
| 6 | የቃላት ተቃራኒ ፍቺ የሚመለከቱ | 11 | 14.7 |
| | ድምር | 75 | 100 |

በሰንጠረዥ 15 እንደተዘረዘረው፣ በመጽሐፉ ውስጥ የቃላትን ፍቻዊ ዝምድና ለማስተማር ከቀረቡት የተለያዩ ተግባራት 11(14%) ለቃላት ጥሬ ትርጉም እንዲሰጡ፣18(24%) የቃላት ፍች በዓረፍተነገር ሠርተው እንዲያሳዩ የሚጠይቁ፣ 4(5.3%) የቃላትአጠቃላይና ዝርዝር የሚመለከቱ ይዘቶች፣ 24(32%) በአረፍተነገራዊ አውድ የቀረቡ ይዘቶች፣ 7 (9.3%) አብሮ ተሰላፊ ቃላት አውድ ተኮር ሆነው የቀረቡ፣ 11 (14.7%) ደግሞ የቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጥ የሚጠይቁ ይዘቶች በመጽሐፉ ውስጥ ቀርበዋል።

የሰነድ ምርመራው ውጤት እንደሚያሳየው የፍቺ ዝምድና የሚመለከቱ መልመጃዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በብዛት የተካተቱ መሆናቸውን ነው። የሰነድ ምርመራው ውጤትም የመምህራኑን እና የተማሪዎቹን ምላሽ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል።

የፍች በመጽሐፉ ከቃላት ፍቻዊ ዝምድና ጋር በተያያዘ ንበት ሊያመጣ የሚችለውን ለውጥና የቃላትን የንግግርና የጽሑፍ ባህሪያት የሚያስገነዝቡ ይዘቶች ማካተቱን ለማረጋገጥ በተካሄደው የሰነድ ፍተሻ በገፅ 7፣8፣9፣10 እና 106 ንበትን የሚመለከቱ መልመጃዎች ቀርበዋል። ከመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት ተግባራት በገፅ 7-10 የሚገኙት የቃላትን አንደበታዊና ፅሑፋዊ ባህሪይ፣ እንዲሁም ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚኖራቸውን የትርጉም ለውጥ የሚመለከቱ መልመጃዎች ይገኛሉ። የተወሰኑ መልመጃዎች፣ ተማሪዎች ቃላቱ በጥብቀት የተነሳ ያላቸውን የትርጉም ለውጥ በቁማቸው

እንዲገልጹ የሚጠይቁ ሲሆኑ፣ የተወሰኑት መልመጃዎች ደግሞ የትርጉም ልዩነቱን በአረፍተነገር እንዲያሳዩ የሚያደርጉ ናቸው። (ይህን የሚመለከቱ መልመጃዎች በአባሪ "ሀ" አሰረጅ 6-8 ያሉትን መመልከት ይቻላል)።

ባጠቃላይ የተተኳሪ መጽሐፉ የቃላት የፍቺ ዝምድና አቀራብ በዓይነትም ሆነ በመጠን በርከት ያሉ ተግባራትን ይዟል። በቃላት ፍቻዊ ዝምድና ስር የሚካተቱ ይዘቶችን በሙሉ ግምት ውስጥ አስገብቷል። ይሁን እንጂ ቃላትን በአውድ አስደግፎ በማቅረብ ረገድ ድክመት ይታይበታል።

### 4.5.3 የቃላት ርባታና ምስረታን አቀራረብ ትንተና

በዚህ ንኡስ ክፍል ስር ተተኳሪ መጽሐፉ ለቃላት ርባታና ምስረታ የሰጠውን ትኩረትና የአቀራረቡ ተገቢነት ለማየት ተሞክሯል።

በመሆኑም በምዕራፍ ሁለት ተራ ቁጥር 4.5.3 ቃላት የሚረቡበትንና የሚመሰረቱበትን ሂደት በሚያሳይ መንገድ ማቅረብ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላት በሚገጥሟቸው ጊዜ የቃላቱን ውስጣዊ መዋቅር በመፈተሸ ፍቻቸውን ለመረዳት የሚያስችሉ ፍንጮችን እንዲያገኙ ይረዳቸዋል። ከዚህ አንፃር ለጀማሪ ተማሪዎች ቀጥተኛ ባልሆነ አቀራረብና በርባታ ላይ፣ ለበሳል ተማሪዎች ደግሞ በቀጥታና ምስረታን ጨምሮ ማቅረብ እንደሚገባ ተጠቁሟል።

በተጨማሪም የቃላት የርባታና የምስረታ ትምህርት ከመረዳት(ማንበብና ማድመጥ) ክሂሎች ጋር በተያያዘ ተማሪዎች የሚያውቁት ቃል ሲገጥማቸው የቃሉን ምእላዳዊ አወቃቀር በመመርመር ፍቺውን እንዲደርሱበት ያግዛል። ከማፍለቅ አንፃርም እንዲሁ በተማሩት የአረባብ ስርአት ተጠቅመው ሌሎች ቃላትን በማፍለቅ ለተግባቦት እንዲያውሉ መሰረት ሊሆኑ እንደሚችሉ ተገልጿል።

ከዚህ አኳያ የቃላት ምዕላዳዊ ስርአት አቀራረብ ሁኔታ ለመምህራን ጥያቄ ቀርቦላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 16፡- የቃላት ርባታና ምስረታን የተከተለ ትምህርት አቀራረብ ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ ምላሾች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 7 | በመጽሐፉ ቃላት የሚረቡበትንና የሚመሰረቱበትን ሂደት ተመርኩዘው የሚቀርቡ ቃላት፣ የጥያቄዎቹን ተግባርና ቃላቱ ቅጥያዎቹን ያሳዩትን የቅርጽና የፍች ለውጥ ለመዳሰስ በሚያስችል መልኩ ቀርበዋል። | በቁጥር | 2 | 2 | 4 | 3 |
| | | በ% | 18.2 | 18.2 | 36.5 | 27.2 |

በሰንጠረዥ 16 እንደሚታየው፣ መምህራኑ በመጽሐፉ ውስጥ ቃላት የሚረቡበትንና የሚመሰረቱበትን ሂደት ተመርኩዘው የሚቀርቡ ቃላት፣ የቅጥያዎቹን ተግባርና ቃላቱ ቅጥያዎቹን ተቀብለው ያሳዩትን የቅርፅና የፍቺ ለውጥ ለመዳሰስ በሚያስችል መለኩ ቀርበዋል ለሚለው ጥያቄ 4(36.4%) አዎንታዊ 7(63.0%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ከመምህራኑ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው፣ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ቃላቱ ቅጥያዎችን ተቀብለው ያሳዩትን የቅርፅና የፍቺ ለውጥ ለመዳሰስ የማያስችል መሆኑን ነው። በመሆኑም መማሪያ መጽሐፉ በቃላት የርባታና የምስረታ ስርአት አቀራረብ ተገቢነት የጎደለው መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ስለተተኳሪ መጽሐፉ የቃላት የርባታና የምስረታ ስርአት አስመልክቶ ለተማሪዎች ጥያቄ ቀርቦላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሰንጠረዥ 17፡- ስለ የቃላት ርባታና ምስረታ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎች ምላሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 4፣3 | 2፣1 |
| 12 | በመጽሐፉ ውስጥ ያለው የጥምርና የምህፃረ ቃላት አቀራረብ በመጽሐፉ ውስጥ ያለው የጥምርና የምህፃረ ቃላት አቀራረብ የቅጥያዎችን የአመሰራረት ስርዓት ለመረዳት አግዞኛል። | በቁጥር | 168 | 32 |
| | | በ% | 84 | 16 |
| 6 | በመጽሐፉ ውስጥ የቅጥያዎችና የዋና ቃሎች አቀራረብ ቅጥያዎችንና ዋና ቃሉን ለመለየትና ፍቻቸውን ለመረዳት አግዞኛል። | በቁጥር | 179 | 21 |
| | | በ% | 89.5 | 10.5 |

በሠንጠረዥ 17 እንደሚታየው፣ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የጥምርና የምህፃረ ቃላት አመሰራረት ስርዓት ለመገንዘብ እንዳስቻላቸው አብዛኞቹ

168(84%) ተማሪዎች አዎንታዊ ጥቂት 32(16%) ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። እንዲሁም ስለቃላት ርባታና ምስረታ አቀራረብ ለቀረበላቸው ጥያቄ 179 (89.5) ያህሉ አቀራረቡ ተገቢ እንደሆነ ሲስማሙ፣ 21(10.5%) ደግሞ እንደማይስማሙ መልስ ሰጥተዋል።

ከመምህራንና ከተማሪዎቹ የተገኘውን ውጤት ለማመሳከር መጽሐፉ ውስጥ በቃላት ርባታና ምስረታ ላይ የተመረኮዙ ይዘት የሚገኙበትን ሁኔታ ለማየት የሰነድ ምርምራ ተካሂዷል። ከሰነድ ምርመራ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው የቃላት ርባታና ምስረታን የሚመለከቱ መልመጃዎች ብዛት 31 መሆናቸውን ነው። የዚህ ምሳሌ አባሪ "ሀ" አስረጅ 9ን ይመልከቱ።

በተተኳሪ መጽሐፉ በገጽ 106 መልመጃ ሁለት "ሠ" የሚያመለክተው፣ ከአንድ ቃል ቅጥያዎችን በመጨመር የተለያዩ ቃላትን መመስረት እንደሚቻል ወይም የአማርኛ የግስ ርባታ ስርአትን ለተማሪዎች ያሳያል። ነገር ግን በተመሰረቱት ቃላትና በተሰጠው ቃል መካከል ያለውን ልዩነት እንዲገነዘቡ አላደረገም። ሌላው በምሳሌው የቀረቡት ምስርት ቃላት አንዳንዶቹ የቅርፅም ሆነ የይዘት ልዩነት እያላቸው አንድ አይነት እንደሆኑ ተደርገው ነው የቀረቡት። ለምሳሌ "ማወቅ" እና "ማገበር" የሚሉትን ብንመለከት በቅርፅም ሆነ በይዘት የተለያዩ ናቸው። ይኸውም "አወቀ" ለሚለው "ማወቅ" ከተባለ "ገበረ" ለሚለው ደግሞ "መገበር" የሚለው ቅርፅ ነበር የሚስማማው ይሁን እንጂ ቃሉ (ማገበር)በቋንቋው የግስ ርባታ ስርአት ስላልተለመደ ተማሪዎች ሊደናገሩ ይችላሉ።

መጽሐፉ የቃላትን የርባታና የምስረታ ስርአት ለማስተማር በርካታ ተግባራትን በማቅረብና አቀራረባቸውን በማለዋወጥ ትኩረት ሰጥቷል። ይህም የቃላትን የርባታና የምስረታ ስርአት መሰረት አድርጎ ቃላትን ማቅረብ ለተማሪዎች የቃላትን ፍች ለመረዳትም ሆነ ለመጠቀም እንደሚረዳቸው ከሰነድ ምርመራው የተገኘው ውጤት ያሳያል። ይሁን እንጂ መጽሐፉ የአቀራረብ ቴክኒክ ጉድለት እንዳለበት ጥናቱ ይመሰክራል። የሰነድ ምርመራው ውጤት ከመምህራኑ መልስ ጋር ሲመሳሰል ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ ጋር ግን ይቃረናል። በጥቅሉ ሲታይ ግን መምህራን የሰጡት ምላሽ ከሰነድ ምርመራው ጋር የሚቀራረብ በመሆኑ መጽሐፉ ለቃላት የርባታና ምስረታ ስርአት ትኩረት በመስጠት ረገድ ጠንካራ ጎን እንዳለው ለመገንዘብ ይቻላል።

### 4.5.4 የቃላት አጠቃቀምንና አመራረጥL ስልት መሰረት በማድረግ ማቅረብ

በምዕራፍ ሁለት 4.5.4 እንደተገለፀው ቃላት ሁሉ ሐሳብን እኩል የመግጽ አቅምና ደረጃ የላቸውም። አንዳንዶቹ ተራና ዝርው፣ ሌሎቹ እምቅና ምስል ከሳች ወይም ሀሳብን ከማጎልበት ይልቅ የሚያደበዝዙ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ በባህሪያቸውም እንደ ርእሰ ጉዳዩ፣ እንደ መወያያው ቦታና ሁኔታ፣ እንደተወያዮቹ ማህበራዊ ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ፆታ፣ ወዘተ.. ይለያያል። በመሆኑም ይህን የቃላት ባህሪይ ተማሪዎች ተገንዝበው ቃላትን እንዳስፈላጊነታቸው መርጠው እንዲጠቀሙ ማስተማር በቃላት ትምህርት ዓይነተኛ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። አቀራረባቸውም ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ መርጦ ለመጠቀም በሚያስችል፣ ፈሊጦችንና ዘይቤዎችን ከተራ ቃላት የተለየ ባህል-ጠቀስና ምስል ከሳች ፍች እንዳላቸው በሚያስገነዝብ ዓውድ ማቅረብ ከሚፈለገው ውጤት ያደርሳል። ከዚህ አንጻር ተተኳሪ መጽሐፉ የሚገኝበትን ሁኔታ ለመመርመር ሲባል ለመምህራን ጥያቄ ቀርቦላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 18፦ ስለመጽሐፉ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም በመጽሐፉ የቀረቡበትን ሁኔታ ለመምህራን ለቀረበው ጥያቄና የተሰጠ መልስ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9 | በመጽሐፉ ውስጥ የቃላት እማሬ/ፉካሬ፣ ፈሊጥና ዘይቤ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቷቸው በቀላሉ ለመረዳትና አፍልቆ ለመጠቀም በሚያስችል መንገድ ቀርበዋል። | በቁጥር | 1 | 6 | 4 | - |
| | | በ% | 9.9 | 54.5 | 36.5 | |

በሰንጠረዥ18 እንደተመለከተው፣ በመጽሐፉ ውስጥ እማሪ/ፉካሬ፣ ፈሊጥና ዘይቤ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል ለሚለው 7(64.4%) አዎንታዊ 4(36.5%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። የመምህራኑ ምላሽ የሚጠቁመው የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ስልት በመጽሐፉ ውስጥ ተገቢ ትኩረት አግኝተው በቀላሉ ለመረዳትና አፍልቆ ለመጠቀም በሚያስችል መንገድ መቅረባቸውን ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ስለመጽሐፉ የቃላት

አመራረጥና አጠቃቀም ስልት አቀራረብ ለተማሪዎች ጥያቄ ቀርቦ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 19፡- ስለመጽሐፉ የቃላትን አመራረጥና አጠቃቀም ስልት አቀራረብ ለተማሪዎች የቀረበ ጥያቄና የተሰጠ ምላሽ።

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ መልሶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 4፣3 | 2፣1 |
| 5 | በመጽሐፉ ፈሊጣዊና ዘይቢያዊ ቃላት የቀረቡበት ስልት ፈሊጦችንና ዘይቤዎችን ለመረዳትና አስታውሶ ለመጠቀም አያስችልም | በቁጥር | 2 | 148 |
| | | በ% | 26 | 174 |

ከላይ በሰንጠረዥ 19 እንደሚታየው፣ በመጽሐፉ ፈሊጣዊና ዘይቤያዊ ቃላት የቀረቡበት ስልት ፈሊጦችንና ዘይቤዎችን ለመረዳትና አስታውሶ ለመጠቀም አያስችልም ለሚለው ጥያቄ 52(26%) አዎንታዊ 148(174%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። የተማሪዎች መልስም ከመምህራኑ ጋር የሚመሳሰል ሆኖ ተገኝቷል።

በቃላት መረጣና አጠቃቀም ዙርያ የሚነሳ ሌላው ጉዳይ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። በተተኳሪ መጽሐፉ የፈሊጣዊ አነጋገሮች አቀራረብ ምን እንደሚመስል ለመመርመር ተሞክሯል። በተደረገው ፍተሻም በገጽ 25 እና 251 ከዘይቤዎችና ከጥምር ቃላት ጋር ተቀላቅለው፣ በገጽ 191 ደግሞ ያለ አውድ ቀርበው ይገኛሉ።

ለምሳሌ በመጸሐፉ በገጽ 25 "ሀ" የቀረበው ተግባር ብንመለከት፣ ተማሪዎች በቀረበው መልመጃ /ተግባር/ አማካኝነት ፈሊጦች በቃላት ጥምረት ሊመሠረቱ እንደሚችሉ ለማሳየት ጥረት ማድረጉ ተገቢ ነው። ይሁን እንጂ እንዲጣመሩ ከተሠጡት ቃላት ያንዳንዶቹ ቅርጽ (ለምሳሌ ደመ እና ፈጅ) ከተጣመሩ በኋላ የሚኖራቸውን ቅርጽ ይዘው ቀርበዋል። ይህ ደግሞ ተማሪዎች የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዙ ያደርጋል።ከዚም ሌላ በምሳሌነት የቀረበው "ደመ ነፍስ" ቀድመውት በ"ሀ"ና በ"ለ" ረድፈ ከሠፈሩት ቃላት የተመሠረተ ስለሚመስል አቀራረቡ ግልፅነት ይጎድለዋል። እንዲሁም ፈሊጣዊ ቃላት ብቻቸውን ሳይሆን ከተራ ጥምር ቃላት ጋር ተቀላቅለው መቅረባቸው በተማሪዎች አእምሮ ፈሉጦችም ሆኑ ተራ ጥምር ቃላት አንድ አይነት ፍች እንዳላቸው የሚያስገነዝብ መንገድ ከአውድ ውጭ መቅረባቸው ተገቢ አይደለም። (አባሪ ሀ አስረጅ 11ን ይመልከቱ)

ከዚህ አንጻር፣ ፈሊጢዊ አነጋገሮችን የሚመለከቱ መልመጃዎች አቀራብ ፈሊጣዊ ቃላትን ለመረዳት አመቺ አይደለም። በመሆኑም በምዕራፍ ሁለት 2.5.4.2 ከአንድ ቃል በተመሳሳይ ሁኔታ የሚፈጠሩ ቃላትን በአንድ ላይ እያቀረቡ ማስተማር ውጤቱ በጣም ዝቅተኛ ሆኖ መገኘቱ፣ ለዚህም ምክንያቱ ፈሊጦች የሚመሳሰሉት በቅርፅ እንጂ በፍቺ አይደለም በማለት ከተገለፀው ሃሳብ ጋር የሚጣረስ ሆኖ ተገኝቷል።

ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ ለመጠቀም ብሎም ፈሊጣዊ አነጋገሮችና ዘይቤያዊ አጠቃቀሞች ከተራ ቃላት የተለየ ፍች በሚያሳይ ዐውድ አስደግፎ ማቅረብ የመማር ማስተማሩን ሂደት ስኬታማ እንደሚያደርገው በምዕራፍ ሁለት 2.5.4 ተገልጿል። ከዚህ አንጻር በገጽ 191 መልመጃ ሁለት /ሠ/ የቀረቡ ሃረጋት ስንመለከት ዘይቤዎችን ብቻ ሳይሆን ፈሊጦችንም ያካተቱ ናቸው። ለምሳሌ "ቡና ቤት" የሚለው ተራ ቃላዊ ሃረግ ሲሆን፣ በእጄ በደጄ" እና "አንድ ፍሬ ልጅ" ፈሊጦች ናቸው። ስለዚህ ተማሪዎች ዘይቤዎች፣ ፈሊጦችንና ተራ ቃላዊ ሃረጋት በቅርጽም ሆነ በይዘት አንድ አይት እንደሆኑ ሊገነዘቡ ይችላሉ። በመሆኑም ዘይባዊ አጠቃቀሞች ከፈሊጦችና ከተራ ጥምር ቃል ጋር ተቀላቅለው መቅረባቸው በምዕራፍ ሁለት 2.5.4 ከተነሳው ሀሳብ ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል። (አባሪ "ሀ" አስረጅ 12 ይመልከቱ)

### 4.5.5 ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ማቅረብ

በምዕራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 4.5.5 እንደተጠቆመው፣ ተማሪዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች የተረዷቸውን ቃላት አስታውሰው ትርጉም ባለው አውድ ውስጥ የሚጠቀሙበት የቅበላ እውቀታቸውን ተጠቅመው ነው። ስለዚህ ቃላት ከሌሎች ክሂሎች ጋር አጣምሮ ማቅረብ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም የተማሪዎች የተግባቦት አቅም መጠንና ሚዛኑን በጠበቀ የቃላት ትምህርት ክንውን መታገዝ ይኖርበታል። የተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎች ማዳበርም ከቃላት ውጭ የሚታሰብ አይደለም።

ስለዚህ የቃላት ትምህርት ህይወት የሚኖረው ቃላት በተናጠል ሳይሆን ለመረዳትና ለመጠቀም በሚያስችሉ አውዶች ውስጥ መቅረብ ሲችሉ ነው። በሌላ አገላለጽ መረዳት በማዳመጥና በማንበብ፣ መጠቀም ደግሞ በመናገርና በመጻፍ የሚገለጹ ክሂሎች ናቸው። ተማሪዎች ቃላት የመረዳት ችሎታቸውን የሚያዳብሩት አቀባይ ክሂሎችን ተጠቅመው ነው።ለዚህ ደግሞ አዳዲስ ቃላት ከሌሎች ጋር አብረው የሚገኙበት ውህድ አሃዱ እንዲያዳምጡና እንዲያነቡ ማድረግና አስቀድሞ በተቀመጠላቸው ተግባር መሰረት

ተፈላጊውንና የማይፈለግን መረጃ እንዲለዩ መደረግ እንዳለበት በምእራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 4.5.5 በስፋት የተገለጸ ጉዳይ ነው። ከዚህ አንጻር በተተኳሪ መጽሐፉ የቃላት ትምህርቱ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ተጣምሮ የቀረበበትን ሁኔታ ለማወቅ መምህራን ተጠይቀው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 20፡ ቃላት ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ስላላቸው ጥምረት ለመምህራን ለቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ ምላሾች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 10.1 | የቃላት ትምህርት በማዳመጥ ክሂል ጋር ተጣምሮ ቀርቧል | በቁጥር | 1 | 7 | 3 | - |
| | | በ% | 9.1 | 63.6 | 27.3 | - |
| 10.2 | የቃላት ትምህርት ከንግግር ክሂል ጋር ተጣምሮ አልቀረበም | በቁጥር | - | 2 | 7 | 2 |
| | | በ% | - | 18.2 | 63.6 | - |
| 10.3 | የቃላት ትምህርት ከአንብቦ መረዳት ትምህርት ጋር ተጣምሮ ቀርቧል | በቁጥር | 1 | 8 | 2 | - |
| | | በ% | 9.1 | 72.2 | 18.2 | - |
| 10.4 | የቃላት ትምህርት ከጽሕፈት ክሂል ጋር ተጣምሮ አልቀረበም | በቁጥር | - | 2 | 9 | - |
| | | በ% | - | 18.2 | 81.2 | - |

በሰንጠረዥ 20 እንደሚታየው፣ መፅሐፉ ውስጥ የቃላት ትምህርት ከማድመጥ ክሂል ጋር ተጣምሮ ቀርቧል የሚለው 8 (72.7%) ሲስማሙ 3(27.3%) ደግሞ አልተስማሙም፣ የቃላት ትምህርት ከንግግር ክሂል ጋር ተጣምሮ አልቀረበም ለሚለው 2(18.2%) አዎንታዊ 9(81.8%) አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። እንዲሁም ለተራ ቁጥር 10.3 እና 10.4 9 (81.8 %) አዎንታዊ 2(18.2%) አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። የመምህራኑ ምላሽ የሚያመለክተው መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ቃላት ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ተጣምረው የቀረቡበት ሁኔታ የተመጣጠነ መሆኑ ነው።

በመጽሐፉ ውስጥ ቃላት በአብዛኛው ተጣምረው የቀረቡት ከየትኛው የቋንቋ ክሂል ጋር ነው? የሚል በቃለመጠይቅ ተራ ቁጥር 7 ለመጽሐፍ አዘጋጁ ጥያቄ ቀርቦ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል። የቃላት ትምህርት በተቻለ መጠን ከሁሉም(4ቱ) ክሂሎች ጋር ለማመጣጠን ጥረት ተደርጓል። እንደሚታወቀው ቃላት ከአራቱ ክሂሎች ተነጥለው

የሚታዩ አይደሉም ይሁን እንጂ በተተኳሪ መጽሐፉ በአብዛኛው ከንባብ ክሂል ጋር ተቆራኝተው እንደቀረቡ ገልጸዋል።

ከዚህ አንጻር ከመምህራኑና ከመጽሐፉ አዘጋጁ የተገኙትን መልሶች ለማጠናከርና መጽሐፉ የቃላት ትምህርት ከክሂሎች ጋር አጣምሮ ከማቅረብ ረገድ ምን ያህል ትኩረት እንደሰጠ ለማወቅ የሰነድ ምርመራ ተካሂዷል። ውጤቱ እንደሚያመለክተው ከመልመጃ አንድና ሁለት ውስጥ ከቀረቡት አጠቃላይ ተግባራት 24 የሚሆኑት ከንባብ ጋር፣ 33 ያህሉ ደግሞ ከሰዋስው ጋር ተጣምረው ቀርበዋል። እንዲሁም የመልመጃ ሶስት ተግባራት በአብዛኛው አራቱን ክሂሎችን (የንግግር፣ የማድመጥ፣ የንባብና የጽሕፈት) ክሂለን አጣምረው ይዘዋል። (ለአብነት በገጽ 28 የሚገኘውን መልመጃ በአባሪ "ሀ" አስረጅ 13 ይመልከቱ)።

በተተኳሪ መጽሐፉ በገጽ 28 በመልመጃ 3 ያሉት ተግባራት ሲፈተሹ የመጀመሪያው ጥያቄ (የንግግርና ማዳመጥን)፣ ሁለተኛው ጥያቄ (የጽሕፈት፣የንባብና የማድመጥን)፣ ሶስተኛው ጥያቄ (ስነጽሑፍን)፣ እንዲሁም የመጨረሻው ጥያቄ (የማድመጥና የመናገር) ክሂሎችን ይመለከታል። የጥያቄዎቹ አቀራረብ ከቃላት ትምህርት ጋር ያላቸው ጥምረት ሲታይ በሚነበቡ ጽሑፎች ላይ በመመስረት ተማሪዎች ከጓደኞቻቸውም ሆነ ከተግባሮች ጋር ተራክቦ እንዲማሩ ጥረት አድርገዋል።

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ ከመምህራን፣ ከመጽሐፉ አዘጋጅና ከሰነድ ምርመራ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው በመጽሐፍ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ሁሉም ከክሂሎች ተጣምረው መቅረባቸውን ነው። ይህም Eyaud (2000:2) "አብዛኛው የቃላት እውቀት የሚጨበጠው በንባብ፣ በማድመጥ፣ በውይይት፣ ወዘተ ነው" በማለት ከገለጹት ሃሳብ ጋር የሚስማማ ሆኖ ተገኝቷል።

### 4.5.6 የቃላት ትምህርት በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ

በመዝገበ ቃላት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከሆኑት መካከል ንበትን፣ ሰዋሰውንና ፍችን ማስተማር ይቻላል። ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ተማሪዎች የአንድን ቃል የተለያየ ፍቺ እንዲረዱ ያግዛቸዋል፣ የአንድን ቃል ትክክለኛ ፍቺ ከአውድ እንዲገነዘቡ ማድረግም ጉልህ ድርሻ እንዳለው በምእራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 2.5.6 ተገልጿል።

ከዚህ አንጻር ተተኳሪ መጽሐፉ የሚገኝበትን ሁኔታ ለማወቅ ስለመጽሐፉ በመዝገበ ቃላት የተደገፈ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ለመምህራን ጥያቄ ቀርቦ የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 21፡- በመጽሐፉ ስለመዝገበ ቃላት የተደገፈ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ለመምህራን የቀረበው ጥያቄና የተሰጠ ምላሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.2 | በመጽሐፉ በመዝገብ ቃላት አጠቃቀም ላይ ያተኮሩ መልመጃዎች የመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ጥበብን የማለማመድ ብቃታቸው ዝቅተኛ ነው። | በቁጥር | - | 4 | 6 | 1 |
| | | በ% | | 36.5 | 54.5 | 9.1 |

በሰንጠረዥ 21 እንደተመለከተ፣ ተተኳሪ መጽሐፉ ቃላትን በመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ላይ ያተኮሩ መልመጃዎች የመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ጥበብን የማለማመድ ብቃታቸው ዝቅተኛ ነው ለሚለው 7(63.6%) አሉታዊ 4(36.5%) ደግሞ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። የመምህራኑ ምላሽ እንደሚጠቁመው፣ ተተኳሪ መጽሐፉ የመዝገበ ቃላት አጠቃቀምን የሚያለማምዱ የቃላት ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብ ድክመት የማይታይበት መሆኑን ነው።

መምህራኑ የሰጡትን ምላሽ ለማጠናከር ሲባል መጽሐፉ በመዝገበ ቃላት የተደገፈ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ለቃላት ትምህርት ያበረከተውን አስተዋጽኦ እንዲገልጹ ለተማሪዎች ጥያቄ ቀርቦ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 22፡ በመዝገበ ቃላት የተደገፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎች ምላሽ።

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ብዛት | አማራጭመልሶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 4፣3 | 2፣1 |
| 9 | በመጽሐፉ ቃላት ከመዝገበ ቃላት ውስጥ እንዴት ፈልጌ ማግኘት እንዳለብኝ ተምሪያለሁ። | በቁጥር | 131 | 69 |
| | | በ% | 65.5 | 34.5 |

በሠንጠረዥ 22 እንደሚታየው፣ መጽሐፉ ቃላት ከመዝገበ ቃላት ውስጥ እንዴት ፈልጌ ማግኘት እንዳለብኝ ተምሬያለሁ ለሚለው 131(65.5%) ያህሉ ሲስማሙበት 69(34.5%) ደግሞ አልተስማሙበትም። የተማሪዎቹ ምላሽ የሚያመለክተው፣ መጽሐፉ ውስጥ የመዝገበ ቃላት አጠቃቀምን የሚያለማምዱ መልመጃዎች በበቂ ሁኔታ የቀረቡ መሆናቸውን ነው። የተማሪዎቹ ምላሽም መምህራን ከሰጡት መልስ ጋር የሚጣጣም ሆኖ ተገኝቷል።

ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ መጽሐፉ ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብ ረገድ ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ የሰነድ ፍተሻ ተደርጓል። በመሆኑም መጽሐፉ ውስጥ በገጽ 27 እና በገጽ 79 የተለያዩ ቃላትን በማቅረብ ተማሪዎች በፊደል ቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ የሚጠይቁ መልመጃዎች ቀርበዋል። ይህንኑ የሚያሳይ በገጽ 79 የሚገኘውን መለመጃ ቀጥለን እንመልከት

ረ. ቀጥሎ የተሰጡትን ቃላት በመዝገበ ቃላት ላይ በሚገኘው ሆሄ ተራ መሰረት በቅደም ተከተል ደርድራችሁ ጻፉ

1. ትግራይ
2. አክሱም
3. ይሐ

ከላይ በአስረጅ እንደሚታየው፣ መልመጃው በመዝገበ ቃላት ላይ እንዴት ባለ ቅደም ተከተል ሊቀመጡ እንደሚችሉ ተማሪዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ያለመተግበር ነው።

መልመጃው በመዝገበ ቃላት ላይ ቃላት በፊደል ተራቸው መሰረት እንደሚሰፍሩ ማስገንዘቡ በመዝገበ ቃላት ላይ ቃላትን የሚመለከት መረጃ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ብልሃቶች በአንዱ ላይ ማተኮሩ ተገቢ ነው። ይሁን እንጂ ቃላትን በፊደል ተራ የማስቀመጥ ጥያቄ ከመጠየቅ ይልቅ ተማሪዎቹ መዝገበ ቃላት ተጠቅመው የሚሰሩባቸው መልመጃዎች መቅረጽና ማቅረብ የተሻለ ይሆን ነበር። የመዝገብ ቃላት አጠቃቀም ግቡም ይኸው ነበር። በዚህ አኳኋን ተማሪዎች መዝገበ ቃላትን እንዲጠቀሙ አለመገፋፋታቸው የመምህራን ጥገኛ በመሆን በራሳቸው እንዳይተማመኑ ያደርጋቸዋል።

ባጠቃላይ ከሰነድ ምርመራ የተገኘው መረጃ ከመምህራን እና ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ ጋር በተወሰነ መልኩ የሚቀራረብ ሆኖ ተገኝቷል። ይሁን እንጂ በመጽሐፉ መዝገበ ቃላትን እንዲጠቀሙ የሚገፋፉና አጠቃቀሙን የሚያለማምዱ መልመጃዎች በሚፈለገው መጠንና ዓይነት አለመካተታቸው ከሰነድ ምርመራ የተገኘው ውጤት ይጠቁማል።

### 4.5.7 የቃላት ትምህርት መመሪያ አቀራረብ ግልጽነት

የቃላት መልመጃ ሲዘጋጅና መመሪያ ሲቀረፅለት መልመጃው ያተኮረበትን የቃላት ትምህርት ይዘት ግምት ውስጥ ማስገባት፣ ያንን ይዘት ለተማሪዎች ለማቅረብ በምርምር የተደገፈውን ስልት መሰረት ማድረግ ይኖርበታል። እንዲሁም ክንዋኔዎቹን ለማለማመድ የሚቀረፁ መመሪያዎች ግልጽ ሊሆኑ ይገባል። ከዚህ አንጻር የመጽሐፉ የቃላት ትምህርት መመሪያዎች ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ ለመምህራን ጥያቄ ቀርቦ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 23፦ ስለቃላት ትምህርት መመሪያዎች ተገቢነት የመምህራን ምላሽ፡-

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.1 | በመጽሐፉ የቃላት ትምህርት መመሪያዎች በተገቢ ማብራሪያዎችና ምሳሌዎች ተደግፌው የቀረቡበት ደረጃ ዝቅተኛ ነው። | በቁጥር | 2 | 6 | 3 | - |
| | | በ% | 18.2 | 54.5 | 36.5 | - |

በሰንጠረዥ 23 እንደሚታየው፣ በመጽሐፉ ውስጥ የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ተግባራቱን ለማከናወን በሚያስችሉ ምሳሌዎችና ማብራሪያዎች ተደግፌው ስለመቅረባቸው መምህራኑ ተጠይቀው 8(63.5%) አዎንታዊ 3(36.5%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። በመሆኑም በመጽሐፉ የቃላት ትምህርት የቀረቡባቸው መመርያዎች በማብራሪያና በምሳሌ የተደገፉ እንዳልሆኑ ከመምህራኑ የተገኘ ማስረጃ ይመሰክራል።

የቃላት ትምህርት መመሪያዎች ግልጽነት ለመፈተሽ እንደመምህራኑ ሁሉ ለተማሪዎችም ጥያቄ ቀርቦ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 24፦ በተተኳሪ መጽሐፉ ውስጥ ስለ ቃላት ትምህርት መመሪያዎች ግልጽነት የተማሪዎች ምላሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | አማራጭ መልሶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | 4፡3 | 2፡1 |
| 3 | የቃላት ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብ በተብራሩና በምሳሌ የተደገፉ መመሪያዎች የታገዘ አይደለም | በቁጥር | 53 | 147 |
| | | በ% | 26.5 | 73.5 |

በሰንጠረዥ 24 እንደሚታየው የቃላት ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብ በተብራሩና በምሳሌ የተደገፉ መመሪያዎች የታገዘ አይደለም ለሚለው 53(26.5%) አዎንታዊ፣ 147 (73.5%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። የተማሪዎቹ ምላሽ የሚያመለክተው በመጽሐፉ የቀረቡ የቃላት ትምህርት መምሪያዎች ግልጽና የተብራሩ መሆናቸውን ነው። ይሁን እንጂ የተማሪዎቹ መልስ ከመምህራን ምላሽ ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል።

ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኘውን መረጃ ለማረጋገጥ ሲባል የተተኳሪ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት መመሪያዎች በተመለከተ የሰነድ ምርመራ ተካሂዷል። በምርመራው የተገኘ ውጤት እንደሚያመለክተው፣ በመጽሐፉ ውስጥ አልፎ አልፎ አደናጋሪ መመሪያዎችና ምሳሌዎች ይገኛሉ። ለአብነት በገጽ 25(ሪ) ተራ ጥምር ቃላትና ፈሊጣዊ አነጋገሮች ተቀላቅለው የቀረቡበት፣ በገጽ 66 (2) ምስርት ቃልና ቃሉ የገባበት አረፍተነገር የተቀላቀሉበት፣ በገጽ 106(2) ምሳሌውና ጥያቄው ያልተለዩበት፣ በገጽ 235(ሰ) በውስጣቸው የሚፈለግ ነገር የሌላቸውና ተጠይቃዊነታቸውን ያልጠበቁ አረፍተነገሮች የተካተቱበት፣ ወዘተ. ሆነው መገኘታቸውን መጥቀስ ይቻላል። ይህ ውጤት ከላይ መምህራን ከሰጡት መልስ ጋር ተስማሚ ሆኖ ሲገኝ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ ጋር ግን የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል።

በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሐፉ የቃላት መመሪያዎች በምሳሌና በተብራራ መልኩ ተደግፈው እንዳልቀረቡና ግልጽነት የሚጎድላቸው የተወሰኑት መልመጃዎች ቢኖሩም እንኳ፣ በተገቢ ምሳሌዎችና ማብራሪያዎች የተደገፉ መልመጃዎች በብዛት እንዳሉም የሰነድ ምርመራው ውጤት አረጋግጧል።

# ምእራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በትግርኛ አፋቸውን ለፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት ትምህርት አመራረጥ አደረጃጀት እና አቀራረብ መመርመር ነው። በዚህ አብይ አላማ ስር የሚካተቱ ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎች ይገኛሉ።

1. ተተኳሪ መጽሐፍ የቃላት ትምህርቶችን ለመወሰን ተገቢ መስፈርቶች ተጠቅሟልን?
2. መጽሐፉ የቃላት ትምህርት ይዘቶችን ሲያደራጅ ለቃላት ትምህርት አደረጃጀት መሰረት የሆኑ መስፈርቶችን ባገናዘበ መንገድ ነውን?
3. በመጽሐፉ ተገቢ የሆኑትን የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ብልሃቶች አገልግሎ ላይ ውለዋልን? የሚሉት ነበሩ።

እነዚህ ጥያቄዎች ለመመለስ በቅድሚያ ተጠኝዎች እና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተመርጠዋል። ጥናቱ በዋናነት ያጠነጠነው ለትግራይ ክልል ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎቸ የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ነው። የዚህን መጽሐፍ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ አደረጃጀትና አቀራረብ፣ ለመመርመር ከተተኳሪ መጽሐፍ በሰነድ ፍተሻ ከመምህራን እና ከተማሪዎች በጽሑፉ መጠይቅ እንዲሁም ከመጽሐፉ አዘጋጅ በቃለ መጠይቅ አስፈላጊ መረጃ ተሰብስቦና ተደራጅቶ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በገላጭ አቀራረብ ስልት የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ተሰጥቷል። በዚህ መሰረት ከጥናቱ የተገኙ ውጤቶች ቀጥለው ይቀርባሉ።

## 5.1 ማጠቃለያ

ለትግራይ ክልል ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ከሌሎቹ የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች አንጻር ሲታይ በቂ ቦታ እንደተሰጠው በጥናቱ የተገኘው ውጤት ያመለክታል። በመጽሐፉ ውስጥ ቃላት

ተመርጠው የቀረቡበት ዋና መንገድ በሚነበቡ ጽሑፎች አማካኝነት ሲሆን ጽሑፎቹ ሲመረጡ ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላት ታሳቢ እንደተደረጉ፣ በምንባቦቹ ውስጥ ያሉት ቃላት ከባህል ጋር የማይጋጩ፣ ተማሪዎች አካባቢያቸውን ለመገንዘብና ለመግለጽ የሚያስችሏቸው፣ ተስተማሪነታቸው የሚሉት መስፈርቶች አካትተዋል። እንዲሁም አንድ ቃል ሰፊ የአገልግሎት ሽፋንና ስርጭት ባይኖረውም እንኳ ለቋንቋ ማስተማሪያነት በሚቀርቡ ምንባቦች ውስጥ የተለየ አስፈላጊነት ይዞ ሲገኝ የሚመረጥበት ሁኔታ (በቅርብ የመገኘት መስፈርት) ግምት ውስጥ አስገብቷል። ይሁን እንጂ በመጽሐፉ መደበኛነትን ያልጠበቁ ቃላት ተስተውለዋል።ይህም የቃላት አገልግሎትና የስርጭት ሽፋን ከግምት ውስጥ እንዳላስገባ የጥናቱ ውጤት ጠቁሟል።

በመፅሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀትን በተመለከተ በአብዛኛው የቃላቱን አውዳዊ ዝምድናና የሚያወሱትን ርዕሰ ጉዳይ መሠረት በማድረግ እንደተደራጁ፣ ነገር ግን ይህ በአጋጣሚ የሆነ እንጂ ቃላትን በመልመጃ ለማደራጀት አዘጋጁ ከመነሻው ይህ ነው የሚባል መስፈርት እንዳልተጠቀሙ በጥናቱ ተደርሶበታል። ከዚህም ሌላ ቃላት ያላቸውን የተለየ የፍቺ ገጽታ ከግምት ያስገባ አደረጃጀት እብዛም ትኩረት እዳልተደረገበት፣ ከዚህም የተነሳ ፈሊጦች ከነጠላ ቃላት፣ ከጥምር ቃላት፣ ከምሳሌያዊ አነጋገርና ከዘይቤዎች ጋር ተደባልቀው መደራጀታቸው ተረጋግጧል። በመሆኑም ተማሪዎች አዲስ የቀረበላቸውን ፈሊጣዊ አነጋገር እንደማንኛውም ጥምር ቃል ተመልክተው በተጣማሪ ቃላቱ ፍች ላይ በመመርኮዝ በተሳሳተ መንገድ ፍቺውን ሊረዱ ይችላሉ።

በቃላት ፍቺ ላይ ያተኮረ ትምህርት አቀራረብ ስንመለከት፣ ከመጽሐፉ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘት ግማሽ ያህሉ በአውድ ተደግፈው ቀርበዋል። ቃላቱ ከቀረበላቸው አረፍተ ነገራዊ አውዶች በአብዛኛው የቃላትን ፍቺ በገቡበት ቦታ ለመገመት የሚያስችሉ አውዳዊ ፍንጮች ይዘውና የተመጣጠነ ርዝመት ያላቸው ሆነው ቀርበዋል። ይሁን እንጂ ግማሽ ያህሉ ያለአውድ መቅረባቸው የመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አውዳዊነት እንደሚጎድለው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

በመጽሐፉ ውስጥ የቃላት ፍቻዊ ዝምድና የቀረበበት ስልት ዐውድ ተኮር ነው። ይሁን እንጂ የቃላት ተመሳስሎና ተቃርኖ ትምህርት በአዛምድ መልክ የቀረበ በመሆኑ ተማሪዎች ቃላቱ በምን አይነት አገባብ ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቺ እንደያዙ ለመረዳት ያስቸግራቸዋል። በአዛምድ መልክ ከቀረቡመልመጃዎች በተጨማሪ ሌጣቸውን ቀርበው

ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ የተጠየቀበት ሁኔታ አለ። ይህም የቃላት ተመሳስሎና ተቃርኖ ትምህርት ደካማ አቀራረብ እንዳለው ያመለክታል። እንዲሁም ተተኳሪ መጽሐፍ ለቃላት አጠቃላይ/ ዝርዝር ፍቻዊ ዝምድና ምንም አይት ትኩረት እንዳልሰጠ ጥናቱ አረጋግጧል።

በቃላት የርባታና የምስረታ ሂደት ላይ የተሞረከዘው ትምህርት ትኩረት ተደርጎበት በተለያዩ የአቀራረብ ስልቶች እንደቀረበ፣ ነገርግን የቃላት ትምህርት ይዘት ለማስጨበጥ ታስበው በቀረቡት መልመጃዎች ላይ የቅርጽና የይዘት መጣረስ ይታይባቸዋል። ይህም መጽሐፉ ተገቢ የሆነ አርትኦት እና ትኩረት እንዳልተቸረው ያመለክታል።

መጽሐፉ ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ በማቅረብ ረገድ የተወሰነ ትኩረት ቢያደርግም፣ ተማሪዎች የአጠቃቀም ጥበቡን እንዲካኑ የሚያስችል ተግባራዊ አካሄድን እንዳልተከተለ ተረጋግጧል። ይህም ተማሪዎችን የመምህራቸው ጥገኛ እንዲሆኑና በራሳቸው እንዳይተማመኑ በማድረግ አሉታዊ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ከዚህ ሌላም የቃላት ትምህርት ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ተጣምሮ የቀረበበትን ሁኔታ ስንመለከት በተወሰነ መልኩ ከአንብቦ መረዳት ጋር ተጣምሮ ይቅረብ እንጂ ሚዛናዊ አካሄድ እንዳለው ጥናቱ አሳይቷል።

ሌላው የቃላት ትምህርቱ የቀረበባቸው መመሪያዎች ተገቢነትን የሚመለከት ነው። በመጽሐፉ መመሪያዎች አብዛኛው በተገቢ ማብራሪያዎችና ምሳሌዎች በመደገፍ ግልጽ ሆነው ሲቀርቡ፣ አልፎ አልፎ ግን ተገቢነት የሚጎድላቸው አደናጋሪ መመሪያዎች ፣ ተገቢ ማብራሪያ የሚጎድላቸውና በምሳሌ ያልተደገፉ መመሪያዎች መኖራቸው ጥናቱ አረጋግጧል።

በአጠቃላይ መጽሐፉ ለቃላት ትምህርት ተገቢ ትኩረት እንደሰጠ፣ በመጽሐፉ ቃላት በአብዛኛው አውዳዊ ዝምድናና የሚያወሱትን ርእሰ ጉዳይ መሰረት በማድረግ እንደተደራጁ፣ ፍቺ ላይ ያተኮረ ትምህርት ግማሽ ያህሉ ያለአውድ የቀረበ መሆኑ፣ የቃላት ተመሳስሎና ተቃርኖ በአዛምድ መልክ የቀረበ መሆኑ፣ የቃላት ትምህርት ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በመጣመር የቀረበበት ደረጃ በተወሰነ መልኩ ሚዛናዊ እንደሆነ፣ እንዲሁም የቃላት ትምህርት የቀረቡባቸው መመሪያዎች በአብዛኛው በተገቢ ማብራርያና መመሪያ የተደገፉ መሆናቸውን ተረጋግጧል። ሌላው ተተኳሪ መጽሐፉ፣ መደበኛነታቸውን

ያልጠበቁ ቃላት የሚስተዋሉበት፣ የቃላት ትምህርት አቀራረብ አውዳዊነት እንደጎደለው፣ ቃላት ያላቸው የተለየ የፍቺ ዝምድና ገፅታ ከግምት ያስገባ አደረጃጀት እምብዛም ትኩረት እንዳልተሰጠው፣ ለቃላት አጠቃላይ/ ዝርዝር ፍቻዊ ዝምድና ግምት ውስጥ ያላስገባ መሆኑን፣ እንዲሁም አልፎ አልፎ አደናጋሪ መመሪያዎችና ምሳሌዎች በተተኳሪ መጽሐፉ ውስጥ እንደሚገኙ የጥናቱ ውጤት ያረጋግጣል።

## 5.2 አስተያየቶች

የጥናቱ ውጤት መሰረት በማድረግ ወደፊት ለሚያዘጋጀው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፉም ሆነ ሌሎች ተከታታይ መጻሕፍት መነሻ በመሆን ያገለግሉ ዘንድ የሚከተሉት አስተያየቶች ቀርበዋል።

- መጽሐፉ የተወሰኑ መስፈርቶችን ተመርኩዞ ቃላትን ለመምረጥ ጥረት ማድረጉ የሚበረታታ ነው። ነገር ግን ለቃላት መምረጫነት ያገለግላሉ ብለው ምሁራን ከአሰፈሯቸው መመዘኛዎች ውስጥ ሁሉም ላይ አላተኮረም። ስለዚህ የቃላት መረጣ ሲካሄድ በተቻለ መጠን ቋንቋን ለጠቅላላ አላማ ለማስተማር ለሚነደፍ መርሃ ግብር እንዲውሉ በመስኩ ምሁራን ለተዘረዘሩት የቃላት መምረጫ መስፈርቶች ሁሉ ተገቢ ትኩረት ቢሰጥ፣
- በመጽሐፉ ግማሽ ያህሉ የቃላት ትምህርት ተግባራት በአውድ ተደግፈው መቅረባቸው የቃላትን ፍቺ ከማለማመድ አኳያ የሚበረታታ ነው። ይሁን እንጂ ግማሽ ያህሉ ያለአውድ መቅረባቸው መጽሐፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ አውዳዊነት እንደጎደለው ያመለክታል። ስለዚህ ቃላቱ በአብዛኛው በአውድ ተደግፈው ቢቀርቡ፣
- በመጽሐፉ መመሪያዎች በአብዛኛው በተገቢ ማብራሪያ እና ምሳሌዎች ተደግፈው መቅረባቸው የሚበረታታ ነው። ነገር ግን የተወሰኑ መልመጃዎች ተገቢ የሆኑ ማብራሪያዎችና ምሳሌዎች ይጎድላቸዋል። ስለዚህ መመሪያዎቹ የእያንዳንዱን ክንዋኔ የአሠራር መንገድ የሚጠቁሙ፣ የተብራሩና ምሳሌዎችን ያካተቱ ሆነው ቢዘጋጁ።
- በመጽሐፉ በዋነኛነት ቃላትን በሚያወሱት ርእሰ ጉዳዮች ሌሎች የተወሰኑ ማደራጃ መንገዶች ስራ ላይ መዋላቸው ጥሩ ነው። ይሁን እንጂ የቃላት ትምህርት ሲደራጅ

ለማቅረብ የተፈለገው ይዘት ብቻ ሳይሆን፣ ለተማሪው የቀድሞ እውቀትና ፍላጎት፣ ለቃላቱ ተስተማሪነትና ሌሎች መስፈርቶችም ትኩረት እየተሰጠ ቢዘጋጅ፣

❖ መጽሐፉ በንባብ የተነሳ በቃላት ላይ ሊመጣ ለሚችለው የፍቺ ለውጥ፣ ለቃላት የርባታና የምስረታ ስርአት፣ ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ለማቅረብ፣ ለቃላት አንደበታዊና ጽሑፋዊ ባህሪያት ትምህርቱ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ስርአት እንዲኖረው ከማድረግ ረገድ ጠንካራ ጎን ይታይበታል። ነገር ግን ተማሪዎች እንዲገነዘቡት የተፈለገው ይዘት በቅርጽም ሆነ በይዘት ግልጽነቱንና ትክክለኛነቱን ጠብቆ በማቅረብ ረገድ ችግሮች ይታዩበታል። ስለዚህ ተተኳሪ መጽሐፉን በተመለከተ የሚመለከታቸው አካላት(ለምሳሌ መምህራን፣አዘጋጆች እና ተማሪዎች) ተከታታይ ግምገማ በማድረግ አስፈላጊውን ማሻሻያ ቢያደርጉለት።

❖ በመማሪያ መጽሐፉ ለትምህርት የተመረጡ አዳዲስ ፈሊጦች ከነጠላ ቃላት፣ ከጥምር ቃላት፣ ከምሳሌያዊና ዘይቤአዊ አባባሎች ጋር ተደባልቀው ቀርበዋል። ስለዚህ ለትምህርት የሚቀርቡ ፈሊጦች የፈሊጣዊ ቃላት የፍቺ ገጽታን በአገናዘበ መንገድ ለብቻ ተደራጅተው ቢቀርቡ።

❖ በመጽሐፉ ከተካተቱት ቃላዊ ሀረጎች፣ በተለይ የፈሊጣዊ ቃላት ትምህርት የፈሊጦችን ፍች ለመለየትና በተግባቦት ሂደት አፍልቆ ለመጠቀም በሚያስችል ስልት ቢቀርብ።

# ዋቢ ጽሑፎች


ማረው ዓለሙ። (1987) "በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል በሁለተኛዓመት ተማሪዎች በግልና በቡድን የሚጻፉ በሳል ድርሰቶች ንጽጽራዊ ግምገማ ጥናት።" በአድስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)

______። (1998)። *አማርኛ ቋንቋን የማስተማር* ዘዴ። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተምያ ድርጅት።

ሲሳይ ተበጀ። (1990) "በአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ያለው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ቃላትን በማስተማር ረገድ ያለው ብቃት።" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ስነዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)

ተስፋ አበራ እና ማረው ዓለሙ። (1993)። "አማርኛ ቋንቋን በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማስተማር ዘዴ።" ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ፣ ለልዩ ዲግሪ ፕሮግራም የርቀት ትምህርት የተዘጋጀ። (ያልታተመ)

ትንሳኤ ብርሃኔ። (1988)። "የአማርኛ የቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት።" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ሥነዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)

ባየ ይማም። (2000)። *የአማርኛ ሰዋስው* (የተሸሻለ ሁለተኛ እትም):: አዲስ አበባ፤ እሌኒ ማ.ኃ.የተ.የግ. ማኀበር።

አንበሴ በቀለ። (1993)። "በኦሮሚያ ክልል ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ትንተና።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ መሟያ የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል። (1993)። *የአማርኛ መዝገበ ቃላት*። አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ጌታሁን አማረ (1990) *ዘማናዊ አማርኛ ሰዋሰው በቀላል አቀራረብ*። ንግድ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።

ጌታቸው እንዳለማው (1994) *የቋንቋና ስነ ልሳን መግቢያ*። ቅጽ ሁለት፣ ዲላ፣ ዲ.መ.ጤ.ሳ.ኮ (ያልታተመ)

Alderson J.C, Clopham.C, and Wall, (1995). *Language Test Construction and Evaluation.* Cambridge: Cambridge university press.

Allen, V.F (1983) ***Techniques in Teaching Vocabulary***. Oxford: Oxford University Press.

Bauer, L. (1998). ***Vocabulary.*** London and New York: Rouledge.

Biber, D. et al. (1998). ***Corpus Linguistic: Investigating Language Structure and Use.*** Cambridge: Cambridge University Press.

Batstone, R.(1994a). ***Grammer.*** Oxford: Oxford University Press.

Bastone, R. (1994b). "Product and Process: Grammer in the Second Language Classroom". in Bygate. M. Alan Tonkyn and Eddia Williams (eds.). ***Grammer and the Language Teacher.*** London: Prentice Hall International (UK) Ltd. Vol. 12, No. 3, PP 19-21.

Blachowicz, C.and J. Fisher Peter. (2005). Integrated Vocabulary Instruction: Meeting the Diverse Learners in Grade K- 5. WWW.learninggpt.Org. Retrieved 6 Oct. 2010. 10:08 a.m.

Carter, R.(1991). Lexis In Bowers, R. and Christopher Brimful (eds.). ***Applied Linguistics and English Language Teaching***. London: Macmilan Publishers Limited.

Carter, R. and McCarthy Micheal. (1988). ***Vocabulary and Language Teaching.*** New York: Longman.

Celce Murcia, (1991) ***Teaching English as a Second or Foreign Language.*** Boston: Heinle Publishers.

Cumino, M. (1990), "The role of Vocabulary in Forign Language Teaching." In Hill, D. and SusanHolden (eds.). ***Effective Teaching and Learning.*** London: Modern English Publications. Vol 26, No. 4, PP83-89.

Cunningsworth, A. (1995). ***Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials***. Oxford: Heinemann International.

Dubin, F. and Olshatin Elite . (1986). ***Course Design: Developing Programs and Matereals for Language Learning.*** Cambridge: Cambridge University Press.

______ (1992). ***Course Design: Developing Programs and Matereals for Language Learning*** (6th ed.) Cambridge: Cambridge University Press.

Elley, W.(1989).Tailoring the Evolution to Fit the Context.In Johnson, R.(ed.). ***The Seconed Language Curriculum*** Cambridge: Cambridge University Press. Vol. 21, No. 2, PP 53-60.

Ellis. R. (1995) ***Understanding Second Language Acquisition.*** Oxford: University Press.

Eyraud, K. (July 2000). The world wall Approach: Promoting 12 Vocabulary Learning. ***Englis Teaching Forum.*** Vol. 38, No. 3, pp. 1-11.

Gairns, R. and Redman Stuart . (1986). ***Working with Words: A Guide to Teachin Vocabulary.*** Cambridge: CUP.

Harmer, J (1987). ***Teaching and Learning Grammer.*** London: Longman group UK. Ltd

Harmer, J (1991). ***The Practice of English Language Teaching.*** London: New York: Longman Group (UK) Ltd.

Harmer, J. (1993). ***The Practice of English Language Teaching.*** London: Longma groups (UK). Limited.

Hunt, A and Belgar David. (2002).Current Research and Practice in Teaching Vocabulary. In Richards, J and Willy Renandya (eds.). ***Methodology in Language Teaching: An Anthology of Current Practice.*** Cambridge: Cambridge University Press. Vol. 4, No. 4 PP 313-319.

Joe, A. (June 1995). The Value of Retelling Activities to Vocabulary" ***Guidelines: A Periodia for a Classroom Language Teaching.*** Vol.17, No1, pp. 1-8.

Lewis, M. and Jimie Hill. (1992). ***Practical Technique for Language Teaching.*** London: Commercial Colours Press.

Lewis, M. (1993). ***The Lexical Approach.*** London: Commercial Colour Press.

Lowson, M and Donald Hogben. (March 1996)."The Vocabulary- Learning Strategies for Foregn Language Students. ***Language Learning Journal.*** Vol. 16, No. 1, PP. 101-135.

McCarthy, M.(1990). ***Vocabulary.*** Oxford: OUP.

McCarten, J.(2007).Teaching Cocabulary: Lesson from the Corpus Lesson for the Classroom www.cambridge.org. Retrieved 14 Set. 2010. 9:37am.

Ming, T. (July 1993). Innovative ways to Teach Vocabulary Some Practical Idea for the Classroo Teacher.***Guidelines: A Periodical for Classroom Teacher.*** Vol. 19, No.1, pp. 11-21

Morley, J. (1990).Lexicography and Language Learning. In Hill, D. and Susan Holden(eds.). ***Effevtive Teaching and Learning.*** London: Modern English Publications. Vol. 13 No. 4, PP. 34-37.

Nation, P. and Cody Jams. (1988). Vocabulary and Reading." In Carter, R. and Micheal MCCarthy (eds.). ***Vovabulary and Language Teaching*** . New York: Longman Group (UK) Limited.

Nation, P. (October 2000). Designing and Improving a Language Course. ***English Teaching Forum.*** Vol. 38, No. 4, pp.2-11. http://www.victoria.ac.nz/lals/staff/paulnation.aspx . Retrieved 13 Sep. 2010. 8:22am.

Nattinger, J. (1988).. Some Current Trends in Vocabulary Teaching." In Carter, R. and Micheal McCarthy(eds.). ***Vocabulary and Language Teaching.*** New York: Longman Group (UK) Limited. Vol. 32, No. 3, PP. 23-26.

Nunan, D.(1991). ***Language Teaching Methdology: A Textbook for Language Teachers.*** Edinberurgh: Pearson Education Ltd.

Pikulski, J. and Templeton Shane. (2004).Teaching and Developing Vocabulary: Key to Long-Term Reading Success. http://www.eduplace.Com/state/author/pik_temp.pdf Retrieved 2 Sep. 2010. 2:19 pm.

Richards, J. C. and Rodgers, T.S. (1986). ***Approaches and Methods in Language Teaching.*** Cambridge: Cambridge University Press.

River, W. (1994). ***Communicating Naturally in Second Language.*** (8th ed.) Cambridge: Cambridge University Press.

Scrivener, J. (1998). ***Learning Teaching.*** Oxford: Macmilan Publishers Limited.

Seal, B. (1991). Vocabulary Learning and Teaching." In Celce- Murcia, M. (ed.). ***Teaching English as Second of Foreign Language.*** Boston: Heinle and Heinle Pulishers. Vol. 18, No. 2, PP. 46-49.

Sinclair.J.McH andRenouf Antoinette. (1988) "A Lesxical Syllabus for Language. " in Carter. R. Michael. McCarthy (eds) ***Vocabualry and Language Teaching.*** New York: Longuman Group (UK) Limited. Vol. 22, No. 3, PP. 67-69.

Simcock, M. (1993). Developing Productive Cocabulary Using the Ask and Answer Technique." ***Guidelines: Aperiodical for Classroom Language Teachers.*** Vol. 15, No. 2, pp.1-7.

Taylor, L. (1990). ***Teaching Learning Vocabulary.*** New York: Prentice Hall.

Ur.P. (1996). ***A Course in Language Teaching: Practice and Theory.*** Cambridge: Cambridge University Press.

Wallace, M. (1982). ***Teaching Vocabulary: Practical.*** Oxford: Heinemann Education Book Ltd.

Wilkins. D.A. (1972) ***Linguistics and Language Teaching.*** London: Edward Arnold.

Wilkins, A. (1982). ***Linguistics in Language Teaching.*** London: The English Language Book Society and Edward Arnold (Publishers) Ltd.

Yule. G. (1996) ***The Study of Languages (2nd ed.).*** Cambridge: Cambridge University Press

# ሙዳየ ቃላት

| ቃሉ /ሐረጉ በመገኛ ቋንቋው | የአማርኛው አቻው |
|---|---|
| Availability | መገኘት |
| Billngual Dictionary | ልሳነ ክልኤ መዝገበ ቃላት |
| Collocations | አብሮ ተሰላፊ |
| Connotation | ፍካሬ |
| Denotation | እማሬ |
| Derivation | ምስረታ |
| Frequency | ድግግሞሽ |
| Guessing Clues | ለመገመት የሚረዱን ፍንጮች |
| Hyponym | አጠቃሊ |
| Inflection | ርባታ |
| Learnability/ Teachability | ለመማር/ለማስተማር ያላቸው አመቺነት |
| Monolingual Dictionary | ለሳነ ዋህድ |
| Morphological Clue | ሥነምዕላዳዊ ፍንጭ |
| Personalized Groups | ግላዊ ፍላጎትን መሠረት ያደገ ፍረጃ |
| Real-World Groups | የተለመደ /የገሃዱ ዓለም ፍረጃ |
| Receptive Knowledge | የቅበላ ዕውቀት |
| Standard Monolingual Dictionary | ደረጃውን የጠበቀ ልሳነ ዋህድ መዝገበ ቃላት |
| Text | አሃድ |
| Word Structure | የቃላት መዋቅር |
| Corpus | ስብስብ |

# አባሪዎች

# አባሪ "ሀ"

አስረጅ 1

ለምሳሌ በመጽሐፉ ውስጥ በገፅ 205 ያለውን የቃላት ትምህርት መልመጃ ቀጥለን እንመልከት፡፡

ለ. በሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት ዐውደንባባዊ ትርጉማቸውን ፈልግላቸው

-----------1. እግራቸውን ለቀለቀቻቸው፡፡

ሀ. ሳመቻቸው ሐ. አጠበቻቸው

ለ. ከለከላቻቸው መ. አሸቻቸው

----------2. የመንግስት ተቋሞች በከተሞች ብቻ ተወስነው አይቀሩም፡፡

ሀ. ቢሮዎች ሐ. ምስሶዎች

ለ. መሪዎች መ. ድርጅቶች

-----------3. የሚጣፍጥ ምግብ የተመገብኩበት ጊዜ ትዝ አይለኝም፡፡

ሀ. አልታዘዘውም ሐ. አላስታውስም

ለ. አልወደውም መ. አይማርከኝም

------------4. የገጠሩ ህዝባችንን ኑሮ ለማሳደግ አዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲያችን ወሳኝ ነው፡፡

ሀ. ለመፍጠር ሐ. ለማተለቅ

ለ. ለመስራት መ. ለማሻሻል

------------5. እንዴታ አሳምሬ ነው እንጂ፡፡

ሀ. በእውነት ሐ. በሃቅ አቀነጃጅቼ

ለ. በትክክል ለይቼ መ. ሶስቱም

አስረጅ 2

ሠ. ከዚህ በታች ለተሰጡ ቃላት ከተሰጡት አማራጮች መሃል ይበልጥ የሚቀራረበውን ትርጉም በመምረጥ የመልሱን ሆሄ ብቻ ፃፉ፡፡

1. ልሳን

ሀ. አንደበት ለ. ምላስ ሐ. ቋንቋ መ. ሁሉም

2. ቅርናት

ሀ. ድክመት ለ. ጥንካሬ ሐ. አድሃሪነት መ. መጥፎ ሽታ

3. ምራት

ሀ. የባል ወንድም ሚስት
ለ. የራስ ሚስት
ሐ. የልጅ ሚስት
መ. የእኅት ሚስት

4. ዋርሳ

ሀ. የባል ወንድም
ለ. የእማት ወንድም
ሐ. የሚዜ ወንድም
መ. የእኅት ወንድም

5. ብላቴና

ሀ. ሽማግሌ ለ. ጎረምሳ ሐ. ወጣት መ. ህፃን ልጅ

6. ዳንዴ

ሀ. ቀማኛ ለ. ሰላማዊ ሐ. ደንዳና መ. ሃይለኛ

7. ጉማ

ሀ. ዕዳ ለ. የነፍስ ዋጋ ሐ. የነፍስ ካሳ መ. "ለ" እና "ሐ"

8. ቤተኛ

ሀ. ባለቤት ለ. የኛ ቤት ሐ. የቅርብ ወዳጅ መ. ቤተዘመድ

9. ኮበሌ

ሀ. ሽማግሌ ለ. ጎረምሳ ሐ. ወጣት መ. ህፃን ልጅ

10.ባይተዋር

ሀ. እንግዳ ለ. ጠላት ሐ. ዘዋሪ መ. ባለብዙ ዘመድ

አስረጅ 3

ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ፈልጉ

1. ሊንቀለቀል
2. ሲገፉ
3. ለወግ
4. ለቡረቃ
5. ቆፈን
6. ዱር
7. ሲድህ
8. አኮራመተው

አስረጅ 4

ለ. ለሚከተሉት ቃላት ቀጥተኛ ትርጉም ፈልጎላቸው

1. ስጋጃ
2. ቀለም
3. አዲስ
4. የተስማማ
5. አፋፍ
6. ህይወት

አስረጅ 5

መ. ቀጥሎ በ"ሀ" ስር የተሰጠትን በ"ለ" ስር ከተሰጡት ጋር አዛምዷቸው

| "ሀ" | "ለ" |
| --- | --- |
| ---------1. ተቆረቆረ | ሀ. አላፊው |
| ---------2. ለመጎብኘት | ለ.ማዕከል |
| ---------3. ሳይፈርስ | ሐ. ተመሰረተ |

----------4. ገናና

----------5 እምብርት

----------6. መተክያ

----------7. ያወሳል

----------8. ቀደምት

----------9 መለክያው

----------10. ትወስናለች

መ. ሳይወድም

ሠ. መመዘኛው

ረ. እውቅ

ሰ. ትጎራበታለች

ሸ. መለወጫ

ቀ.ይዘከራል

በ. ለማየት

አስረጅ 6፡- የቃላትን አንደበታዊና ጽሑፋዊ ባህርይ የሚያሳይ መልመጃ

ሀ. ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጎች በምንባቡ መሰረት ትርጉም ሲሆኑ የሚችሉትን ከ"ለ" ስር በመፈለግ አዛምዱ

ሀ

---------1. ስንዴ

----------2. ዝናቡ ሲፈፀም

----------3. ህብር

----------4. ያበቦች ሽታ

---------5. ሙጃ

----------6. ሙጃ

----------7 ሰርዶ

----------8. መስክ

ለ

ሀ. ስር

ለ. አረም

ሐ. ቀለም

መ. አሸተ

ሠ.መአዛ

ረ. ውህድ

ሰ. ሜዳ

ሸ. ደመናው ሲሸሽ (ገጽ፡7)

አስረጅ 7

ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚኖራቸውን የትርጉም ለውጥ የሚመለከት መልመጃ

ሰ. የሚከተሉት ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚሰጡትን ትርጉም ለይታችሁ ፃፉ

1. ይገባል
2. መሳል
3. ሳማ
5. በራ
6. እያለ
7. ተጋጩ
8. ወጡ
9. ከፋኝ
10. አብረው

4. ይባላል

(ገፅ 10)

አስረጅ 8

የትርጉም ልዩነት በዓረፍተ ነገር እንዲያሳዩ የሚጠይቅ መልመጃዎች

ረ. የሚከተሉት ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነገሩ የሚኖራቸውን ትርጉም ዐረፍተነገሮችን በመስራት አሳዩ

1. መላስ ሀ) ማር መላስ ወይም መቅመስ ጥሩ ነው፡፡

ለ) ጥጆች በላሞች መላስን ይወሳሉ፡፡

2. መጨረስ ሀ) ______________________

ለ) ______________________

3. መመደብ ሀ) ______________________

ለ) ______________________

4. መመርመር ሀ) ______________________

ለ ______________________

5. መላክ ሀ) ______________________

ለ)______________________

6. መሳል ሀ) ______________________

ለ)______________________

አስረጅ 9

ሠ. በሚከተለው ምሳሌ መሰረት የተሰጡዋችሁን ቃላት በልዩ ልዩ ቅፅ ፃፉ፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አወቀ | አዋቂ | ማወቅ | ታወቀ | ማወቂያ |
| 2. | -------------- | ፈጣሪ | ---------- | ------------ | --------- |
| 3. | -------------- | -------------- | መገበር | ------------ | --------- |
| 4. | -------------- | ------------ | ----------- | ----------- | መመስከርያ |
| 5. | -------------- | ------------ | ----------- | ታየ | ---------- |
| 6. | -------------- | ------------ | ----------- | ---------- | መጠጫ |
| 7. | -------------- | ------------ | ----------- | ----------- | ------------ |
| 8. | -------------- | ተጫዋች | ------------ | ----------- | ----------- |
| 9. | አወከ | -------------- | ------------ | ----------- | ------------ |
| 10. | -------------- | ------------ | ----------- | ----------- | ማቆያ |

(ገጽ 106)

አስረጅ 10

ለ. ለሚከተሉት ቃላት የሚያስገኙትን ትርጉም (እማሬያዊ ትርጉማቸውን) ፈልጋችሁ ፃፉ::

1. ሰምሮ
2. ባህሪይ
3. አውራጅ
4. በመዝለቅ
5. ይለምናሉ
6. ይወርዳሉ
7. የተበረከታላቸው
8. ይሰናበታሉ::

ገጽ(250)

አስረጅ 11

ረ. በ "ሀ" ስር የሚገኙትን ቃላት በ"ለ" ስር ከሚገኙት ጋር በማጣመር ትክክለኛውን ጥምር ቃል መስርቱ::

ምሳሌ

ጥምር ቃል = ደመ ነፍስ

| "ሀ" | "ለ" | |
|---|---|---|
| ቃል | ቃል | 1.__________ |
| በግ | ድርብ | 2.__________ |
| ማታ | ደረቅ | 3.__________ |
| ስር | ምድር | 4.__________ |
| እጥፍ | ልል | 5.__________ |
| አንድ | ፈጅ | 6.__________ |
| ህግ | አንድ | 7.__________ |
| ስርአት | ነፍስ | 8.__________ |
| ዓይን | መንግስት | 9.__________ |
| ደመ | ትምህርት | 10.__________ |
| ልብ | ማታ | 11.__________ |

አስረጅ 12

ገጽ 25

ሐ ቀጥሎ ከምንባብ ውስጥ ለተውጣጡ ዘይቤያዊ አገላለጾች በተራ አባባል ተኳቸው::

ምሳሌ:- 1. እጅ የሚያስቀረጥም = የሚጣፍጥ

2. ቀውጢ ሰዓት--------------------------------

3. ዕድሜ ባደቀቀው ----------------------------

4. የሕይወት ጣእም ----------------------------

5. በእጅ በደጅ ---------------------------------

6. የዶሮ አይን --------------------------------

7. አንድ ፍሬ ልጅ ---------------------------

8. ባዶ ቤት -----------------------------------

አስረጅ 13

መልመጃ ሶስት

ሀ. ት.ል.ማ በአሁኑ ወቅት በየአካባቢያችሁ የሚያንጸቸው የልማት ተቋማት ወይም ማህበራዊ አገልግሎቶች ካሉ የሚሰጡትን ግልጋሎት አስመልክታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ለ. የምንባቡን መልእክት በጽሑፍ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብባለቸው

ሐ. ደስ በሚላችሁ ርእስ ላይ የጽሕፈትን ስርአት የተከተል ድርሰት በማዘጋጀት ለመምህራችሁ አሳዩ።

መ. መምህራችሁ በቃል የሚነግሯችሁን ተረት፣ ታሪክ ወይም አጭር ልቦለድ በጥሞና ካዳመጣችሁ በኋላ በራሳችሁ አባባል መልሳችሁ ተናገሩ።

አስረጅ 14

ረ. ቀጥሎ የተሰጡትን ቃላት በመዝገበ ቃላት ላይ በሚገኘው ሆሄ ተራ መሰረት በቅደም ተከተል ደርድራችሁ ጻፉ

| | | |
|---|---|---|
| 1. ትግራይ | 5. መቀሌ | 9. ፈረደ |
| 2. አክሱም | 6. ዩሃንስ | |
| 3. ይሐ | 7. ነጋሶ | |
| 4. ሳባ | 8. ሐውልቱ | |

# አባሪ "ለ"

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሑፍ ትምህርት ክፍል

## በትግራይ ክልል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መመህራን የሚሞላ የፅሑፍ መጠይቅ

ውድ መምህር! የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በትግራይ ክልል ግልጋሎት እየሰጠ ያለውን የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሐፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ አጠቃላይ ገፅታ ለመመርመር የሚያግዙ መረጃዎችን መሰብሰብ ነው።

ጥናቱ ከታቀደለት ግብ ለመድረስ ከናንተ የሚገኙ መረጃዎች ማስደገፍ ተገቢ እንደሆነ ታምኖበታል። በመሆኑም የቀረቡልዎትን ጥያቄዎች በጥሞና ተመልክተው ትክክለኛ ምላሽ እንዲሰጡ በትህትና እጠይቃለሁ። እርስዎ ከሚሰጡት መልስ የሚገኘው መረጃ ለታቀደው ጥናት ብቻ የሚውል መሆኑን አረጋግጣለሁ።ውድ ጊዜዎን ሰውተው መጠይቁን በመሙላት ስለተባበሩኝ ከልቤ አመሰግናለሁ።

<u>ማሳሰቢያ</u>

- በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም
- መጠይቁ የሚሞላው በግል ነው። ከሌላ ሰው ጋር ተወያይቶ መሙላት የጥናቱን ውጤት ሊያዛባ ይችላል።

<u>ክፍል አንድ</u>

- ከዚህ በታች የርስዎን ዳራዊ መረጃዎች የሚሹ ጥያቄዎች ቀርበዋል። መልስዎን በጥያቄዎቹ አንፃር በተሰጡ ክፍት ቦታዎች ላይ ያስፍሩ።

1. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም ______________________________
2. ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት፣ ክልል______________ዞን ____________
   ወረዳ___________ከተማ__________
3. ፆታ_________________
4. የአገልግሎት ዘመን፡-በመምህርነት___________በሌላ___________
5. የትምህርት ደረጃ_____________
6. የሰለጠኑበት ትምህርት፡-
   አብይ____________________ንኡስ_______________
7. ከ1990-2003 ዓ.ም ያስተማሩባቸውን የክፍል ደረጃዎች የ(x)ምልክት በማድረግ ያመልክቱ።
   7.1 5ኛ ክፍል_______________________
   7.2 6 ኛ ክፍል__________________
   7.3 7ኛ ክፍል_______________________
   7.4 8ኛ ክፍል __________________
8. የአፍ መፍቻ ቋንቋዎ __________ሌላ ቋንቋ________________

<u>ክፍል ሁለት</u>

ቀጥሎ በቀረበልዎ ሰንጠረዥ ውስጥ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሐፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ አጠቃላይ ገፅታ የሚፈትሹ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በጥያቄዎቹ የቀረቡት ሃሳቦች አንድ በአንድ በማጤን ሙሉ በሙሉ የሚስማሙ ከሆነ "በጣ እስማማለሁ" በተወሰነ ደረጃ የሚስማሙ ከሆነ "እስማማለሁ"፣ ሃሳቡን በተወሰነ ደረጃ የማይቀበሉት ከሆነ "አልስማማም" ፤ሃሳቡን ፈፅሞ የማይቀበሉት ከሆነ "ፈፅሞ

አልስማማም" በማለት በአማራጮች ትይዩ ይህን /x/ ምልክት በማድረግ ያመልክቱ። ለአንድ ሃሳብ አንድ ምርጫ ብቻ መምረጥዎንም ያረጋግጡ።

| የጥያቄ ቁጥር | ጥያቄዎች | በጣም እስማማ | እስማማ ለሁ | አልስማ ማም | ፈፅሞ አልስማ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከሌሎች የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች አንፃር ሲታይ መፅሐፉ ለቃላት ትምህርት በቂ ሽፋን ሰጥቷል። | | | | |
| 2 | የመፅሐፉ የቃላት ትምህርት ይዘት የክፍል ደረጃውን አይመጥንም። | | | | |

- መፅሐፉ ለቃላት ትምህርት የሰጠውን ሽፋንና ለክፍሉ ደረጃ ለተማሪዎች ያለው መጣኝነት ያሎችን አስተያየት

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | <u>የመፅሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት</u> | | | | |
| 3.1 | ቃላቱ የሚያወሱትን ርእስ ጉዳይ ያገናዘበ ነው። | | | | |
| 3.2 | ከከባድ ወደ ቀላል የሚሄድ ነው። | | | | |
| 3.3 | የቃላቱን ቅርፃዊ ባህሪ ያገናዘበ አይደለም። | | | | |
| 3.4 | የቃላቱን አውዳዊ ዝምድና ያገናዘበ ነው። | | | | |
| 3.5 | በመፅሐፉ መጀመሪያ አካባቢ የተለመዱ ነጠላ ቃላት ቀርበዋል አደረጃጃት ስልትን ተከትሏል። | | | | |
| 3.6 | በመፅሐፉ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ይታይባቸዋል። | | | | |
| 3.7 | መፅሐፉ ለትምህርት ዕርከኑ ከሚመጥኑ ነጠላ ቃላት በመነሳት በጥምርነት ወደሚፈጠሩ ቃላት የሚያመራ አደረጃጀት ስልትን ተከትሏል። | | | | |
| 3.8 | በጽሐፉ የቃላት ትምህርት ቅርፅን መሠረት ያደረገ አደርጃጀትን ተከትሏል። | | | | |
| 4<br>4.1 | <u>የመፅሐፉ የቃላት የፍቺና የአውድ ዝምድና አቀራረብ</u><br>አብዛኞቹ አረፍተ ነገሮች የአዳዲስ ቃላትን ፍች ለመረዳት የሚያስችሉ አውዳዊ ፍንጮች አሏቸው። | | | | |
| 4.2 | ቃላት በአብዛኛው በአውድ ተደግፈው አልቀረቡም | | | | |
| 4.3 | ቃላትን ለማስተማር የቀረቡ ዓረፍተነገሮች ረዣዥም ናቸው። | | | | |
| 4.4 | ቃላትን ለማስተማር የቀረቡ ዓረፍተነገሮች አጫጭርና በሃረግ መልክ የቀረቡ አይደሉም። | | | | |
| 4.5 | ቃላት ከአገባባቸው ፍቺያቸው እንዲተነበይ ለማድረግ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የቀረቡ ዓ.ነገራዊ አውዶች በመነሳት ለመገመት የሚያስችሉ ናቸው። | | | | |
| 4.6 | ቃላት የቀረቡባቸው ዓረፍተነገሮች የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመገመት የሚያስችሉ አይደሉም። | | | | |

- በመፅሐፉ የቃላት ዓውዳዊ አቀራረብ ያለዎትን አስተያየት ባጭሩ ይግለፁ

________________________________________

________________________________________

በመፅሐፉ ውስጥ አብዛኞቹ የቃላትን የእርባታና ምስረታ ሂደት ተመርኩዘው የቀረቡ ቃላት፣ የቅጥያዎቹን ተግባርና ቃላቱ ቅጥያዎቹን ተቀብለው ያሳዩትን የቅርፅና የፍቺ ለውጥ ለመዳሰስ በሚያስችል መንገድ ቀርቧል።

- ስለ መፅሐፉ እርባታና ምስረታ አቀራረብ ያሎትን አስተያየት ባጭሩ ይግለፁ።

________________________________________

________________________________________

________________________________________

በመፅሐፉ ውስጥ በአብዛኛው የቃላትን እማርያዊ ፍካርያዊ፣ ፈሊጥና ዘይቤ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቷቸው በቀላሉ ለመረዳትና አፍልቆ ለመጠቀም በሚያስችል መልኩ ቀርቧል።

- በመፅሐፉ የቃላትና የሃረጎችን አጠቃቀም ለተማሪዎች በማሳየት ረገድ ያበረከተው አስተዋፅኦ ባጭሩ ይገለፅ። __________________________

________________________________________

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | የቃላት የጥቅልና ዝርዝር ፍቺ ዝምድና ትምህርት አቀራረብ የቃላቱን ዝምድና ለመለየትና ለመጠቀም የሚያስችል ነው። | | | | |
| 6 | በመፅሐፉ ንበት ሊያመጣ የሚችለውን የፍች ለውጥና የቃላትን የንግግርና የፅሑፍ ባህሪያት የሚያስገነዝቡ ይዘቶች አልተካተቱም። | | | | |
| 7 | በመጽሐፉ ቃላት የሚረቡበትንና የሚመሰረቱበትን ሂደት ተመርኩዘው የሚቀርቡ ቃላት የቅጥያዎቹ ተግባርና ቃላቱ ቅጣያዎችን ተቀብለው ያሳዩትን የቅርጽና የፍቺ ለውጥ ለመዳሰስ በሚያስችል መንገድ ቀርበዋል። | | | | |
| 8 | <u>የቃላት ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብ በተመለከተ</u> | | | | |
| 8.1 | በመፅሐፉ የቃላት ትምህርት መመርያዎች በተገቢ ማብራርያዎችና ምሳሌዎች ተደግፈው የቀረቡበት ደረጃ ዝቅተኛ የሉም። | | | | |
| 8.2 | በመፅሐፉ በመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ላይ ያተኮሩ መልመጃዎች የመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ጥበብን የማለማመድ ብቃታቸው ዝቅተኛ ነው። | | | | |

.ስለቃላት ትምህርት መልመጃዎች አራረብ ያሎትን አስተያየት ይግለፁ

______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | በመጽሐፉ ውስጥ የቃላት እማሬ/ፍካሬ፣ ፈሊጥና ዘይቤ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቷቸው በቀላሉ ለመረዳትና አፍልቆ ለመጠቀም የሚያስችል መንገድ ቀርበዋል። | | | | | |
| 10. | የቃላት ትምህርት ከሌሎች ክሂሎችና ከሌሎች የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ጋር ያለው ጥምረት በተመለከተ | | | | | |
| 10.1 | ከማደመጥ ክሂል ትምህርት ጋር ተጣምሮ ቀርቧል። | | | | | |
| 10.2 | ከንግግር ክሂል ጋር ተጣምሮ አልቀረበም። | | | | | |
| 10.3 | ከአንብቦ መረዳት ትምህርት ጋር ተጣምሮ ቀርቧል። | | | | | |
| 10.4 | ከፅህፈት ክሂል ጋር ተጣምሮ አልቀረበም ። | | | | | |

- ስለ መፅሐፉ የቃላት ትምህርት አራረብ ከሌሎች ክሂሎች ጋር ስላለው ጥምረት ያሎትን አስተያየትይግለፁ ::

______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
____________

11. በመፅሃፉ በዚህ መጠይቅ ያልተዳሰሰ የቃላት ትምህርት አደረጃጀትና አቀራረብ ችግር የሚሉትን ይግለፁ ______________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________

12. በመፅሐፉ ውስጥ የቃላት ትምህርት የይዘት በአመራረጥ፣ አቀራረብና አደረጃጀት በተመለከተ ያሎትን አጠቃላይ አስተያየት ባጭሩ ይዘርዝሩ

______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________

# አባሪ "ሐ"

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል
## በትግራይ ክልል በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የፅሑፍ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በትግራይ ክልል ግልጋሎት እየሰጠ ያለውን የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሐፋችሁ የቃላት ትምህርት አቀራረብ አጠቃላይ ገፅታ ለመመርመር የሚያግዙ መረጃዎችን መሰብሰብ ነው። ጥናቱ ከታቀደለት ግብ ለመድረስ ከናንተ የሚገኙ መረጃዎች ማስደገፍ ተገቢ እንደሆነ ታምኖበታል። በመሆኑም የቀረቡላችሁን መጠይቆች በጥሞና ተመልክታችሁ ትክክለኛ ምላሽ እንድትሰጡ በትህትና እጠይቃለሁ። እናንተ ከምትሰጡት መልስ የሚገኘው መረጃ ለታቀደው ጥናት ብቻ የሚውል መሆኑን አረጋግጣለሁ።
ውድ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ መጠይቁን በመሙላት ስለተባበራችሁኝ አመሰግናለሁ።

ማሳሰቢያ

- በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም
- መጠይቁ የሚሞላው በግል ነው። ከሌለ ሰው ጋር ተወያይቶ መሙላት የጥናቱን ውጤት ሊያዛባ ይችላል።
- መጠይቁ ከተገለፀው አላማ ውጭ አያገለግልም።

ክፍል አንድ

ከዚህ በታች የእናንተን የግል መረጃዎች የሚሹ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በመሆኑም መልሳችሁን ከጥያቄዎቹ አንፃር ባሉ ክፍት ባታዎች ላይ አስፍሩ።

1. የትምህርት ቤቱ ስም________________________
2. የክፍል ደረጃ _______________ምድብ (Section)________________________
3. ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ክልል__________ ዞን____________________
   ወረዳ________ከተማ_______________________
4. ፆታ______________________
5. የአፍ መፍቻ ቋንቋ__________

ክፍል ሁለት

ቀጥሎ በቀረበላችሁ ሰንጠረዥ ውስጥ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሐፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ አጠቀላይ ገፅታ የሚፈትሹ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በጥያቄዎቹ የቀረቡት ሃሳቦች አንድ በአንድ በማጤን መሉ በሙሉ የምትስማሙ ከሆነ "በጣም እስማማለሁ"፤ሃሳቡ በተወሰነ ደረጃ የምትቀበሉት ከሆነ" እስማማለሁ"፤ ሃሳቡ በተወሰነ ደረጃ የማትቀበሉት ከሆነ "አልስማማም"፣ ሃሳቡ ፈፅሞ የማተቀበሉት ከሆነ "ፈፅሞ አልስማማም" በማለት በአማራጮች ትይዩ ይህንን ምልክት በማድረግ /x/ አመልክቱ።

ለአንድ ሃሳብ አንድ ምርጫ ብቻ መምረጣችሁ አረጋገጡ።

| የጥያቄ ቁጥር | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ፈፅሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በመፅሐፉ ውስጥ የቀረቡ የቃላት ትምህርት መልመጃዎች በአብዛኛው ከእለት ተእለት ህይወቴ ጋር የተያያዙ ናቸው። | | | | |
| 2 | በመጽሐፍ ውስጥ በአብዛኛው የቃላት ፍቺ ትምህርት በአውድ የቀረቡ አይደሉም። | | | | |
| 3 | የቃላት ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብ በተብራሩና በምሳሌ በተደገፉ መመሪያዎች የታገዘ አይደለም። | | | | |
| 4 | በመፅሐፉ ውስጥ ያሉት የጥምርና የመህፃረ ቃላት አቀራረብ አመሰራረታቸውን ለመረዳት አስችሎኛል። | | | | |
| 5 | በመፅሐፉ ፈሊጣዊ ቃላት የቀረቡበት ስልት ፈሊጦችን ለመረዳትና አስታውሶ ለመጠቀም አያስችልም። | | | | |
| 6 | በመፅሐፉ ውስጥ የቅጥያዎችና የዋና ቃሎች አቀራረብ ቅጥያዎችንና ዋና ቃሉን ለመለየትና ፍቻቸውን ለመረዳት አግዞኛል። | | | | |
| 7 | በመጽሐፉ የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ የፍቺ ዝምድና ትምህርት ቃላቱን ለመለየትና ለመጠቀም በሚያስችል መንገድ የቀረበ ነው። | | | | |
| 8 | በመጽሐፉ ውስጥ ቃላት የቀረቡባቸው ዓረፍተ ነገራዊ ዐውዶች በአብዛኛው ፍቻቸው ለመገመት አግዞኛል ። | | | | |
| 9 | በመጽሐፉ ቃላት ከመዝገበ ቃላት ውስጥ እንዴት ፈልጌ ማግኘት እንዳለብኝ ተምሬአለሁ። | | | | |
| 10 | የቃላት የፍቺ ተመሳሰሎና ተቃርኖ ትምህርት የቀረበው በአውድ አይደለም። | | | | |
| 11 | በመጽሐፉ መጀመሪያ አካባቢ ያሉ ቃላት ወደ መጨረሻ ካሉት ለመረዳት ያስቸግራሉ። | | | | |
| 12 | መጽሐፉ ውስጥ ያሉት የጥምርና የምህፃረ ቃላት አቀራረብ የቃላትን የአመሠራረት ሥርአት የመረዳት አግዞኛል። | | | | |

# አባሪ "መ"

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር
## የኢትዩጲያ ቋንቋዎችና ስለጹሁፍ ትምህርት ክፍል
## ለትግራይ ክልል 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ
## መጽሃፍ አዘጋጆች የቀረበ ቃለ መጠይቅ

መግቢያ ፡- የዚህ ቃለመጠይቅ ዋና አላማ በመጀመሪያ በ1990 እና በ2001 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በስራ ላይ ያለው የትግራይ ክልል የ8ኛ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት አዘገጃጀትና አቀራረብን መገምገም የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን መሰብሰብ ነው። ለዚህ ጥናተ መሳካት ደግሞ ከእርሰዎ ፤በመጽሃፍ ዝግጅት ከተካፈሉ ባለሙያዎች የሚገኙ መረጃዎች ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርጉ አምናለሁ።
ስለዚህ ቀጥዪ ለማቀርብልዎ ጥያቄዎች ትክክለኛ ምላሽ እንዲሰጡኝ በትህትና እጠይቃለሁ።በበኩሌ እርሰዎ ከሚሰጡኝ ምላሽ የማገኘውን መረጃ ለታቀደው ጥናት ብቻ እንደማውል አረጋግጥሎታለሁ።
የማቀርብልዎትን ጥያቄዎች ለመመለስ ፍቃደኛ ሆነው ይህንን ጊዜ ስለሰጡኝ በቅድሚያ አመሰግናለው።

መሪ ጥያቄዎች

1. በቅድሚያ ሰምዎን፤ የትምህርት ደረጃዎችን፤ የሰለጠኑበትን የትምህርት መስክ ፤የአገልግሎት ዘመንዎን፤ የትና በምን አይነት የስራ ሃላፊነት ላይ እንዳገለገሉ ቢገልጹልኝ።
2. ከ1990 ዓ.ም በፊት በመማሪያ መጽሃፍ ዝግጅትም ሆነ በሌላ የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት ተከፍለው ከሆነ መቼ በየትኛው ደረጃና በዝግጅ ቱ የነበሮትን ሃላፊነት ቢነግሩኝ።
3. የትግራይ የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ ስታዘጋጁ መሰረት ያደረጋችኃቸውን ሰነዶች ቢገልጹልኝ።
4. በመጽሃፍ የተካተቱት ቃላት የተመረጡበት መስፈርት ምን ነበር?
5. ቃላቱን ለማደራጀትና በመልመጃ መልክ ለመቅረጽ የተጠቀማችሁበት መስፈርት ምን ነበር?
6. በመጽሃፉ ውስጥ ያለው የቃላት ትምህርት አቀራረብ ተከታታይነት እንዲኖረው የተደረገ ጥረት ቢገልጹልኝ?
7. በመጽሃፉ ውስጥ ቃላት በአብዛኛው ተጣምረው የቀረቡት ከየትኛው የቋንቋ ክሂል ወይም የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ጋር ነው? ለምን?
8. በመማሪያ መጽሃፉ መልመጃዎች ተቀርጸውላቸው የቀረቡ ቃላት የተውጣጡት በመጽሃፍቱ ከተካተቱ ምንባቦች ውስጥ ነው ወይስ ከምንባቦች ውጪም የገቡ ቃላት አሉ?

ጊዜዎን ሰውተው ለሰጡኝ ቃለምልልስ በድጋሚ አመስግናለሁ።

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የኔ መሆኑንና በጽሑፉ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

ስም ሞላ አጽብሃ

ፊርማ ____________________


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋክልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር
አዲስ አበባ